በግሪክ በፀሃይ የተቃጠለ ማለት ‹‹ካውማትዲዞ (kawmatdizo)›› ነው:: ‹‹ፊት›› ማለት ደግሞ ‹‹ፔሪካሉፕቶ (perikalupto)›› ነው:: ስለዚህ በግሪክ ‹‹ፊቱ የተቃጠለ›› ማለት ‹‹ካውማትዲዞ-ፔሪካሉፕቶ›› ነው:: (strong`s Greek Lexicon,p.239 and p.4020) በዚህ ሁኔታ "ኢትዮጵያ" የሚለው ቃል ‹‹ካውማትዲዞ-ፔሪካሉፕቶ›› መሆን ነበረበት:: እኛ ኢትዮጵያውያንም ‹‹ካውማትዲዞ ፔሪካሉፕቶኢያንስ›› ተብለን መጠራት ነበረብን ማለት ነው:: ግሪክ ‹‹ኢትዮጵያ›› ብላ ስየመችን ብሎ ማሰብ ምን ያህል አሳፋሪ እንደሆነ እዩ! ፍፁም ሃሰት ነው::

ሌላው ክርክር በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ "ኢትዮጵያ" የሚለው ቃል ‹‹ኩሽ››ን ተኪ ነው የሚለው ነው::(27) ኩሽ በጸታው ተባዕታይ ሲሆን ኢትዮጵያ ግን በእንስታይ ጾታ ነው የምትነገረው:: ንጉሥ ዳዊት በመዝሙሩ ላይ ኢትዮጵያን እንደ ኩሽ በ‹‹ተባዕታይ ጾታ›› አልጠራትም:: ‹‹ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች››(መዝሙር 68:31) አለ እንጂ ‹‹ኩሽ እጁን ወደ ግዚአብሔር ይዘረጋል›› አላለም:: "ኢትየጵያ" እና ‹‹ኩሽ›› በሚሉት ቃላት ላይ ብንከራከር እንኩዋ በዚህ ትንቢት ‹‹እሷ›› በሚለው ሃሳብ ላይ ግን ልንከራከር አንችልም:: ማንም እንደሚስማማበት በዚህ ትንቢት ውስጥ ተውላጠ-ስሙ ‹‹እሷ›› ነው እንጂ ‹‹እሱ›› አይደለም:: ሌሎች ተጨማሪ ምሳሌዎችን መጥቀስ ቢቻልም ለመነሻ በዚህ ላብቃ::

ኢትኤል፣ "ኢትዮጵ" የሚል መለኮታዊ ስም ከወጣለት በሁዋላ ከኢየሩሳሌም ወደ ኩሻዊቷ ምድር አሁን ‹‹ኢትዮጵያ›› ተብላ ወደምትጠራዋ አገር የመጣበት ምክንያት እንደሚከተለው ነው:: በርግጥ አመጣጡ ተልዕኮ ነበረው::

አክሱማይ ሲራክ በተባለው ከአንድ ሺ ዓመት በፊት በነበረው የታሪክ ሰው በተላለፈልን፣ እንዲሁም የአንዳ-ቤቱ ዘግዱር አማካኝነት በደረሱን ከሦስት ሺ ዐመታት በላይ ባስቆጠሩት ጽሁፎች (28) ውስጥ በተለይም በ *መጽሐፈ- ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ* የጥንት ታሪካችን መረጃ መሰረት ሁለቱም፣ ኦሮሞም አማራም፣ እንዲሁም ሁሉም ኢትዮጵያውያን የአንድ አባትና እናት ልጆች ናቸው:: ያ የጥንት አባታችን መልከጼዴቅ ይባላል:: እርሱም የሰላምና የጽድቅ ንጉሥ፣





እንዲሁም በምድሪቱ ላይ ከፍተኛው የእግዚአብሔር ካሕን የነበረ፣ ኢየሩሳሌምን የገነባ፣ አብርሃምና ሌሎችም ነገሥታት ጎንበስ ብለው እጅ የነሱት እና ምርቃቱን ለማግኘት ዓሥራት የገበሩለት ሰው ነው:: (ዕብ. 7:127) የእሱ ሚስት እናታችን ሳሌም ነበረች:: አባታችን የአሳደጋትን ከተማ ለእናታችን መታሰቢያ ሳሌም ወይም እየሩሳሌም አላት:: ሰማያዊ ሰላም ማለት ነው:: ይህ አፈ-ታሪክ አይደለም፤ ተረትም አይደለም:: የተመዘገበ እውነተኛ ታሪክ እንጂ::

ከእየሱስ ክርስቶስ ልደት 2000 ዓመት በፊት (አሁን ከ4000 ዓመት በፊት ማለት ነው) እግዚአብሔር መልከጼዴቅን አንድ ትዕዛዝ አዘዘው:: ይኸውም ልጁን ኢትኤልን ቆየት ብሎ በእግዚአብሔር በራሱ ኢትዮጵ የተባለውን የዓባይ ወንዝ ምንጭ ወደ ሆነው ወደ ጣና ደሴት ሄዶ ይሰፍር ዘንድ እንዲልከው ነበር:: ‹‹ኢትኤል›› ማለት ‹‹የእግዚአብሔር ስጦታ›› ማለት ነው::

እግዚአብሔር ኢትኤልን ወደ ኢትዮጵያ ሲልከው እግዚአብሔር ወልድ (እየሱስ ክርስቶስ፣ መሲሕ፣ ሙስሊሞች ደግሞ ኢሣ፣ ነቢይ የሚሉት) ከ2000 ዓመት በሁዋላ ሰው ሆኖ በቤተልሔም ሲወለድ የኢትኤል ዝርያዎችን ወደ ቤተልሔም ሲመራቸው በኢትዮጵያ በሚወጣው ኮከብ እየተመሩ የኢትዮጵያን ስጦታ ቢጫ ወርቅ፣ ከርቤና እጣን እንደሚያመጡለት አስቀደሞ ሲያመለክት ነው:: በዚሁ መሰረት ኢቴኤል በዚያን ጊዜ የኩሽ ምድር ወደ ምትባለው ወደ ኢትዮጵያ መጣና ዛሬ ጎጃም በሚባለው ቦታ ሰፈረ:: እግዚአብሔርም ስሙን ከኢትኤል ወደ ኢትዮጵ ቀየረለት:: ትርጉሙም ‹‹ለእግዚአብሔር የቢጫ ወርቅ ስጦታ›› ማለት ነው:: በዚህም ኢትኤል "ኢትዮጵ" መባሉ ብቻ ሳይሆን የሰፈረባት ምድርም "ኢትዮጵያ" ትባል ጀመር:: ከ2000 ዓመታተት በሁዋላ የኢትዮጵ ተወላጆች በዚያን ጊዜዋ የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ 12 ንጉሦች ሆኑ:: እግዚአብሔር እንዳለው እየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ ስጦታ ለማበርከት ኮከቡ እየመራቸው ወደ ቤተልሄም አቀኑ::(29 )

አስራ ሁለቱም ንጉሶች አማራን፣ ኦሮሞን፣ አፋርን፣ ሶማሊን፣ ሐዲያን፣ እና ትግሬን ጨምሮ የኢትዮጵያን የተለያዩ ነገዶችን ይወክላሉ:: አማራን የወከሉ ንጉሶች አቦል፣ ጦና፣ በረካ (እነዚህ ሶስቱ

አቦል፣ ጦና እና በረካ የሚባሉት የተፈላ ቡና ደረጃዎችን ይጠቅሳሉ) እና አጎድጃ ጃቦን ይባላሉ። በጣና ሐይቅ ደሴት እና በተቀሩት የጎጃም አካባቢዎች ነበሩ። ንጉሥ መጋል የኦሮሞን ብሔር ይወክላሉ። የደርዲ እና፣ የሰገል፣ የማጂ እና የኦሮሞ ንጉሥ ነበሩ። እኝህ ታላቅ ንጉሥ እየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ከ20 ዐመታት በፊት የመደባይ ኦሮሞን ካህናትና የኦሮሞን ሰራዊት ክተት ብለው ይዘው በዛን ጊዜ በመርከብ ሥራ ስሙ-ጥር በነበሩት በአፋር ባለእጆች በተበጁ አስደናቂ መርከቦች ወደ ፖርቱጋል እና ስፔን ቀዝፈው ነበር። የጉዞአቸው ዓላማ እነዚህን አገሮች ለማስገበር እና ቅኝ ለመግዛት ነበር። (30) እቅዳቸውም በወቅቱ ተሳክቶላቸዋል። እዛ ከደረሱም በሁዋላ አፋር ውስጥ የነበረችውን የባህር ዳር ተርሴስን ለማስታወስ የእስፔንን ባህር ዳር ተርሴስ ብለው ሰይመዋታል። እስከ ዛሬም ድረስ ተርሴስ ትባላለች። በርግጥም ስፔን ውስጥ ያለችው ተርሴስ ወይም ታርሲስ ስምዋ ኢትዮጵያ ውስጥ በአፋር ከነበረችው ታርሲስ ወይም ተርሴስ ጋር ተመሳሳይ ነው። እቅጩን ለመናገር ንጉሥ ዳዊት በመዝሙር ላይ (31) የተርሴስ (አፋር ውስጥ) እና የደሴት ነገሥታት ስጦታ (ለእየሱስ) ያመጣሉ ይላል። ከተተነበየ ከአንድ ሺ ዓመት በሁዋላ የተፈፀመ ትንቢት ነው። ከ12ቱ ንጉሦች አንዱ የአፋር ግዛትን የሚወክለው ሙርኖ ኦፊር የተሰኘውን የአፋርን ወርቅ ከተርሴስ ይዞ ወደ ቤተ-ልሔም ተጉዟል። (32) ፖርቱጋል ሲባል ‹‹ፖርት-ጋል›› ማለትም ‹‹ፖርት ጋላ፤ የጋላ ወደብ›› ለማለት ይሆናል እያልኩ እመራመራለሁ። በዚያን ወቅት ‹‹ጋላ›› የሚለው ቃል አሉታዊ ትርጉም አልነበረውም። ጥበበ-እውቀትን እና ጠቢብነትን ነበር የሚያመለክተው። የሆነው ሆኖ ኦሮሞ ከስፔን እና ከፖርቱጋል ጋር የሆነ ግንኙነት እንደነበረው ‹‹ሴፎራ›› (በኦሮምኛው አጠራር ሰጲራ) የሚለው ቃል ያመለክታል። እነዚህ የስፔንና የፖርቱጋል ስሞች በኢንተርኔት ላይም ይገኛሉ። አባ ባሕርይ እንደ ዘገቡት የቦረና አባት ሰጲራ ነው። (33) የቦረና አባት የፖርቱጋል ወይም የስፔን ስም የሚኖረው በምን ታምር ነው? Huntingford ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ይህ ነው፦

*"ጋሎች (በኢትዮጵያ ውስጥ) ድል ከተቀዳጁ በኋላ ሁለት ፖርቹጋሎች እናርያ መጥተው ተቀመጡ። የግራኝ ወረራን ለመቀልበስ*



የኦሮሞ እና የአማራ እውነተኛው የዘር ሐረግ ምንጭ ፍቅሬ ቶሎሳ

*ገላውዲዎስን ሊረዳ የመጣውን ጦር ከመራው ከክሪስቶፎር ዳጋማ ጋር ወደ አቢሲኒያ የመጡ ሲሆኑ በባሕላዊው አጠራር ሲጲራ እና ሳጵየራ ተባሉ። ሁለተኛው የጋላ ሴት አግብቶ ምናልባትም በእናሪያ የሆነ ሹመት ሳይሰጠው አልቀረም። በ19ነኛው ክፍለ-ዘመን የተነሱ ንጉሦች የሱ (የሳጵየራ) ዝርያ ነን ብለው የማዕረግ ስማቸውንም "ሞቲ" እና "ንጉስ" ከሚሉት "ሱጴራ" ወደሚለው ቀይረዋል።"* (34)

ኢትዮጵ ሲና ከተባለችውና በሁዋላ እንቆጳግዮን (የግዮን ቢጫወርቅጌጥ) ተብላ ከተጠራችው ሚስቱ አሥር ወንዶችንና ሶስት ሴቶችን ወልዷል። ይኸውም ባልና ሚስቱ በ‹‹ቢጫ ወርቅ›› በተሞላው በግዮን ወንዝ መነሻ ላይ ከሰፈሩ በሁዋላ ነው። ወንዶቹ ልጆች ፣አቲባ፥ ቢኦር፥ ተምና፥ አቴር፥ አሻን፥ አክዚብ፥ በሪሳ፥ ቴስቢ፥ ቶላ፥ እና አዜብ ይባላሉ። (35)

የሴቶቹ ስም ሉዛ፤ ሚልካ እና ሱባ ናቸው። ከኢትዮጵ ወንዶች ልጆች አንዱ እላይ እንደ ሰፈረው ቶላ ይባላል። የሚገርመኝ ነገር፥ በወለጋ የኦሮሞው አባቴ ወንድም፥ የኔ አጎት ስም ቶላ ነበር። ኢትዮጵ እና ልጁ ቶላ ከኦሮሞዎች ጋር አንድ አይነት ግንኙነት እና ትስስር እንዳለው ይህ ክስተት ይጠቁመኛል። በአጋጣሚም እንዳልሆነ ይነግረኛል። ሌላው የሚደንቀኝ ነገር ሁለተኛው የኢትዮጵ ልጅ ተስቢ መባሉና ተስቢያው ኤልያስ የሱ ተወላጅ መሆኑ ነው። በእስራኤል የእስራኤላውያን ነብይ ሆኖ ሲኖር እግዚአብሔር በአጸደ ሥጋ እያለ በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማይ ነጠቀው። ወይም አመጠቀው። ይህ ሞትን ሳያይ በህይወት የሚኖር እጅግ ታላቅ ነቢይ ከአባታችን ከኢትዮጵ የወረደ የኛ ወገን በመሆኑ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ልንኮራ ይገባል። የእግዚአብሔር ሰው ኢዮብም የኛው ወገን ነበር እንጂ እስራኤላዊ አልበረም። የእሱን የህይወት ታሪክ እስራኤላውያን በመፅሃፍ ቅዱሳቸው ውስጥ ከተቱት እንጂ። እሱም ከመልከፀዲቅ ወርዶ በእስራኤል ሲኖር ነበር ሰይጣን በእሱ ላይ ከእግዚአብሔር ተወራርዶ፥ እግዚእብሄርን አስፈቅዶ የተፈታተነው። ኢትዮጵ ዘመዱን ለማስታወስ "ኢትዮጵ" ተብሎ ተጠራ። በልማዳዊ አጠራር "ኢትዮጵ" ከሚለው ቃል ውስጥ "ት" ን ጥለው እና "ጵ" ን "ብ" ብለው "እዮብ" አሉት። መባል የነበረበት ግን "ኢትዮጵ" ነው። ሰይጣን ልጆቹን ገድሎበት እግዚአብሔር እንደገና 10 ወንዶች ልጆች ሰጥቶ ከካሰው በሁዋላ

አስሩም ልጆች ወደ ኢትዮጵያ አፋር ግዛት መጥተው ከኢትዮጵያውያን ዘመዶቻቸው ጋር ተቀላቅለው እዛው መቅረታቸውን ታሪካችን ይዘግባል። እዮብ ዘመዳችን ባይሆን ኖሮ ልጆቹ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ባልኖሩ ነበር። አስሩ የኢትዮጵ ወንዶች ልጆችና ልጆቻቸው እጅግ ብዙ ጎሳዎችና ነገዶች ሆነው የሁሉም ኢትዮጵያውያን አባትና እናት ሆነዋል። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ሕዝቦች ሁሉ አስገኝተው ሁላችንንም አዛምደውናል። ሁላችንም የአንድ አባት እና እናት ልጆች ስለሆንን ደስ እንድንሰኝ ይገባል።





**የ፲፪ ፡ ከዋክብት ፡ የባሕርያቸው ፡ ምሳሌ**



*ከላይ የቀረበውን ምስል በፊርማቸው አረጋግጠው በኢንተርኔት ያደረሱን ዶ/ር አየለ በከሪ ናቸው።*

ደሼት የዞዲያኩን ምስል የመስራት ሀሳብ የመጣለት ከኖኅ ወደ መልከጼዴቅ ከዚያም ወደ ኢትዮጵ በቅብብሎሽ ከመጣልንና ለኔም ከደረሰኝ የዩኒቨርስን አፈጣጠር ከሚተርክ አንድ ጥንታዊ መጽሐፍ

ይወልዳል፡፡ እነሱም ማጂ፣ ጂማ፣ መንዲ እና መደባይ ናቸው፡፡ ማጂ ማራ(አማራ)ን፣ እና ጂማ ወይም ጃማን ይወልዳል፡፡ ጂማ ወይም ጃማዎች በዛሬው ሸዋ ውስጥ በሚገኘው በነገዳቸው ስም በሰየሙት በገርማ ወንዝ ዳር የሰፈሩ ናቸው፡፡ ጂማ ገንቲን፣ አሬቲን እና ማራን ይወልዳል፡፡ ከመደባይ፣ ከጂማና ከመንዲ ኦሮሞ ተገኘ፡፡ መደባዮች ነቢያት እና ቀሳውስት ስለነበሩ እጅግ የሚደመጡና የሚወደሱ ነበሩ፡፡ ከላይ እንዳልኩት ኦሮሞዎች ኦሮሞ ከመባላቸው በፊት መደባይ ነበር የሚባሉት፡፡ ከ2950 ዓመት በፊት በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን እንኳ ኦሮሞዎች መደባይ እየተባሉ ይጠሩ ነበር፡፡

ቆየት ብሎም የ‹ማራ› ልጆች ‹‹ኡ-ማራ›› ወይም ‹‹ሃ-ማራ›› እየተባሉ መጠራት ጀመሩ፡፡ እነዚህ ምእላዳት ‹‹አ›› እና ‹‹ሃ›› እንደጠቋሚ ያገለግላሉ፡፡ በርግጥ የግእዝ ተናጋሪው ኣግኣዚ ነበር ‹‹ሃማራ›› ብሎ የጠራቸው፡፡ ስለዚህ ደሸት የኦሮሞ አባትና የአማራ አያት ነው፡፡ "-ማራ" ለሚለው ቃል የተለያዩ ትርጉሞች ተሰጥተውታል፡፡ ቢሆንም መነሻ ትርጉሙን እጠቅሳለሁ፡፡ "ማራ" ከመነሻው የሱባ ቃል ነው፡፡ በሱባ ቋንቋ "ማ" ማለት "እውነት" ማለት ሲሆን "ራ" ማለት ደግሞ "ብርሃን" ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት "ማራ" ማለት "እውነተኛ ብርሃን" ማለት ነው፡፡ (39)

ከዚህ ቀጥሎ የጎሳን እና ነገድን ልዩነት አብራራለሁ፡፡ ሰዎች ሁለቱን ያምታቱአቸዋል፡፡ ጎሣንና ነገዶችን በዛፍ ስር፤ በግንድ እና ቅርንጫፍ ጋር አመሳስለን መረዳት እንችላለን፡፡ ጎሣ በግንዱ ሲመሰል ነገዶች ደግሞ በግንዱ ላይ እንደበቀሉ ቅርንጫፎች ናቸው፡፡ ስሮች ከምንጭ ጋር ተመሳሳይ ስለሆኑና DNAን ስለሚጠቅሱ ዘር ቢባሉ የተሻለ ነው፡፡ ዛፉ በእድሜ እየገፋ እና እየገዘፈ ሲሄድ ቅርንጫፎቹ እየተባዙ እና እየተስፋፉ ይመጣሉ፡፡ ጎሣም እየገዘፈ ሲመጣ ነገዶቹ እየተባዙ ይሄዳሉ፡፡ ግንዱ እና ቅርንጫፎቹ ካንድ ዘር የበቀሉ በመሆናቸው አንድ ዓይነት ውስጣዊ ባህርያት እየተጋሩ የየራሳቸውን ግላዊ ጠባያትም ያሳያሉ፡፡ የሁለት እና ከዚያም በላይ የሆኑ ጎሣዎች አባላት የሆኑ ግለሰቦችም በጀነቲክ ኢንጂነሪንግ እንደተዳቀሉ ፍራፍሬዎች ወይም አዝእርት ናቸው፡፡ ድቅል አዝእርት ቅልቅል ባሕርያት እንደሚኖራቸው ሁሉ ከተለያዩ ጎሣዎች የሚወለዱ





ልጆችም የሁለቱንም ወላጆቻቸውን ባህርያት ቀላቅለው ይይዛሉ፡፡ ወላጆቻቸውም ድቅሎች ከሆኑም እንዲሁ ነው፡፡

በመጨረሻም እያንዳንዱ ጎሳ ወደ ነገድ እየተከፋፈለ እና እየተሰራጨ በመላ ኢትዮጵያ ከዳር እስከዳር እና አልፎም በተቀረው አፍሪቃ እድሉን ለመሻት ተሰራጨ፡፡ በየሄደበትም ከሌሎች ብሔሮችና ብሔረሰቦች ጋር ባደረገው መስተጋብር እና መቀላቀል የተለያዩ ቋንቋዎችን እና ባሕሎችን ፈጥሯል፡፡ መደባይ፣ ኦሮሞ እና ማጂ መጀመሪያ ቅስናንና በኖኅ በኩል ከኖኅ እና ከማቱሳላ የተላለፉትን የመልከጼዴቅንና የኢትዮጵን ክህነትና የጥንት መጽሐፎችን ወረሱ፡፡ ሆኖም፥ የታሪክ አዋቂ የሆኑት አለቃ አጽመጊዮርጊስ እንደጻፉልን በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን የተወሰኑት መደባዮች/ኦሮሞዎች ወታደሮች ሆኑ፡፡ (ይህም ከ2950 ዓመት በፊት መሆኑ ነው)፡፡

የደሸት ልጆች ከሌሎች ጎሳዎች ጋር ከመቀላቀላቸው የተነሳ በጊዜ ሂደት ውሥጥ አማርኛና ኦሮምኛ የተባሉ የሁለት ቋንቋዎች ተናጋሪዎች የመሆናቸው እውነታ ሁለት የተለያዩ ጎሣዎች እንዲሆኑ አደረጋቸው፡፡ የጋራ ቋንቋ አንድን ጎሣ ከሌላው የሚለይ ዋናው ሁኔታ መሆኑ ሊጤን ይገባል፡፡

ነገዶች የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ ‹clan› ከሚለው ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም አንድ አይደለም፡፡ ‹tribe› ለሚለው አቻ ቃል ላልሆነው "ጎሣ" ለሚለው እሳቤ የጋራ ቋንቋ ዋናው መስፈርት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ዌብስተር የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት "Tribe" የሚለውን ቃል የሚፈታው እንደሚከተለው ነው፤

1. የተለያዩ ቤተሰቦችን፣ ነገዶችን ወይም ትውልዶችን ያቀፈ የማኅበረ-ሰብ ስብስብ፣

2. ተመሳሳይ ጠባይ፣ ሥራ ወይም ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ስብስብ፣

3. የሚዛመዱ እጽዋት ወይም እንስሳት፡፡

በገሃዱ ዓለም "ጎሣ" የሚመሰረተው በጋራ ቋንቋ ላይ ነው፡፡ ሊቀ ጎሩያን በላይ መኮንን "ህያው ልሳነ መዝገበ-ቃላት ግዕዝና

ነዋሪዎች አማሮች በነበሩበት ወቅት ላኮ የወሎ የጥንት መጠሪያ ነበር። ወሎ የሚለው ስያሜ የመጣው በቅርቡ በ16ኛው ክፍለ ዘመን አንድ የኦሮሞ የጦር አበጋዝ ጥካባቢው ከሰፈረና ልጆቹ ባባታቸው ስም "ወሎ" እያሉ አካባቢውን መጥራት ከጀመሩ በኋላ ነው። እዚህ ላይ ቤት ማለት ነገድ እንደ ማለት ነው። የሰባት ቤት ወሎ ሁኔታ ልዩ ነው። ከምንጫቸው ሁሉም ሰባት ቤት ወሎዎች የኦሮሞ ነገዶች ናቸው። "ወረ-" የሚለው ቅድመ-ግንድ አሮምኛ ምዕላድ ይህንን ያረጋግጣል። ያንድ ቤተሰብ ባለንብረትነትን ያመለክታል። መጀመሪያ ላይ ሁሉም ኦሮምኛ ተናጋሪዎች ነበሩ። አሁን ግን ባመዛኙ አማርኛ ተናጋሪዎች ሆነዋል። በዚህም ባደረጉት ያፍ መፍቻ ቋንቋ ለውጥ ኦሮምኛ ያፍ መፍቻ ቋንቋቸው በነበረበት ወቅት የነበሩበትን የመጀመሪያውን የኦሮሞ ጎሣቸውን በአማራ ጎሣ ቀይረዋል። በዘር ግን ከአማራ ጋር ያልተዋለዱቱ አሁንም አሮሞ ናቸው።

እዚህ ላይ ሰባት ቤት አገው እና ሰባት ቤት ጉራጌም መነሳት ይኖርባቸዋል። ሰባት ቤት አገው በተናጠል ሲታዩ እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ልዩ ባሕል ያላቸው ሰባት ነገዶች ናቸው። ጎሣቸው አገው ነው። ሁሉም አገውኛ ቋንቋ ይናገራሉ። ይህ ሁኔታ አንድ ቢያደርጋቸውም የጎጃም አገው እና የሰቆጣ አገው ግን አንድ አይደሉም። እነዚህ ሁለቱ አገዎች የጋራ ቋንቋ እና የጋራ ባህላዊ መገለጫዎች የሏቸውም። እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ቋንቋ እና ባሕል ነው ያላቸው። ይህ የጎጃም አገው እና የሰቆጣ አገው ልዩ መሆን በግልጽ መታወቅ ያለበት ነው።

ሰባት ቤት ጉራጌም ሊነሳ ይገባዋል። ሁኔታው ከሰባት ቤት አገው ጋር ይመሳሰላል። ሰባት ነገዶች አሉት። እነሱም፦ እነሞር፣ አንደገኝ፣ እዣ፣ ቸሃ፣ ጌቶ፣ ጉራ እና ጉምር ናቸው። እያንዳንዱ ቤት ወይም ነገድ የየራሱ ባሕላዊ መገለጫዎች አሉት። የጉራጌ ጎሣ አባላት ናቸው። ምክንያቱም ሁሉም ያፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከመጠነኛ ዘዬ ጋር ጉራጌኛ ነው። የቋንቋ ዘዬ ባንድ ቋንቋ ውስጥ ያለ መጠነኛ ልዩነት ሲሆን በሌሎች ቋንቋዎች ለምሳሌ በኦሮምኛ ውስጥም ይገኛል።





የትግሬ ህዝብን በሚመለከትም እስከ10ኛው ክፍለ-ዘመን ድረስ ልክ እንደ ሰባት ቤት አገው እና ጉራጌ ሰባት ነገዶች ነበሯቸው። እነሱም ትግረ፣ ትግሩ፣ ትግሪ፣ ትግራ፣ ትግሬ፣ ትግር፣ እና ትግሮ ነበሩ። እነዚህ ነገዶች ሁሉም ትግርኛ ይናገሩ ስለነበር የትግሬ ጎሣ አባላት ነበሩ። ዛሬ በትግራይ ውስጥ ሚሙተው ያንድ ቋንቋ፦ የትግርኛ ተናጋሪዎች እና ያንድ ጎሣ፦ የትግራዋይ (የትግሬ) ጎሣ አባላት ወይም ትጋሩ (ትግሬ) ሆነው የባሕል ልዩነታቸው ጠፍቶ የነገድ ልዩነታቸው ከስሟል።

የጎሣ መሥፈርት ሥነ-ሕይወታዊ/ባዮሎጂካል/ ወይም ስነዘራዊ ሳይሆን ሥነ-ልሳናዊ/ቋንቋዊ/ነው። ሰዎችን የሚለየው በዘር ሳይሆን በቋንቋ ነው። ለምሳሌ ኦሮሞዎች የሌላውን ልጅ ወስደው እንደራሳቸው ልጅ አድርገው ማሳደግ ይወዳሉ። ጉዲፈቻ ይባላል። ከአማሮች የሚወለድ አንድ ሕጻን ከኦሮሞዎች ጋር በጉዲፈቻነት ቢያድግ፣ አፉን በኦሮምኛ ቢፈታ እና ከኦሮሞዎች ጋር ቢኖር ልጁ በዘሩ አማራ ቢሆንም በጎሣው ኦሮሞ ነው። ጎሣ የሚወሰነው በአፍ መፍቻ ቋንቋ ነው። በአንድ ቋንቋ አፉን ከፈታ በኋላ ሌሎች ቋንቋዎችን የሚለምድ ሰው ጎሣው የሚወሰነው አፉን በፈታበት ቋንቋ ነው። አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሕጻናት ልሳነ-ክልኤ ይሆናሉ። ለምሳሌ አንድ ሕጻን ወላጆቹ አማራና ኦሮሞ ቢሆኑና በሁለቱም ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ እና በኦሮምኛ አፉን ቢፈታ ልጁ የሁለቱም የአማራና የኦሮሞ ጎሣዎች አባል ነው። በእንግሊዝኛ አፋቸውን የሚፈቱ ጥቁር አፍሪቃውያን ጎሣቸው የቋንቋቸው ጎሣ የነጮቹ ነው። ከሁለት ጎሣዎች የሚወለድ ሕጻን በሁለት ቋንቋዎች አፉን እስከ ፈታ ድረስ የሁለቱም ጎሣዎች አባል ነው። ለምሳሌ ከኦሮሞ አባት እና ከአማራ እናት የሚወለድና በሁለቱም ቋንቋዎች በኦሮምኛም በአማርኛም አፉን የፈታ ልጅ የኦሮሞና የአማራ ጎሣዎች አባል ነው። ሁለቱን ጎሣዎች ለማገናኘት እንደ ድልድይ ሊያገለግል ይችላል። ከሚናገራቸው ቋንቋዎች አንፃር የኦሮሞና የአማራ ጎሣዎች አባል ሲሆን ከደም አንፃር ደግሞ የኦሮሞና የአማራ ዘር ቅልቅል ነው።

ከባሕላዊና ኣዕምሮኣዊ ሁኔታ አንፃር ደግሞ ጉዳዩ ለየት ይላል። አንድ ሰው ቋንቋውን ጠንቅቆ ከሚያውቀው ማኅበረሰብ ጋር

ሙሉ በሙሉ ከተዋሀደ በባሕልም በሥነ-ልቦናም ይመሳሰላል እንጂ የተለየ አይሆንም። የሚለየው በዘር ሐረጉ ብቻ ነው።

የኦሮሞና የአማራ ጉዳይ ግን ፍጹም የተለዩ ነው። አንደኛ ምንጫቸው አንድ ነው፤ ሁለቱም ኦሮሞም አማራም የመነጩት ከአንድ ሰው ነው፡- ከደሸት ወይም ከደሴት። ኦሮሞም አማራም ከ አንድ ዘር ነው የተገኙት፡- እሁንም ከደሸት። ምንም እንኳ በጊዜ ሂደት ከሌሎች ጎሳዎች ጋር ተገናኝተው ሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች ቢናገሩ እና የሁለት ጎሣዎች አባላት ቢሆኑም ቅሉ ገና ሲፈጠሩና በኋላም እርስ በርሳቸው እየተጋቡ እና እየተዋለዱ በደም ተዛምደዋል፤ በባህላዊ፣ በማኅበራዊና በመንፈሳዊ ሕይወት ተዋሕደዋል። እነዚህ ምክንያቶች ኦሮሞዎችንና አማሮችን እርስ በርስ በጥብቅ እንዲቆራኙ፣ እንዲተሳሰሩ፣ እንዲዋሀዱና እንዲዛመዱ አድርገዋቸዋል። ምንም እንኳ በመካከላቸው አልፎ አልፎ ድንገተኛ የድንበር ግጭቶች ቢከሰቱም እርስ በርስ ያደረጉት መዳቀል፣ መቀላቀል፣ መዋሀድና መዛመድ እጅግ ጥልቅ እና ጥብቅ ነው።

የኦሮሞን እና የአማራን ሥነ-ሕይወታዊ ምንጭ ራቅ አድርገን ከዛሬ 4000 ዓመት ጀምሮ ያለውን ብናይ ደግሞ የሁሉም ኢትዮጵያውያን አባት የሆነውን ኢትዮጵን እናገኛለን። አስሩ የኢትዮጵ ልጆች ተራብተው ዛሬ ሁሉንም የኢትዮጵያ ጎሣዎች ለመሆን በቅተዋል። ኢትዮጵ የሳሌም ንጉሥ የመልከጼዴቅ ልጅ ሲሆን መልከጼዴቅም በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት ከኩሽ የተወለደና፣ ከኖኅ፣ አልፎም ከአዳምና ከሄዋን የመጣ ነው።

የአማራ ጎሣ የሚባል አለ ወይ? በሚለው ላይ ክርክር ነበር። በትክክል ለመኖሩ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ። ቀደም ሲል እንዳልኩት ልክ እንደ ኦሮሞዎቹ ዘመዶቻቸው አማሮች ምንጫቸው ጎጃም ነው። እላይ እንዳልኩት፣ የሁለቱም የአማራም የኦሮሞም መገኛቸው የኢትዮጵያ መስራች የኢትዮጵ ቀጥተኛ ተወላጅ የሆነው እና ፈላስፋ የነበረው ደሸት ነው። ደሸት ማጂን፣ ጂማን፣ መደባይን፣ እና መንዲን ወለደ ብለናል። ለመድገም ያህል፣ ማጂ የአማራን ዝርያ ያስገኙትን ማራ/አማራ/ን እና ጃማን ወለደ። ከጋፋት ነባር ነዋሪዎች ጋር መዋጋት ሲሰለቻቸው ከጎጃም ተንቀሳቀሰው ከሌሎች ማሕበረሰቦች ጋር





ተቀላቀሉና የራሳቸውን ቋንቋ አማርኛን ፈጠሩ። ደሸት፣ ልጆቹ እና የአማራ አባት ማራ ይናገሩት የነበረው ፊደሉ በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ሽፋን ላይ የሚታየውን የሱባን ቋንቋ ሳይሆን አይቀርም። የግዕዝና የሱባ መዝገበ ቃላት፥ በሱባ የተከተቡ መጣጥፍ እና የሱባ ፊደላት ተገኝተው በእጃችን ስለአሉ ግን ጥንታውያን አባቶቻችን በሱባ ፊደላት መፃፋቸው እሙን ነው። በኋላ የማራ ልጆች አማርኛን ፈጥረዋል። አጎቶቻቸው መደባይ፣ ጂማ እና መንዲም እንዲሁ አዲስ መሬት እና ግዛት ለመያዝ ከጎጃም እየራቁ ሄዱ እና ከሌሎች ኢትዮጵያውያን እና ከምሥራቅ አፍሪካ ከ አፍሪካ ቀንድ ህዝቦች ጋር በፈጠሩት መስተጋብር የተነሳ ዛሬ ኦሮምኛ እያልን የምንጠራውን የራሳቸውን አዲስ ቋንቋ ፈጠሩ። አማራ እና ኦሮሞ በፈጠሯቸው ሁለቱ ቋንቋዎቻቸው ሳቢያ ሁለት የተለያዩ ጎሣዎች ሆኑ። ቋንቋም የጎሣ መስፈርት ሆነና አማርኛ ወይም ኦሮምኛ የሚናገር ማንኛውም ሰው ከቋንቋው አንፃር አማራ ወይም ኦሮሞ ይባል ጀመር። ከሥነ-ሕይወት ወይም ከስነ-ዘር አንፃር ግን ከአንድ ምንጭ የመጡ በመሆናቸው አማራም ኦሮሞም ሥረ-መሠረታቸው አንድ ነው። ማንም ልጅ በመወለድ ወይም በጉዲፈቻ በማደግ አማራ ወይም ኦሮሞ መሆን ይችላል። ቋንቋ የጎሣ መለያ መሥፈርት ነውና። ሁለቱም፣ የአማራም የኦሮሞም ጎሳዎች በዚህ መልክ ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥረው ይኸው እስከዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ይኖራሉ። የአመጣጣቸው እና አኗኗራቸው ሁኔታ ተጨባጭ እና ጠንካራ እውነታ ነው።

ግለሰቦች በተፈጥሮአዊ መንገድ ቋንቋን ሲለምዱ ለሚለምዱት ቋንቋ ባሕል፣ ልምድ፣ ሃይማኖት እና ሥነ-ልቦና እና ያኗኗር ይትባሕሎች ይገዛሉ። ይማረካሉም። (ይጋለጣሉ።) በዚህ ምክንያት ከቋንቋው ባለቤቶች ጋር ራሳቸውን ያመሳስላሉ፣ ያዋህዳሉ። ሆኖም ከኗሪው ጋር እየተጋቡ ካልተቀላቀሉ በስተቀር በደም ራሳቸውን ነው የሚሆኑት። ከተጋቡና ከተዋለዱ ግን ልጆቻቸው እና 2ኛ፣ 3ኛ 4ኛ ትውልድ ዝርያዎቻቸው የተቀላቀለ ጎሣ አባላት ይሆናሉ።

የትግራይ ራያ ኦሮሞዎች ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው። በደም ኦሮሞዎች ሲሆኑ በጎሣ ግን ያፍ መፍቻ ቋንቋቸው ትግርኛ በመሆኑ የትግራዋይ ጎሣ አባላት ሆነዋል። ጥቂቶች ግን ልሳነ-ክልሌ

ሆነው ትግርኛም ኦሮምኛም ይናገራሉ:: ጎሣ የሚወሰነው አፍ በፈቱበት ቋንቋ በመሆኑ እነዚህ ልሳነ ክልኤ የሆኑ ግለሰቦች በጎሣ ረገድ የትግሬም የኦሮሞም የሁለቱ ጎሣዎች አባላት ናቸው:: ሆኖም በአካባቢው የበላይነትን የያዘው ቋንቋ ባሕሉን፣ ወጉን፣ ሃይማኖቱን፣ ሥነ-ልቦናውን እና የአኗኗር ይትባሕሉን ስለሚጭንባቸው ጎሣቸው የዚሁ ቋንቋ ጎሣ መሆኑ አይቀርም::

ጠቅለል ለማድረግ፣ ዘር፣ ጎሣ እና ነገድ ስነ-ሕወታዊ፣ ስነ-ልሳናዊ እና ባሕላዊ ዳራ ያላቸው አምደ-ቃላት ናቸው:: ጎሣቸውን እና ነገዳቸውን መወሰን ያለባቸውም ግለ-ሰቦች ራሳቸው ናቸው:: ለምሳሌ አንድ ሰው ኦሮምኛ አቀላጥፎ እየተናገረ ያፍ መፍቻው ግን አማርኛ ቢሆን ጎሣውም አማራ ነው የሚሆነው:: ሆኖም የኦሮሞ ጎሣ አባል መሆን ቢፈልግ የሚከለክለው ነገር የለም:: የሚፈልገውን መሆን ይችላል:: ይህ የማይነካበት ሰብአዊ መብቱ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ የማንኛውም ጎሣ እና ነገድ አባል ተደርገው መቆጠር የማይፈልጉ ግለሰቦች ይኖራሉ:: ኢትዮጵያዊ ወይም ሰብአዊ ተደርገው መታየት ብቻ ይሆናል የሚፈልጉት:: መብታቸው ነው:: የድሬዳዋ ልጆች ለዚህ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው:: ልሳነ-ብዙ፣ ባሕለ-ብዙ፣ አፍቃሬ-ሰብዕ ናቸው:: አንድ የድሬዳዋ ሰው ኦሮምኛ፣ አማርኛ፣ ሶማልኛ አልፎም አረብኛ አቀላጥፎ ሲናገር መስማት የተለመደ ነገር ነው:: ባመዛኙ ጎሣቸው የሚወሰንበት አንድ ያፍ መፍቻ ቋንቋ ይኖራቸዋል:: ወላጆቻቸው ምንም ዓይነት ቋንቋ ይናገሩ፣ የማንኛውም ጎሣ አባላት ይሁኑ፣ የድሬ ልጆች ልሳነ-ብዙ ናቸው:: ይሁን እንጂ ቋንቋ-ተኮሮች አይደሉም:: ለድሬዎች ቋንቋ መግባቢያ እንጂ መለያያ አይደለም:: በቋንቋ፣ በባሕል እና በስነ-ልቦና ተቀላቅለው እና ተዋህደው የድሬ ልጆች አንድ ሆነዋል:: የሐረር ልጆችም እንዲሁ ናቸው:: የሚያስተሳስራቸው ኢትዮጵያዊነት ነው:: ድሬ እና ሐረር ጎሣ ቀልጦ የሚዋሃድባቸው ለመላዋ ኢትዮጵያ አርኣያ የሆኑ የአንድነት እና የፍቅር ማሰሮዎች ናቸው::

"ብሔር" የሚለውስ እንዴት ይታያል? የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ አራማጆች "ብሔር" የሚለውን ቃል አላግባብ ተጠቅመውበታል:: ኋላቀርነትን ያንጸባርቃል በሚል ከጎሣ ጋር አምታተውታል:: ስህተት ነበር:: ብሔር ጎሣን አይተካም:: ቦታን ነው





የሚያመለክተው:: ብዙውን ጊዜ ትልቅ ወይም ትንሽ አካባቢን ይጠቁማል:: ለምሳሌ ቡልጋ፣ ሸንኮራ፣ ምንጃር ተጉለት፣ ዳሞት፣ ዘጌ፣ ጨልያ፣ ሰላሌ፣ ተምቤን፣ እና ጨርጨር የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል:: ለዚህ ነው በኔ ዕድሜ ከነበረው ከዚያ ተራማጅ ትውልድ በተቃራኒው የነበሩት በሳል ሰዎች የትውልድ ቦታቸውን ሲጠቅሱ "ዘብሔረ ቡልጋ፣ ዘብሔረ ዘጌ፣ ዘብሔረ ተምቤን ወዘተ" ይሉ የነበረው:: በዚህ ረገድ "ዘብሔረ ኦሮሞ፣ ዘብሔረ አማራ" ማለት ትክክል አይደለም:: ግልጽ ለመሆን "የኦሮሞ ጎሣ፣ የአማራ ጎሣ" ነው ማለት ያለብን::

ብሄሮችና ብሄረሰቦች እንዴት ይታያሉ? ብሄርና ብሄረሰብ የሚሉት ፅንሰ ሃሳቦች ወደ ኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ የገቡት ተማሪዎቹ ማርክሲዝም-ሌኒኒዝም-እስታሊኒዝም-ትሮትስኪዝም በሚያጠኑበት ወቅት ነበር:: ከእነዚህ ከአራቱ ኢዝሞች ባለቤቶች ዋናው ኮምዩኒስቱ የሩስያው ጆሴፍ እስታሊን የዛሬ መቶ ዓመት ገደማ በሶቭየት ሕብረት ምስረታ ወቅት ያቀነቀነው ሃሳብ ነበር::

በዚያን ወቅት ስታሊን ‹‹የብሄሮች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል›› የሚለውን ጨመረበት እና ፕሮፖጋንዳውን ሠራ:: ሆኖም አንዳንድ ብሔሮች ከሕብረቱ መውጣት(ከሶቭየት ሕብረት መገንጠል) ሲፈልጉ ግን በወታደር ኃይል አመቃቸው:: ስታሊን ስለ ብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ያቀረበውን ሃተታ የመሰረተው፣ የፖሊሽዋ ሲቪል ዴሞክራት ሮዛ ሉክዘምበርግ (1909) በከተበችው እና ቭላዲሚር ኢሊች ሌኒን በፃፈው ጽሁፎች ላይ ነበር::

ስታሊን ጽሁፉን መጀመርያ በ1913 ሲያሳትም ብሔረሰቦች የሚለውን ፅንሰሃሳብ ‹‹አንድ ጂኦግራፊያዊ አካባቢ እና አንድ ዓይነት ቋንቋ የሚጋሩ፣ ተመሳሳይ ስነ-ልቦናዊ አመለካከት እና አንድ አይነት ባሕል ያላቸው ሕዝቦች›› ብሎ ነበር የፈታው:: እነዚህ አራቱ ነጥቦች የስታሊን አበይት መስፈርቶች ነበሩ:: ይሁንና የስታሊን ፍቺ ሁሉአቀፍ አልነበረም:: በአንዳንድ የሶቭየት ሕብረት ክልሎች እና በምስራቅ አውሮፓ ብቻ ነበር የተሰራበት:: ለምሳሌ በፈረንሣይ እና በእንግሊዝ ሊተገበር አይችልም ነበር:: (አልተሠራበትም::) በኢትዮጵያም ባጠቃላይ የሚሠራ አይደለም:: ሁሉም የስታሊን

የኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥት የመጨረሻዋ ገዢ ንግሥት ሳባ ነች። እኛ ኢትዮጵያውያን የሱባን ቋንቋ እና ለዚህ መጽሐፍ የሽፋን አርማ ዕንዲሆን የተደረገውን የሱባን ፊደል ያገኘነው በዚህ ሁኔታ ነው። የባቢሎን ግንብ ታሪክን ተረት ነው ብለን ብንተወው እንኳ የሱባን ቋንቋ ሕልውና ልንክደው አንችልም። ምክንያቱም ፊደሉ፥ መጣጥፎቹ እና መዝገበ ቃላቱ በእጃችን ይገኛሉና። ስለዚሕ ሥነ-ልሳናዊ በሆነው "ጎሣ" በሚለው ቃል እና ሥነ-ሕይወታዊ በሆነው "ዘር" በሚለው ቃል መካከል ልዩነት እንዳለ መገንዘብ ይኖርብናል። ምንም እንኳ የሰው ዘር በሙሉ ምንጩ አንድ ቢሆንም በሂደት እየተራባ በተለያዩ አካባቢዎች በመኖሩ የተነሳ የተለያዩ ቋንቋዎችን መናገር ሲጀምር የተለያዩ ጎሣዎች ባለቤቶች ሆኗል። በሱ ስርም አያሌ ነገዶችን አፍርቶአል።.

የዝርያ ብዙሃንነትን በተመለከተ "ኅብረ-ብሔራት" ማለት ተስማሚነት አለው። ኢትዮጵያ የበርካታ ዝርያዎች ሀገር መሆኗን ከማመልከቱም በላይ ዝርያዎቹ ኅብረት ፈጥረው በሰላም አብረው መኖራቸውንም ያመለክታል።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1000 ዓ.ዓ ገደማ የወንድማማቾቹ የጀማ እና የማራ (አማራ) ልጆች ከነባር የጋፋት ሕዝቦች ጋር መዋጋት ሰለቻቸውና ወደ ምስራቅ አቀኑ። በዛም የጀማ ልጆች ዛሬ ሸዋ በሚባልው ውስጥ አንድ ወንዝ አገኙና ለአባታቸው መታሰቢያ እንዲሆን ጀማ ብለው ጠሩት (አሁን ዠማ ይባላል)። ማራ (አማራ) ዎች የሰፈሩባቸውን ቦታዎች ሸበል በረንታ፣ ዑሬራ፣ ግራርጌ፣ አዲስጌ፣ መራ (አሁን መራ-ቤቴ)፣ አማራ ሳይንት፣ ሊኮ (አሁን ወሎ)፣ ካቢ እና ገነቴ (አሁን የጁ) እያሉ ጠሩአቸው። (40)

ጀማዎች የግራኝን ወረራ አጥብቀው በመቃወማቸው በአህመድ ግራኝ ክፉኛ ነው የተጎዱት። ግራኝ ለደጋፊዎቹ አረቦች (ኢትዮጵያን የማጥፋት ዓላማ ይዘው ላስታጠቁትና ከጎኑም ተሰልፈው ለተዋጉለት አረቦች) በባርነት ሸጣቸው። ሆኖም የተ ጫኑባቸውን መርከቦች እስፔናውያን ማረኩዋቸውና ዛሬ በስማቸው በጀማ ጃማካ ወይም ጃማይካ በተባለው አገር በባርነት ኖሩ። (41) አገሪትዋም በስማቸው ትጠራ ጀመር። ጀማዎች፥ ማለትም የአሁኖቹ ጃማይካዎች ኢትዮጵያን ከልክ በላይ የሚያፈቅሩትና ራሳቸውንም እንደ





ኢትዮጵያውያን የሚቆጥሩት ያለምክንያት አይደለም። ምንም እንኳዋን የታላለቆቹ የኢትዮጵ እና የደሸት ዘር መሆናቸውን አእምሮአቸው ቢረሳውም የደማቸው ነፍስ ስለአስታወሰው ኢትዮጵያውያን ነን ብለው ግዕዝን እስከመማር እና የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርቲያን አባላት እስከ መሆን በቅተዋል። በተጨማሪም አረንጉዋዴ፣ ቢጫ እና ቀይ የሆነችውን ማንነታችንን ያልተረዳን ሰዎች የምንንቃትን ስንድቅአላማችንንም የራሳቸው አርማ አድርገው በኩራት ያውለበልባሉ። ከእነማይና ዘረ-ደሸቶች በተጨማሪ፥ የአባታቸውን ስም አሁን ድረስ ጠብቀው ያቆዩ ጥቂት የአማራና የመደባይ የሥጋ ዘመዶች በጎጃም ውስጥ አሉ። የቀሩት ግማሾቹ በስተ ሰሜን ዛሬ ጎንደር እና ትግራይ ወደ ሚባሉት ክልሎች፣ ግማሾቹ በስተ ደቡብ ወደ ወለጋ እና እናሪያ (አሁን ሊሙ) ወደሚባሉት ቦታዎች ሄደዋል። ቀስ በቀስ ቁጥራቸው ሲበረክት ደግሞ ወደ ባሊ (አሁን ባሌ)፣ ሶማሊያ፣ ኬንያ (በቦረና በኩል)፣ ሩዋንዳ (የሩዋንዳ ቱቱሲዎች ኦሮሞ መሆናቸውን ያምናሉ፤ ኢትዮጵያዊ መልክም ይታይባቸዋል፤ ሁቱዎች ሊያጠፉዋቸው ሲፎክሩ ወደ ሃገራችሁ ኢትዮጵያ ተመለሱ እያሉ ነበር።) አልፎም እስከ ኒጀር እና ማደጋስካር ድረስ ዘልቀዋል። ማደጋስካር ውስጥ በኦሮምኛ ቋንቋ የሚናገሩ ያገሪቱ ዜጎች እንደነበሩ እዚያ ይኖር የነበረ አንድ ጓደኛዬ ከ45 ዓመት በፊት አጫውቶኛል። የማሊ ህዝብም የኦሮሞ ተወላጅ ነው። በኦሮምኛ ‹‹ማሊ› ማለት ‹‹ምንድነው?›› ማለት ነው። ማሊ የሚኖር ሌላ ኢትዮጵያዊ ጓደኛዬም ከማሊያውያን ጋር በኦሮምኛ ቋንቋ ይግባባ ነበር።

አፍሪቃን ሲያካልሉ ቆይተው በተለያዩ ጊዜያት ወደ አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሱ ኦሮሞዎች ብዙ ናቸው።

ኢትዮጵያውያን የታሪክ አዋቂዎችን ለምሳሌ አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስን፣ አለቃ ታዬንና አልፎም አቶ ተክለጻድቅ መኩሪያን ኦሮሞዎች በሞዛምቢክ፣ ማደጋስካርና ኬንያ በኩል ከእስያ መጡ ለማለት ያነሳሳቸው ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል።

በዛሬዎቹ ጎጃም፣ ወለጋ እና እናርያ የቀሩ በርካታ መደባዮች የጥንት አባቶቻቸውን የመልከጼዴቅን የንጉሦች ንጉሥ እና የሳሌም (የኢየሩሳሌም) ከፍተኛው ካህንን፣ የኢትዮጵንና የዝርያውን የደሸትን

(የኦሮሞና የአማራ አባት)ን መንፈሳዊና አእምሮአዊ ባሕል ቀዳማዊ ምኒልክ የሃይማኖት ጭፍጨፋ እስከ አካሄደባቸው ጊዜ ድረስ ሳይለቁ ጠብቀው በመያዝ ቀሳውስት፣ ፈላስፎች እና ሊቃውንት እየሆኑ ነበር።

ቀዳማዊ ምኒልክ መደባዮችን በከፊል የጨፈጨፋቸው ኢትዮጵያን ወደ አይሁድ ምድርነት ለመቀየር የነበረውን መሰሪ እቅድ በመቃወማቸው ነበር። በሚያሳዝን ሁኔታ እነሱንና መጽሐፎቻቸውን አጠፋ። ከአንድ ሺ ዓመት በሁዋላ እየሱስ ሲወለድ ወደ ኢየሩሳሌም እየመራ የሚወስዳቸው ኮከብ ምስል ያለበትን አርማቸውንና የጥበበ-ብልሃት ምልክታቸውን ለውጦ በዙፋኑ ላይ የይሁዳ አንበሳን ምስል አደረገ። አንዳንድ መደባዮች ጭፍጨፋውን በመፍራት በጥንቱ የሱባ ቋንቋ የተጻፉ መጽሓፎቻቸውን ደበቁ ወይም ለቀዳማዊ ምኒልክ አስረከቡ፣ እና እሱም የወረሳቸውንና በጁ የገቡትን መጽሓፎች በሙሉ አቃጠላቸው። በዚህ ያዘነ አንድ መደባይ መጽሐፉን ለንጉሡ አላስረክብም ብሎ ለላሙ አብልቷታል። ጥቂት ቆየት ብሎ ላሟን ሲያርዳት የተወሰነ ጽሁፍ በስጋዋ ላይ ማግኘቱ ተዘግቧል። እሱና ልጆቹ አንዳንዶቹን ፊደሎች አገጣጥመው ለመተርጎምና ስለታሪካቸው ፍንጭ ለማግኘት በመሞከራቸው መደባይን "ኦሮሞ" ብሎ መጥራት ተጀመረ። በሱባ ቋንቋ ‹‹ኦሮሞ›› ማለት ‹‹እውቀት ገላጭ፣ ተርጓሚ፣ በሰው ልብ ውስጥ ያለውን የሚያነብ ብልኅ ሰው›› ማለት ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ‹‹መደባይ›› የሚለው መጠሪያ እየቀረና ‹‹ኦሮሞ›› የሚለው እየጎላና እንደ ሰደድ እሳት እየተዛመተ መጣ።

የቀዳማዊ ምኒልክን መንግሥት እንዲያገለግሉና የአጋዚን ባህል እንዲላበሱ የተገደዱ መደባዮች (አርባ ሺ የጋዛ ሰዎች፣ ሃያ ስምንት ሺዎቹ ጄቡሳይቶች/ኢያቡሳውያን/፣ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ከእስራኤል መጥተው የነበሩ) የታላላቅ አባቶቻቸውን የኢትዮጵንና የደሸትን የሱባ ቋንቋ እርግፍ አድርገው ትተው የግዕዝ ተናጋሪዎች ሆኑ። እነዚህ አጋዚያን አቡሳውያን ይባላሉ። ራሳቸውን ያዳቀሉ ነገዶች ናቸው። ሐበሻ ወይም አበሻ የሚለው ቃል ‹‹ድብልቅ›› ወይም ‹‹ክልስ›› አለዛም ‹‹አበሳ›› የሚል ክብር ነኪ ፍቺ አለው። የተከበረውን ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን ከእስራኤል ክልሶች ጋር ማምታታት ካላስፈለገ በስተቀር የአማራ ብዙኃን አበሾች አይደሉም። ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵ ልጆች ናቸው። የኢትዮጵ ልጆች ስለሁኑም





ኢትዮጵያውያን ናቸው። ኢትዮጵያውያን ተብለው ነው መጠራት ያለባቸው። ቀዳማዊ ምኒልክ አግኣዚዎችን ሥልጣን ላይ አውጥቶ መንግሥታቸውን፣ ቀደም ሲል እንደገለጽኩት፣ የሰለሞን ሥርወ-መንግሥት የተባለውን በኢትዮጵያ መሰረተ።

በዘመነ-መሳፍንት ማብቂያ ላይ የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ጎንደርን ማዕከል አድርጎ ራሱን ‹‹የጋላ እና የአቢሲኒያ ንጉሥ›› እያለ ይጠራ ከነበረው መንግሥት አውቅና ውጪ የራሳቸውን ግዛት መሰረቱ። ልጆቻቸው ንጉሥ ኃይለመለኮት እና ዳግማዊ ምኒልክም እንደዚያው በማድረግ ቀጠሉ። እነዚህ ሶስቱም ራሳቸውን ከአግኣዚ (አበሻ፤ አቢሲኒያ) ጋር አገናኝተው የሰለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት ይጠቅሱ ጀመር።

አፄ ምኒልክ ከሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት እና ከኣግኣዚ ጋር አለኝ ለሚሉት ትስስር እውቅና ሲሰጡ ‹‹ንጉሠ-ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ስዩመ እግዚአብሔር ድል አድራጊው የይሁዳ አንበሳ›› ብለው ራሳቸውን ጠሩ። ምንም እንኳ እነዚህ ሶስቱ ነገሥታት ከአግአዚ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ብቻ ቢጠቅሱም የኦሮሞ ሥረ-መሠረታቸው የሚካድ አይደለም። የይኩኖ አምላክ (ተስፋ ኢየሱስ) የልጅ ልጆች፣የጊፍቲ መንዲያ እና የአቤቶ ያቆብ ልጅ ተወላጆች ናቸው። አቤቶ ያቆብ የአፄ ልብነ-ድንግል ልጅ ነው። እናቱ እሌኒ ሞገሳ 3ኛ፤ የደዋሮው የቱሉ በዴሳ ሴት ልጅ (ያን ጊዜ ሐረርጌ የደዋሮ አካል ነበር) ናት። በዚህም አጼ ምኒልክ ቢቀበሉትም ባይቀበሉትም፤ በዛም አነሰም፥ በደም ስራቸው ውስጥ የኦሮሞ ደም ነበር።

የህያው እግዚአብሔር ሊቀካህናት የሳሌሙ ንጉሥና የካህኑ የኢትዮጵ ዝርያ የነበረው ትልቁ የኦሮሞ ሕዝብ ከመነሻ ቦታው እየተለየ ሲበታተን፣ ቀሳውስቱም በአይሁድ እምነት ሲዋጡ ወይም ከጥንት የሃይማኖት፣ የታሪክና የፍልስፍና መጽሐፎቻቸው ጋር ጨርሰው ሲጠፉ፣ ውጤቱ በርካታ አማልክትንና መናፍስትን ለምሳሌ እንደ ውቃቢ፣ ዛር፣ አቴቴ፣ ኢሬቻና የመሳሰሉትን ማምለክ ሆነ። እንደዚህ ዓይነቱን አምልኮ የጥንት አባቶቻቸው እነ መልከጸዴቅ፣ ኢትዮጵና ደሸት እንደ ጣኦት አምልኮ ነበር የሚቆጥሩት። ከጊዜ በኋላ አማሮች ዘመዶቻቸውም ዱካቸውን ተከተሉና ብዙዎቹ በክርስትና

እምነት ሽፋን እነዚህን የኦሮሞ መናፍስት አምላኪና በአሎቻቸውን አክባሪ ሆኑ። ይህን ጉዳይ ‹‹ለኢትዮጵያ ስልጣኔ የኦሮሞ አስተዋጽኦ›› በሚለው መጣጥፌ እንደ ዘረዘርኩት እንባቢዬ ያስታውሳል።

‹‹ሱባ፤ ልሳነ-ሰብ (ሰብአዊ ቋንቋ) ቀዳማዊ ምኒልክ ሥልጣን እስከያዘበት ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ ነበር። ይኸውም ነገሥታቱ ትዕዛዞቻቸውንና መመሪያዎቻቸውን የሚጽፉበት እና የሚያውጁበት የመንግሥት የሥራ ቋንቋ ነበር።››(42) ቀደም ሲል እንደተመለከተው በርካታ የመደባይ/ኦሮሞ/ ተወላጆች የጥንት አባቶቻቸውን የመልከጼዴቅን፣ የኢትዮጵን፣ የነቢዩ ደሸትንና እብራዊውን ሙሴን በእግዚአብሔር መንገድ (እንዲሄድ) ለ40 ዓመት ያሰለጠነውን የየትሮአብን ሃይማኖት እርግፍ አድርገው ትተው በሙሴ የተመሰረተውን የአይሁድን እምነት ተቀበሉ። በዚህም የአግአዚያንን አክብሮት አግኝተው ደማቸው ከሰለሞናዊው ደም ጋር ይቀላቀል ዘንድ በጋብቻ መዛመድ ጀመሩ። አማሮች ዘመዶቻቸው ግን ከዚህ ይልቅ የየግዛታቸው ንጉሶች፣ ወታደሮች፣ አገረ-ገዢዎች፤ ህዝብ አስተዳዳሪዎች፥ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች፣ ቀሳውስት እና ሊቃውንት መሆንን መረጡ። የቅርቡን ብናወሳ እንኳዋን በሰለሞናዊው ስርወ-መንግስት ሥልጣን ላይ ከወጡ የኦሮሞ ዝርያዎች መካከል፥ ከዚህ ቀደም ስሙ የተወሳው ይኩኖ አምላክ ይገኝበታል። የጊፍቲ መንዲያ ልጅ ይኩኖ አምላክ በዛጉዬ ሥርወ-መንግስት ለሦስት መቶ አመታት ተቋርጦ የነበረውን የሰለሞንን ሥርወ-መንግስት በ13ኛው ክፍለ-ዘመን እንደገና ያስቀጠለ ንጉሠ-ነገሥት መሆኑ አይዘነጋም።

ጎሳ እና ዘር የተሰኙትን ፅንሰ-ሃሳቦች፥ እዚህ ላይ ከይኩኖ አምላክ ጋር ብናዛምዳቸው፥ አባቱ እድምአሰግድ ከአማሮች ጋር ተጉለት ስለኖረ የመጀመሪያ ቋንቋው አማርኛ ከሆነ ጎሣው አማራ ነበር። እናቶቻቸው ኦሮሞ የሆኑ የይኩኖ አምላክ ተወላጆች በልጅነታቸው መጀመሪያ በየትኛው ቋንቋ እንደተናገሩ አላውቅም፤ መጀመሪያ የተናገሩት ኦሮምኛ ከሆነ ጎሣቸው ኦሮሞ ነበር። መጀመሪያ የተናገሩት ኦሮምኛ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ፤ ምክንያቱም የሚያድጉት ከእናቶቻቸው ጋር ስለሆነ። የመጀመሪያ ቋንቋቸው አማርኛ ከሆነ ግን የጎሣ መስፈርት ቋንቋ ስለሆነ ጎሣቸው አማራ ነው የሚሆነው። ለንግሥና ግን መስፈርቱ ቋንቋ ሳይሆን የዘር ሀረግ ነው።





አንድ ሰው የንጉሣዊ ደም ያለው መሆን አለመሆኑን ማወቅ ሲፈልጉ የሚጠይቁት "ምን ቋንቋ ትናገራለህ?" ብለው ሳይሆን "የማን ዘር ነህ?" ብለው ነበር። የኦሮሞ ነገሥታት በአባት በኩል በዘራቸው የሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት አባላት ናቸው። የንጉሣዊ አባልነትን ለማረጋገጥ ቋንቋ መስፈርት አይደለም። እነዚህ መኳንንቶች የይሁዳ ነገድ፣ ዘረ-እስራኤል ነን ለማለት ከጎሣ ይልቅ በነገድ ላይ ያተኩሩና ርቀው ይቆጥራሉ። ነገዶቻቸው ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን እናውቃለን። በዙፋኑ ላይ መቀመጥ የሚችሉት የሰለሞን ዘር የሆኑ ናቸው ብለው በሚያምኑት ኢትዮጵያውያን ዘንድ ህጋዊነት እና ተቀባይነት ለማግኘት አልጋው ይገባናል የሚሉ መኳንንቶች የይሁዳ ነገድ፣ ዘረ-እስራኤል መሆናቸውን ዘራቸውን ቆጥረው ማስረገጥ ይጠበቅባቸው ነበር። የሆነ ሆኖ እናቶቻቸው አሮሞ የሆኑቱ፥ በእናታቸው በኩል ዘረ-ኦሮሞ መሆናቸው በምንም ሂሳብ የማይካድ ሃቅ ነው። እፍ የፈቱት በናታቸው ቋዋንቋዋ ከሆነ ደግሞ በጎሳም በዘርም አሮሞነታቸው ያመዝናል።

የይኩኖ አምላክ የልጅ ልጅ አጼ አምደ ጽዮንም እንዲሁ ኦሮሞዋን ጃን ሞገሳ ዳዲን አግብቷል። የሱም የልጅ-ልጅ-ልጅ አጼ በዕደ ማርያም የሃረርዋን ደዋሮ ሙስሊም የገራድ መሐመድ በንቲን ሴት ልጅ አግብቶ፤ ክርስትና አስነስቶና ዳገማዊት ጃን ክብራ እሌኒ አሰኝቶ ንግሥት አድርጎአታል። ልጁ አጼ ናኦድም የሐረር ኦሮሞ የሆነችውን ናኦድ ሞገሳ እሌኒ 3ኛ ብሎ የጠራትን የቱሉ በዴሳን ልጅ አግብቷል።

ልጁ አጼ ልብነ ድንግል አባቱ ሲያርፍ ትንሽ ልጅ በነበረበት ወቅት ኦሮሞዋ አያቱ ንግስት ጃን ክብራ እሌኒ 2ኛ እና የቱሉ በዴሳ ልጅ የሆነችው ወላጅ እናቱ እሌኒ ናኦድ ሞገሳ 3ኛ ከቱሉ በዴሳ ጋር ሆነው ኢትዮጵያን ገዝተዋል። ብልህዋና ተከባሪዋ የኦሮሞ ንግሥት እሌኒ ጃን ክብራ 2ኛ ከፖርቱጋል ጋር ለተመሰረተው ፖለቲካዊና ወታደራዊ ግንኙነት አጋዥ ኃይል ነበረች። የእሌኒ ናኦድ ሞገሳ ወንድም፣ ዶሪ ቱሉ በዴሳ ንጉሠ ባህረ-ነጋሽ ተብሎ ነግሦ የቀይ ባሕር እና የኤርትራ ገዢ ሆኗል። ሲሞት ልጁ ባሕረ-ነጋሽ ይሥሃቅ ዶሪ ቱሉ በዴሳ በእግሩ ተተክቶ ነግሷል። በዚህም የኦሮሞ ንግሥቶች ልጆች በተዋረድ የኦሮሞ ዝርያ ነገሥታት ሆነዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ታዋቂው የታሪክ ፀሐፊ ተክለ-ጻዲቅ መኩሪያ (የኢትዮጵያ ታሪክ) *‹‹ንግሥት ናኦድ ምገሳ እሌኒ ሐድያ ናት››* ብለው የጻፉትን እዚህ ላይ ማንሳት ይኖርብኛል፡፡(43) ‹‹ቱሉ በዴሳ›› የሚለው ያባትዋ ስም ኦሮሞ መሆንዋን ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪ ሐረር ውስጥ እስከ ዛሬ ድረስ ‹‹በዴሳ›› እየተባለ የሚጠራ ቦታ አለ፡፡ የቱሉ አባት አቶ በዴሳ ባላባት ሆኖ እሱን ለማታወስ ከጊዜ በሁዋላ በሱ ስም ቦታው በዴሳ ተብሎ ይሆናል፡፡ ወይም እሱ ከመወለዱ በፊት በዴሳ ተብሎ በዴሳን ለመዘከር የተሰየመ ነው፡፡ ሐድያ ውስጥ ግን እኔ እስከማውቀው ድረስ ‹‹በዴሳ›› የሚባል ቦታ የለም፡፡

ኦሮሞው በኢትዮጵያ በቀል ሕዝብ ሆኖ፤ በአግአዚ የሰለሞናዊው ስርወ-መንግሥት ንጉሳውያን ቤተሰብ አባላት ያን ያህል ሲከበርና በጋብቻም ተቀላቅሎአቸው ሳለ ለምን ተገለለ? ለምንስ “አረመኔ” እና “ያልተገረዘ” እየተባለ ተጠራ? ለምን እንደ ስደተኛና ወራሪስ ተቆጠረ? ሁለት ምክንያቶች አሉ፦ መደባይ፣ የኦሮሞ ግንዱ ከሦስት ሺ ዓመት በፊት “ኦሮሞ” የሚል አዲስ ስያሜ ተሰጠውና መደባይ የሚለው ጨርሶ ተረሳ፡፡ ጥቂት መደባዮች ብቻ የቆየውን መጠሪያቸውን/መደባይ የሚለውን/ እነደያዙ መኖር እና መበልጸጋቸውን ቀጠሉ፡፡ አሁንም ድረስ በዚሁ ስም መደባይ ዛና እና መደባይ እየተባሉ በትግራይ ውስጥ እና በወንበርማ አካባቢ በጎንደር አሉ፡፡ አዲሱን መጠሪያ (ኦሮሞ የሚለውን) የያዙት ግን መደበኛውን መኖሪያቸውን እየተዉ በኢትዮጵያ ውስጥና በውጭ አገሮች አዳዲስ መኖሪያ ፍለጋ ተበተኑ፡፡ ያገራቸውን ድንበር አቋርጠው ሄደው ብዙ ዓመታት ያስቆጠሩ ኦሮሞዎች በኢትዮጵያውያን ዘመዶቻቸው ፈጽሞ ተረሱ፡፡ ከብዙ ዓመታት መለየት በሁዋላ ተመልሰው ሲመጡ እንደ ወራሪ ተቆጠሩ፡፡ ከኢትዮጵያ ሳይወጡ የኖሩት ኦሮሞዎች በሙስሊሙ አህመድ ግራኝ እና እንደገና በተመሰረተው ሰለሞናዊ ስርወ-መንግሥት ስር በነገሡ (እንደ እውነታው ግን ራሳቸውም ኦሮሞዎች በነበሩ) ክርስቲያናዊ ነገሥታት መካከል ጦርነት ሲካሄድ አጋጣሚውን ተጠቅመው አዳዲስ ለም መሬቶችን ተቆጣጠሩ፡፡ በዚህም አህመድ ግራኝን ባለመውጋታቸውና ገለልተኛ በመሆናቸው እንደ ጥቅመኛና ከሃዲ ተቆጠሩ፡፡





እንደ እውነቱ ከሆነ ለኦሮሞ ንጉሣዉያን ቤተሰብ ቅርበት የነበራቸው የኦሮሞ ጎሣ መሪዎች ዝና የወደቀበት ዋናው ምክንያት አንዳንዶቹ ለአህመድ ግራኝ በመወገናቸው ነው፡፡ መጀመሪያ ላይ ከኦሮሞ የጎሣ መሪዎች አንዱ የሸዋው አባ ጉቺ ኤልማያ በቱርክ፣ በአረብ፣ በሶማሊ፣ እና በአህመድ ግራኝ የአዳል ጦር ሰራዊቶች ላይ መሬት ጠብ የማይሉ መርዛማ ቀስቶችን እያዘነቡባቸው ከባድ ጉዳት አድርሰውባቸው ነበር፡፡ ይህ የሆነውም በባዱቄ (በሁዋላ ቢሾፍቱ በቅርቡ ደግሞ ደብረ-ዘይት በተባለው) ጦርነት ነው፡፡ ኢላማቸውን በማይስቱት ከአባ ጉቺ ኤልማያ ሰራዊት በሚተኮሱት ቀስቶች የሱ ሠራዊት ክፉኛ መጎዳቱን የተገነዘበው ግራኝ ለአባ ጉቺ ስጦታ ልኮ፣ ሌላ የበለጠ ስጦታ እንደሚሰጣቸው፣ ግዛታቸውን እንደማይነካባቸው እና እርሳቸውንም ሆነ ህዝባቸውን እስልምናን ተቀበሉ ብሎ እንደማያስገድዳቸው ቃል ገብቶ ከክርስቲያኑ ንጉሥ ከአጼ ልብነ-ድንግል ጎን ቆመው እሱን ከመውጋት ተቆጥበው ገለልተኛ እንዲሆኑ አግባባቸው፡፡ አባ ጉቺ ክርስቲያንም እስላምም ስላልነበሩ በክርስቲያኑና በሱ በእስላሙ መካከል በሚደረገው የሃይማኖት ጦርነት ጣልቃ ከመግባት እንዲታቀቡ መከራቸው፡፡ አባ ጉቺ ኤልማያም ክርስቲያኖችን እነደማይረዱ ማሉለት፡፡(44) አባ ጉቺ ኤልማያን መንግሥትንና አገሪቱን ከድተዋል ብለው የኢትዮጵያው ንጉሠ-ነገሥት ወነጀሏቸውና ለግድያ ሲያሳቧቸው አባ ጉቺ የሰሌ (ሰላሌ) ኦሮሞ መሪዎችን፤ አባ መርዞ፣ አባቡላ፣ ንጉሥ አባ ቆርቾ እና አባ ጉታ የተባሉትን የኦሮሞ ባላባቶች አስተባብረው ሸንብራ ኩሬ (አዳማ ወይም የዛሬዋ ናዝሬት) በተባለው ቦታ ድንገት ሳይታሰብ የንጉሠ-ነገሥቱን ጦር ገጥመው አጠቁ፡፡ የሸንብራ ኩሬ ጦርነት ከተካሄደ አንድ ቀን በኋላ ንጉሠ-ነገሥቱ ሰራዊታቸውን አሰባስበው ግራኝን እንደገና ለመግጠም ሲያስቡ የኦሮሞ ጎሣ መሪዎች በነዚያ መርዘኛ ቀስቶቻቸው በርካታ ክርስቲያን ወታደሮቻቸውን ገደሉባቸው፡፡ በዚህ ሳቢያ በጎሣ መሪዎቹና በንጉሠ-ነገሥቱ ጦር መካከል ከባድ ጦርነት ተደርጎ ከሁለቱም ወገን ብዙ ደም ፈሰሰ፡፡ በመጨረሻ የጎሣ መሪዎቹ ሁሉም ተገደሉና እነሱም ተከታዮቻቸውም ከሃዲዎች፣ ያልተገረዙ፣ አረመኔዎች ተባሉ፡፡ ከመላ ሐገሪቱ ውስጥ በጣት የሚቆጠሩ የጎሣ መሪዎች ንጉሠ-ነገሥቱን ስለከዱ ሁሉም ኦሮሞዎች መገለል እና መዋረድ ደረሰባቸው፡፡

በዚህም ኦሮሞዎች፣ የኢትዮጵ ልጆች፣ የደሸት እና የመደባይ ልጆች፣ የነገሥታት ዘሮች፣ ብልሆች፣ ነቢያት፣ ሊቃውንትና አገራቸውን አፍቃሪዎች በመሆናቸው እጅግ እንዳልተከበሩና እንዳልተፈቀሩ ሁሉ እየተናቁ በርካታ ዓመታት አሳለፉ። (45)

ሳልሳዊ ኢትዮጲስ ፣ የምድያም ከፍተኛ ካህን የሆነው የየትሮአብ የልጅ ልጅ ከ3400 ዓመት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ሱባ የተባለ ከተማ መስርቶ ነበር። የመልከጼዴቅ ልጅ የኢትዮጵ ዝርያዎች በዚያ ከተማ ይኖሩ ነበር። የኬንያና የታንዛኒያ አባ ሱባዎች ምናልባት ከሱባ ከተማ የፈለሱ ይሆናሉ። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ከሦስቱ የኢትዮጵ ሴት ልጆች አንዷ ሱባ ትባል ነበር። አባ ባሕርይ እንደነገሩን ሜጫ ደአሌን ይወልዳል። ደአሌ ሱባን እና ሌሎችን ይወልዳል ። ኢትዮጵያ መጠሪያዋን ያገኘችበት ንጉሠ-ነገሥት ኢትዮጵ ከኦሮሞዎች ጋር ምንም ዝምድና ባይኖረው ኖሮ ኢትዮጵ ከ4000 ዓመት በፊት ለልጁ መጠሪያ ያደረገውን ‹‹ሱባ›› የሚለውን ስም እንዴት ኦሮሞም ለልጁ መጠሪያ ሊያደርገው ቻለ? ተዛምዶው ግልጽ ነው፤ ፍንትው ያለ! ይህ የሚያረጋግጠው የኦሮሞ ጥንተ-አባት ኢትዮጵ መሆኑን ነው። ኢትዮጵ ለኦሮሞ ብቻ ሳይሆን ለሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ሁሉ መገኛ አባት ነው። ሱባ ብርቅዬ የሆነ ቆንጆ የኦሮሞ ቃል ነው። የሰው እና የከተማ ስም ይሆናል። የቋንቋችንና የፊደላችን መጠሪያም ነው። ከአፍሪቃ ጥንታዊው መናፈሻ ሱባ ይባላል። በአምቦ መስመር መናገሻ ከተማን አለፍ ብሎ ከአዲስ አበባ 17 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። ኦሮሞውና አማራው እስከ ዛሬ በሚኖሩባቸው ቦታዎች ‹‹ሱባ›› የሚል ስያሜ መኖሩ ኢትዮጵ ከኦሮሞ እና ከአማራ ጋር እንዲሁም አማራ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ጋር ያለውን ዝምድና ያመለክታል።

‹‹ሱባ›› ባለፉት ጊዜያት የተለየ ግምት የሚሰጠው ልዩ ቃል ነበር። የኦሮሞ ሊቃውንት እና ነቢያት የሚጽፉበት ፊደል ‹‹የሱባ ፊደል›› ይባል ነበር። የሱባ ቋንቋም አዳምና ሄዋን ይነጋገሩበት የነበረው የመጀመሪያው ሰብአዊ ቋንቋ እንደነበረ ይገመታል። ሱባ የሚለው ቃል የተገኘው ‹‹ሰብ›› ከሚለው ቃል ነው። ትርጉሙም በሱብኛ ‹‹ሰብአዊ›› ማለት ነው። የሱባ ፊደልም የሱባ ቋንቋ በጽሁፍ የሚገለጽበት ብልሃት ነበር።





አዲስ አበባ የሚኖር የመረጃ ምንጬ፡- ‹‹ሱባ›› የሚባሉ አንድ አዛውንት ከብዙ አመታት በፊት አዲስ አበባ ይኖሩ እንደነበር ነግሮኛል። ያ ወዳጄ እንደነገረኝ አዛውንቱ ከኦሮምኛ ጋር ተመሳሳይ ቋንቋ ይናገሩ ነበር። የተወለዱት በትግራይ እና በኤርትራ ድንበር ኢሮብ አጠገብ ለየት ያሉ ሰዎች በሚኖሩበት “ሱባ” በተባለው ቦታ ነበር። የነዚህ ሰዎች ቋንቋ ከኦሮምኛ ጋር በደንብ የሚቀራረብ ከሆነ ኦሮምኛ የመጣው ከሱባ ቋንቋ ሊሆን ይችላል። ይህ ጉዳይ በወጉ ሊጠና ይገባል። አንድ የኢሮብ ማኅበረሰብ አለ። ምናልባት ይህ ማኅበረሰብ ሱባንና ኗሪዎቹን በተመለከተ ብርሃን ይፈነጥቅ ይሆናል።

ግእዝ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ቋንቋ ከመሆኑ ከሦስት ሺ ዓመታት በፊት የመደባይ (ኦሮሞ) ማጂ ቀሳውስት እና ሊቃውንት ከጥንት አባቶቻቸው ከመልከጼዴቅ፣ ከኢትዮጵ እና ከደሸት በወረሱት መሰረት በሱባ ቋንቋ እና ፊደል ነበር የሚናገሩትና የሚጽፉት። ከፍ ብዬ እንደገለጥኩት፣ በኋላ ግን ቀዳማዊ ምኒሊክ በሱባ ቋንቋ የሚናገር እና የሱባ መጽሐፍ የሚገኝበት ማንኛውም መደባይ/ኦሮሞ/ ይገደል ሲል አወጀ። በዚህ ምክንያት የመደባይ/ኦሮሞ/ ሊቃውንት በሱባ ቋንቋ መጻፍ አቆሙ። እንደ እድል ሆኖ በሱባ ቋንቋና ፊደል የተጻፉ ጥቂት መጽሐፎች ተርፈውልናል። ቀጥሎ በሱባ ቋንቋ በብራና ላይ ከተጻፈ መጽሐፍ የተወሰዱ ጥቂት ገጾችን እና የሱባን ፊደል ለየብቻ እንመለከታለን፡-


1
Wa wi wă wā we wu wue wuā wowa wo
IWa wi wă wā we wu wue wuā wowa wo
Y yi yă yā ye yu yue yuā yowă yo
IYa
Nga
Na ni nă nā ne nu nue nuā. nowa no
Fa fi fă fā fe fu fue fuā fowa fo
Va vi vă vā ve vu vue vuā vowa vo
Ba bi bă bā be bu bue buā bowa bo






2
Pa Pi Pĭ Pā Pe Pu Pue Puā Powa Po
Ma mi mĭ mā me mu mue muā mowa mo
Ra ri rĭ rā re ru rue ruā rowa ro
La li lĭ lā le lu lue luā lawa lo
Tda
Da di dĭ dā de du due duā dowa do
Ta
Ta ti tĭ tā te tu tue tuā towa to
Sa si sĭ sā se su sue suā sawa so



ዝርያዎች ይሆናሉ የሚል ጥርጣሬ አለኝ። ፍርጃ ሆነና የኢትዮጵያ መደባይ/ኦሮሞ እንዳደረገው እነዚህ ህዝቦችም የሱባ ፊደላቸውን ጥለው ያሁኖቹ የኢትዮጵያ ኦሮሞ ምሁራን እንዳደረጉት እነሱም የላቲን ፊደል ጸሐፊዎች ሆነዋል።

የሱባ ቋንቋን ጠብቀው ስላቆዩ (መደባዮች ይጠቀሙበት ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ይሆናል የሚል ግምት አለኝ) ከላይ የቀረቡትን ያባቶቻቸው የነበሩትን የሱባ ፊደላት አባ ሱባ ቢያገኙዋቸው ደስ እያላቸው ይጠቀሙባቸዋል ብዬ አስባለሁ። ልክ እንዲሁ ዘመዶቼ ኦሮሞዎችም አባቶቻችን ፊደልና ሥልጣኔ የሌላቸው ይመስል በተውሶው የላቲን ፊደል ከመጻፍ ይልቅ ወደ ራሳቸው ፊደል ይመለሳሉ የሚል እምነት አለኝ። ኢትዮጵያውያን የሥነ-ልሳን ሊቃውንት እነዚህን ፊደላት መርምረው ለኦሮምኛ መጻፊያነት ውጤታማና ተመራጭ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያጠናሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አንድ ወይም ሁለት የሥነ-ልሳን ተማሪዎች በሱባ ማስተርሳቸውን እየሰሩ እንደ ሆነ ሰምቻለሁ። ነገሩ እውነት ከሆነ፣ እነዚህ ተማሪዎች የአያት ቅድመ-አያቶቻችንን ታላቅ ቋንቋ እንዲያገግም አጋዥ ኃይሎች እንደሚሆኑ አምናለሁ።

የሱባ ፊደላት ‹‹ደኸ (dh)››ን የመሰሉ (ዓየር ከውጪ ወደ ሳንባ በማስገባት የምትፈጠረውን በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ውስጥ ብቸኛዋን) የኦሮምኛ ድምጽን ጨምሮ የማንኛውንም ሰብአዊና የእንስሳት ድምጾችን ለመወከል ብቃት እንዳለው እኔ በግሌ ተገንዝቤአለሁ። የሱባ ፊደላት የላቲን ፊደሎችን ለመተካት አንድ አማራጭ ናቸው። ይህን ለማድረግ የሱባን ፊደላት በወጉ ማጥናት እና የበለጸገውን የኦሮምኛ ቋንቋን ድምጾች በትክክል ለመጥራት የሚያስችሉበትን ሁኔታ ማየት ያስፈልጋል። እንደ መልካም ዕድል ሆኖ የሱባ እና የግእዝ ቋንቋ መዝገበ-ቃላት በመሪራስ አማን በላይ ተገኝቷል፡ የታተመ ቅጂው አለኝ። ይህ መዝገበ-ቃላት የጠፋውን የሱባ ቋንቋ እንደገና እንዲያንሰራራ ለማድረግና ለማስጠበቅ ይጠቅማል። በሱባ ፊደላት ላይ ያደረግሁት ጥናት አንዳንዶቹ ከላቲን-እንግሊዝኛ ፊደላት ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን ያሳያል። ለምሳሌ እነዚህን የላቲን ፊደሎች እናስተውል፡- ‹‹Y, V, D, t, S›› እነዚህ 5 ፊደላት አሁን የላቲኑ





አካል ሆነዋል። የተገኙት ግን ከአባቶቻችን ጥንታዊ የሱባ ፊደላት ነው ።

ይህ ሁኔታ የሱባ ቋንቋን ለአንዳንድ የላቲን ፊደሎች ምንጭ የሆነ የመጀመሪያው ቋንቋ ያደርገው ይሆን? ይህን ማጥናትና በማስረጃ ማንሳት ወይም መጣል የሥነ-ልሳን ምሁራን ጉዳይ ነው። ሱባ የመጀመሪያው ልሳነ-ሰብ ይሁን አይሁን አንድ ነገር ላይ ግን ርግጠኞች ነን፤ ከጥንታዊ እና ከተረሳ ፊደሉ ጋር የጠፋ አንድ ጥንታዊ ቋንቋ ነው።

ምንም እንኳ ዝርያዎቻቸው በሱባ ቋንቋ ቢጽፉና ቢናገሩ ኦሮሞውና አማራው የመጀመሪያ መኖሪያውን እየተወ አንዱ ካንዱ እየተነጠለ በየራሱ መንገድ ሲሄድ እና ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር ሲቀላቀል ከላይ እንዳልኩት የየራሱን አዳዲስ ቋንቋ እየፈጠረ ወይም እየለመደ ወይም እየፈጠረም እየለመደም መጣ።

ግዕዝ የበላይ በሆነበት ወቅት የኦሮሞ ምሁራን በግዕዝ መጠቀምና አንዳንድ የጥንት መጽሐፎቻቸውን ከሱባ ወደ ግዕዝ መተርጎም ነበረባቸው። አንደ አብነትም በርካታ መጽሐፎችን አካትቶ እንደያዘው እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ አንድ ትልቅ መጽሐፍ መጽሐፈ-ሱባኤ ነው። ከሱባ ቋንቋ ወደ ግዕዝ እንደተተረጎሙ የሚገመቱ ጥቂት መጽሐፎችን ይዟል። በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ አንደ አልኩት፥ መጽሐፉን በኑቢያ ውስጥ ከሚገኘው ጀበል ኑባ በአንድ የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ፍርስራሽ ውስጥ ከ50 ዓመታት በፊት እንዳገኙት መሪራስ አማን በላይ ይናገራሉ። ጀበል ኑባ የሚገኘው በሱዳን ውስጥ ኑቢያ ነው። ጉግል ውስጥ ገብቶ የተወሰነ መረጃ ማግኘት ይቻላል።

በመግቢያው ላይ እንደጠቀስኩት መሪራስ አማን በላይ በመጽሐፈ-ሱባኤ ውስጥ ከሚገኘው መረጃ አሳጥረው እያውጣጡ ወደ አሥር መጽሐፎችን ጽፈዋል። መጽሐፎቻቸው ስለ መልከጼዴቅ፣ ኢትዮጵ፣ ደሸት፣ መደባይ/ኦሮሞ፣ አማራና ስለ ሌሎችም ዛሬ ኢትዮጵያውያን ስለሚባሉት የኢትዮጵ ተወላጆች ህይወትና የዘር ሐረግ በዝርዝር ያስረዳሉ።






የሱዳን ማፕ (2011 እ.ኤ.አ በሁዋላ) የኑባ ተራሮች(ጀበል ኑባ) በደቡባዊ ኮረዳፋን ውስጥ ተስለዋል።

ሁለት ምሁራን፣ አንዱ ኢትዮጵያዊው ስርግው ሃበለሥላሴ፣ *(ጥንታዊና መካከለኛው የኢትዮጵያ ታሪክ እስከ 1270 ድረስ፤ ገጽ 31 ላይ)* እና ሁለተኛው አሜሪካዊ፣ ጊ. ደብልዩ. ቦዌርሶክ፣*(የአዱሊስ ዙፋን*፤ ገጽ 69 ላይ) የግዕዝ ፊደል ከሳባዉያን ሆሄያት ጋር ስላለው ዝምድና ያሉት ነገር አለ። ስርግው ሃብለሥላሴ እስከ 20ኛው ክፍለ-ዘመን አጋማሽ ድረስ ግዕዝ ከሳቢያን ተገኘ ብለው ምሁራን ያምኑ ነበር፤ ሆኖም ግዕዝ ከሳባውያን ራሱን አግሏል ሲሉ ይህንን ግምት ውድቅ ያደርጉታል ብለዋል። ጊ. ደብልዩ. ቦዌርሶክ ደግሞ በተቃራኒው "የግዕዝ ፊደል ከሳባ ፊደል መቀዳቱ እውነት ነው፤ ሆኖም አሁን (በ4ኛው ክፍለ-ዘመን) ፊደላቱ የተለዩ ሆነዋል፤ አፃፃፉም ሳባ እንደ ሚጻፍበት ሳይሆን ከግራ ወደ ቀኝ ተቀይሯል" ሲሉ ጽፈዋል። አሜሪካዊው የታሪክ ሊቅ ወደ ሰነዘሩት ሃሳብ አደላለሁ፤ ምክንያቱም ሳቢያን ምንጫቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረችው እና ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1400 ዓመተ-ዓለም በአጼ  እስያኤል የተመሰረተችው ሳባ ከተማ በመሆኗ እና አጼ እስያኤል የአረቢያ ቅኝ ገዢ የነበረና የሳባን ፊደል እና ዘመናዊ ሥልጣኔን ከኢትዮጵያ ወደ አረቢያ የወሰደ በመሆኑ ነው። የተገላቢጦሹ ግን አይደለም። ምክንያቱም በአረቢያ ውስጥ በዚህ ስም የሚጠራ ምንም ዓይነት ከተማ ከመመስረቱ በፊት ሳባ ከተማ ኢትዮጵያ ውስጥ ነበረች። በተጨማሪም በዚያን ጊዜ ቀይ ባሕር አጠገብ የነበረችውን አረቢያን ቀርቶ በአጼ እስያኤል ሥም የተሠየመውን አሕጉር እስያንም ኢትዮጵያ ትገዛ ነበር። ይህም ከአጼ እስያኤል ቀጥሎ ወደ ሥልጣን የመጣችው እና አረቢያንና  እስያን ከሱ ወርሳ ካስተዳደረችው ከንግሥት ሳባ በፊት ነው። አንዳንዶቹ የግዕዝ ፊደላት ከሳባ ሆሄያት ጋር ይመሳሰላሉ። አንድ ሰው አንዳንድ የሳባ-ኢትዮጵያ ፊደላትን ቢገለብጥ ግዕዝ እስከ 4ኛው ክፍለ-ዘመን ሲቆጠር ለ1400 ዓመታት ከነሱ ርቆ ስለነበር ነው። እባክዎ አንዳንዶቹ ሆሄያት ከግዕዝ ፊደላት ጋር መመሳሰላቸውን በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ያለውን የሳባን ፊደል ተመልክተው ያረጋግጡ።





የኣያት ቅድመ-ኣያቶቻቸውን ክብር ታላቅነትና ዝና መረዳት የተሳናቸው አንዳንድ ኢትዮጵያውያን "ግዕዝ" እየተባለ የሚጠራው የኢትዮጵያ ፊደል "ከአርመን ፊደል የተቀዳ ነው" ይላሉ። ይህ ፍጹም ስህተት ነው። እውነታው የዚህ ተገላቢጦሽ ነው። ከክርስቶስ ልደት



የኣያት ቅድመ-ኣያቶቻቸውን ክብር ታላቅነትና ዝና መረዳት የተሳናቸው አንዳንድ ኢትዮጵያውያን "ግዕዝ" እየተባለ የሚጠራው የኢትዮጵያ ፊደል "ከአርመን ፊደል የተቀዳ ነው" ይላሉ። ይህ ፍጹም ስህተት ነው። እውነታው የዚህ ተገላቢጦሽ ነው። ከክርስቶስ ልደት

እስከ 5ኛው ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ድረስ አርመኖች የራሳቸው ፊደል አልነበራቸውም። አሽዲያምን የተባለች ሜሪካዊ ተመራማሪ እንደምትነግረን፣ ቅዱስ መስሮብ ማሽቶትስ የተባለ አርመናዊ መነኩሴ "ለአርሜኒያ አዲስ ፊደል በመቅረጽ ሥራ ላይ ተጠምዶ ነበር።...ቅዱስ መስሮብ ኢየሩሳሌምን ለመሳለም በተጓዘበት ወቅት ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን እንዳገኘ እና ከእምነት መጽሐፎቻቸው አንዱን ይዞ እንደተመለሰ ብዙዎች ይናገራሉ። በግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ እየተመራ የተወሰኑ ሆሄያትን ከግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ ወስዶ የጀመረውን የፊደል ቀረፃ ሥራ እንዳሟላ መገመት የማያስኬድ አይሆንም።" (አሽዲያምን "ስለ አርመን እና ኢትዮጵያ ጽሑፎች" ሰኔ 24፣2011)። አሽዲያምን ሙሉ በሙሉ ትክክል ነች። የግዕዝ ፊደላት ከ2500 ዓመት በፊት ከኢትዮጵ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያውያን እጅ ነበሩ። ስለዚህ ለኢትዮጵያ አብሮ በቀል ናቸው። አርመኖች የራሳቸውን ፊደል ሲቀርጹ ከኢትዮጵያ ፊደል ኮርጀዋል። አርመኖች ፊደሎቻቸውን ያሟሉት ከኢትዮጵያ ወስደው ነው። ለነሱ ድምፀ-ልሳናት እንዲስማሙ ፊደላቱን ስለለዋወጧቸው ከኛ ፊደላት ጋር ቁርጥ አንድ ዓይነት አይደሉም። እኛ ከአርመን የኮረጅን ቢሆን እንኳ ኦሮምኛን ጨምሮ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች መጻፊያነት ከላቲን ፊደል ይልቅ የኛ ፊደል ይበልጥ የተሻለና የተመቸ ነው። በዚህ ተጨባጭ ምክንያት ብቻ እንኳ የላቲኑን ትተን በራሳችን ፊደል ልንጽፍ ይገባል።

በመጨረሻ በኢትዮጵያ የንግሥት ሕንደኬ ንብረት ሃላፊ የነበረውን ሰው ሃዋርያው ፊሊጶስ በሰረገላው ላይ ተቀምጦ ከብሉይ ኪዳን ላይ ስለእየሱስ የተነገረውን የኢሳይያስን ትንቢት ሲያነብ እንዳገኘውና ስለ እየሱስ ክርስቶስ መስክሮለት ስላመነ በውሃ እንዳጠመቀው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጽፏል። ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ኢትዮጵዊ መኮንን የአይሁድ እምነት እንደሚከተልና ያነብ የነበረውም ካገሩ ይዞት የሄደውን በራሱ ልሳን በግዕዝ ቋንቋ እና ፊደል የተጻፈ መጽሐፍ እንደነበር ግልጽ ነው። ያ የሆነው እየሱስ ክርስቶስ እንዳረገ ከዛሬ 2000 ዓመት በፊት ሲሆን አርመናዊያን ለቋንቋቸው ፊደል የቀረጹት ግን ከ400 ዓመት ወዲህ ነው። ከዚያ በፊት ፊደል አልነበራቸውም። ኢትዮጵያውያን ግን ከ2000 ዓመት በፊት መጽሐፍ ያነቡ እንደነበር ነቢዩ ፊሊጶስ ባስመዘገበው መሰረት በመጽሐፍ





ቅዱስ ላይ ተረጋግጧል። ታዲ ማን ከማን ኮረጀ ቢባል ነው ሊያስኬድ የሚችለው?

አርሜንያ ከኢትየዮጵያ ጋር ስትነፃፀር ትንሽ አገር ናት። ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ናት። ከአራት ሚሊዮን ዓመት በላይ እድሜ ያለው የሰው አጽም የተገኘው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ገነትን ያጠጡ ከነበሩት አራት ወንዞች ሁለቱ ማለትም ግዮን እና ዋቢ ሸበሌ በኢትዮጵያ ውስጥ መገኘታቸው ቢያንስ ከፊል ገነት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደነበረች ያረጋግጣል። አክሱም ከተማ በንጉሠ-ነገሥት አክሱማይ የተመሰረተችው ከክርስቶች ልደት 900 ዓመት በፊት ሲሆን የአርመን ዋና ከተማ የሪቫን በንጉሥ አርጊሽቲ የተመሰረተችው ግን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ782 ዓመተ-ዓለም ነው። ይህ ማለት አክሱም በዕድሜ ከየሪቫን በ112 ዓመት ትበልጣለች ማለት ነው። በኛችን የሚገኙ የጽሑፍ ማስረጃዎች እንደሚያረጋግጡት የሪቫን ከመቆርቆርዋ ከ100 ዓመት በፊት በፍትሃዊነቱ "የዓለም አባት" ይባል የነበረው ንጉሠ-ነገሥት አክሱማይ በአፍሪቃ፣ በአረቢያ እና በእስያ አሕጉራት በሥሩ ይተዳደሩ ለነበሩ ለ100 ነገሥታት ሕግ አውጥቶ በጽሁፍ ልኮላቸዋል። ሕጉም በጣኦታት ማምለካቸውን ትተው ባንድ ፈጣሪ አምላክ በእግዚአብሔር እንዲያምኑ የሚያሳስብ ነበር። ከዚህ 1400 ዓመት ቀደም ብሎ ኢትዮጵያን ያለ ዘውድ ማስተዳደሩ የተመዘገበለት "ዝዮን" የተባለው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ "ሁሉም ሰው ማንበብና መጻፍ መማር አለበት፣" ሲል አዋጅ አስነግሮ ነበር። በኋላም በግዛቱ ውስጥ የሚሰራጭ የዜና መጽሔት/ ጦማር/ ነበረው። ያ ጦማርም በዓለም ላይ የመጀመሪያው ጋዜጣ ነው።

ይህ የሆነው ከዛሬ 5350 ዓመት በፊት ነው። ይህም የአርመን ዋና ከተማ የሪቫን ከመመስረትዋ ከ2468 ዓመት በፊት ማለት ነው። ስለዚህ እንዴት ኢትዮጵያ ፊደል ከአርመን ተዋሰች ይባላል? ኢትዮጵያ ከአርመን በፊት ፊደል እንደነበራት ቢካድ እንኳ የኦሮሞና የአማራ ሊቃውንትን ጨምሮ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ይጽፉበት የነበረው ቀደም ሲል በተጨባጭ ያቀረብኩት የሱባ ቋንቋ እና ፊደል እንዴት ይካዳል?

ከኃይሌ ፊዳ በተቃራኒ፣ አርቀ አሳቢና ሃገሩን ይወድ የነበረው ኦናሲሞስ ነሲብ የኦሮሞ ሚሲዮናዊና መምህር በአውሮጳ ተምሮ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን መጽሐፍ ቅዱስን በግእዝ ፊደል ወደ ኦሮምኛ የተረጎመ እንዲሁም አስቴር ጋኖ ከተባለች አንዲት የኦሮሞ ሴት ጋር ሆኖ የኦሮምኛ መዝገበ-ቃላትን የጻፈና መዝሙራትንና ምሳሌያዊ አባባሎችን የሰበሰበ ሊቅ ነበር። ፓስተር ኦናሲሞስ ነሲብ የተረጎመውን መጽሐፍ ቅዱስ "መጽሐፈ ቁልቁሉ" ብሎታል። ያ ጠሊቅ ምሑር ኦናሲሞስ ነሲብ የግዕዝ ፊደላትን ተጠቅሞ በ19ነኛው ክፍለ-ዘመን ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ በኦሮምኛ ከጻፈ እኛ በ21ኛው ክፍለ-ዘመን እንደሱ የማናደርግበት ምክንያት ምንድነው? የተከበረው ፓስተር ኦናሲሞስ ነሲብ እና ጊፍቲ አስቴር ጋኖ የኢትዮጵያ ፊደላት ለኦሮምኛ ቋንቋ መጻፊያነት ከላቲኑ ይበልጥ የተመቹና ተስማሚ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

የኦሮሞ ምሁራን ከኢትዮጵያውያን ፊደል ይልቅ የላቲን ፊደልን የመረጡባቸው ሁለት ምክንያቶች የግእዙ ፊደል ‹‹dh›› ለሚለው የኦሮምኛ ድምጽ መወከያ ምልክት የሌለው መሆኑና ሰባቱ የግእዝ አናባቢዎች አሥር አናባቢዎች ላሉት ለኦሮምኛ ቋንቋ የሚመጥኑ ባለመሆናቸው ነው ይባላል። የሚያስገርመው ነገር ቀደም ሲል እንዳልኩት የሱባ ፊደል ግን ‹‹dh›› የሚለውን የኦሮምኛ ድምጽ የሚወክልበት ፊደል ያለው መሆኑና ሥርዓተ-አናባቢዎቹም ቁጥራቸው አሥር መሆኑ ነው። ከላይ በተቀመጠው የሱባ ፊደል ላይ በ‹‹ዲ›› ተራ የቀረበውን ይመልከቱ እስቲ፣ ‹‹dh›› ከአሥሩ አናባቢዎች አንፃር የሚነበብባቸው ፊደሎች አሉት። የጥንት ኦሮሞዎችና ጥንታውያን አባቶቻችን እንዲህ አሟልተው መጠቀማቸው የሚያስገርም ነው።

ስለ ኦናሲሞስ ነሲብ እና አስቴር ጋኖ እንደገና ለመናገር እነዚህ ሁለቱ ብቻ አይደሉም በግዕዝ ፊደል መጽሐፍት የጻፉ። ከአስቴር ጋኖ እና ከኦናሲሞስ በፊትም ኦሮምኛ በግዕዝ ፊደል ለመጻፉ የተመዘገበ መረጃ አለ። ቋንቋው ኦሮምኛ ሆኖ በግዕዝ ፊደል የተጻፈውን አንድ ጥቅል ቀጥሎ ይመልከቱ። የጥቅሉን እድሜ





በትክክል ልነግርዎ አልችልም፣ እንደሚያዩት ግን እድሜ- ጠገብ ይመስላል። ቢያንስ አንድ ሺ ዓመት እገምተዋለሁ። በአንድ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ነው የተገኘው።



በትክክል ልነግርዎ አልችልም፤ እንደሚያዩት ግን እድሜ- ጠገብ ይመስላል። ቢያንስ አንድ ሺ ዓመት እገምተዋለሁ። በአንድ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ነው የተገኘው።





ጥንታውያን ኦሮሞ ምሁራን በግዕዝ ፊደል መጻፍ ከቻሉ ልጆቻቸውም ፍላጎቱ ቢኖረን ኖሮ እንዲሁ መጻፍ እንችል ነበር። ቁቤን ያስጀመሩ ምሁራን ያንን ርምጃ የወሰዱት የኢትዮጵያ(ሳባዊ) ፊደላት የአማራና የትግሬ ብቻ ስለመሰላቸው በአማራ፣ በአማርኛ እና በግእዝም ላይ በነበራቸው ጥላቻና ቁጣ ተገፋፍተው ነው። ነገር ግን ግለሰቦቹ በዚህ ነጥብ ላይ ፍጹም ተሳስተዋል። ከሁሉ አስቀድሞ የኢትዮጵያ/ሳባዊ ፊደላት ባለቤቶች ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው





ኦሮሞን ጨምሮ ሁሉም ኢትዮጵያውያን መሆናቸው ግልጽ መሆን አለበት። የማንኛውም የአንድ ነገድ የግል ንብረት አይደሉም።

በተጨማሪም እነዚህ ፊደሎች የሚጠቀሙባቸውን ሰዎች ራሳቸውን እንዲገልጹና እርስ በርሳቸው እና ከሌሎችም ጋር እንዲግባቡ ከመርዳት ውጪ ፊደሎቹ በራሳቸው በማንም ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት አላደረሱም። በላቲን ፊደል ከመጻፍ ይልቅ በግእዝ ፊደል መጻፍ ለኦሮሞዎች ጠቀሜታው በርካታ ነው።

አንደኛው የግእዝ ፊደላት ከላቲኑ በተሻለ የኦሮሞን የንግግር ድምጾች 99% ይወክላሉ። ስለዚህ ጥቂቅን ማሻሻያዎችን ለምሳሌ በላቲን ፊደል ላይ ለሌሉት የኦሮሞ ድምጾች እንደ ‹‹À‹ Ŏ— Û— m— ë— '— Ŏ— h— ¤— እና Ê›› አይነቶች አናታቸው ላይ ምልክት አድርጎ ኦሮምኛን በግእዝ ለመጻፍ ያመቻል።

ሁለተኛው ደግሞ ኦሮምኛን በኢትዮጵያዊ ፊደላት መጻፍ ጊዜና ገንዘብ ይቆጥባል። በላቲን ሲጻፉ በርካታ ፊደላትን የሚጠይቁ የኦሮምኛ ቃላት በሳባዊ/ግእዝ ሲሆን ግን በጥቂት ፊደላት ይወከላሉ። ለምሳሌ በላቲን ‹‹Adaamaa›› የሚለውና ሰባት ፊደላት የፈጀው ቃል በ‹‹ሳባዊ/ግእዝ›› ሲጻፍ ‹‹አዳማ›› ተብሎ በሦስት ፊደላት ብቻ ሊፃፍ ይችላል። በ‹‹ግዕዝ›› የሚጻፈው አንድ መጽሐፍ በላቲን ሲጻፍ ሁለት እና ከዚያም በላይ ሆኖ አሳታሚውንም አንባቢውንም ላላስፈላጊ ተጨማሪ ወጪ ይዳርጋል ማለት ነው።

ሦስተኛው በታሪካዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች የ‹‹ሳባዊ/ግእዝ›› ፊደላት በሚለዩኖች በሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በደንብ የሚታወቁና በስፋት የተሰራጩ በመሆናቸው በነሱ መጠቀም መገለልን ለማስቀረትና ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ለመገናኘት ሲባል መሆን ያለበት እውነታ ነው።

አራተኛው የ‹‹ሳባዊ/ግእዝ›› ፊደላት ኦሮሞን ጨምሮ የሁሉም ኢትዮጵያዊ አንጡራ ንብረት ስለሆኑና ከ4000 ዓመታት በፊት የኦሮሞ፣ የአማራና የሌሎችም ኢትዮጵያውያን አባት በሆነው በኢትዮጵ የሚሠራባቸው ስለነበሩ ለኦሮሞ ህዝብ በነዚህ የራሱ በሆኑ



የፊደል ቅርሶቹ መጠቀም የራሳቸው ስለሌላቸው ከላቲን ለመዋስ ከተገደዱት በቅኝ ተገዢነት እና በባርነት ቀንበር ስር ከነበሩት አፍሪቃውያን አንፃር ሲታይ የሚያኮራ ነው። ኢትዮጵያ ከሰብ ሰሀራ አገሮች የራስዋ የሆነ ልዩና ጥንታዊ ፊደል ያላት ብቸኛ አገር ስለሆነች እና ግእዝ ከ12ቱ የዓለም ዋና ዋና ፊደሎች አንዱ ነው ተብሎ ስለሚገመት የግእዝ ፊደል ኦሮሞውን ብቻ ሳይሆን ሌሎች አፍሪቃውያንን እና ባጠቃላይም ጥቁር ሕዝቦችን የሚያኮራ ትልቅ ቅርስ ነው።

አምስተኛውና የመጨረሻው፤ ከላቲን ይልቅ በግእዝ ፊደል መጠቀማቸው ኦሮሞዎችን በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን እንደ እንግዳና እንደ ባእድ ከመታየት ያድናቸዋል። ኦሮሞዎች እና ሌሎችም አማርኛ ተናጋሪ ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን አማርኛን ለጋራ መግባቢያ ቋንቋነት ቢገለገሉበት በርካታ ጠቀሜታዎች ያገኙበታል። የሥራ ቋንቋዋ አማርኛ በሆነባት አገር በኦሮምኛ ወይም በሌላ አካባቢያዊ ያፍ መፍቻ ቋንቋ ብቻ መናገርና መጻፍ ሰፋ ያለ የሥራ እድል አያስገኝም። ለምሳሌ የሥራ ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ሳይማሩ በቁቤና በኦሮምኛ ብቻ የሰለጠኑ ተማሪዎች ከተመረቁ በሁዋላ ከክልላቸው ውጪ ሥራ የማግኘት እድል አጥተው ሲቸገሩ ይታያል። ላይ ላዩን ሲያዩት ጠቃሚ የሚመስል፤ ውስጡን ሲመረምሩት ግን ጎጂ የሆነውን ይህንን አሳሳቢ ሁኔታ ወላጆች ቢገነዘቡትም የማይቆጣጠሩት ሆኖባቸዋል። አሁን አሁን ብልጦቹ አማራ ያልሆኑ ወላጆች እንደሚያደርጉት ኦሮሞዎችም ልጆቻቸው በማናቸውም የኢትዮጵያ ክልል መሥራትና መኖር ይችሉ ዘንድ አማርኛ እንዲማሩላቸው ይፈልጋሉ። ብልጦቹ ልጆቻቸው በድፍን ኢትዮጵያ ተንሰራፍተው መስፈር እና መሥራት እንዲችሉ ተሽቀዳድመው አማርኛ ያስተምሯቸዋል። የትግራይዎቹ መሪዎች አጼ ዮሃንስ እና መለስ ዜናዊም ኢትዮጵያን በቀላሉ ለመግዛት እንዲመቻቸው በአማርኛ ይናገሩም ይጽፉም ነበር። ትግሬ ባልሆኑት ኢትዮጵያውያን ላይ ትግርኛን ጭነውበት ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያን ለመግዛት አስቸጋሪ በሆነባቸው ነበር። ኦሮሞዎችም አማርኛን ችላ ሳይሉ መጠቀሚያቸው ለማድረግ ብልሆች መሆን አለባቸው። የአማርኛን ጥቅም የተገነዘቡት ተጋሩዎች ወገኖቻችን በትግርኛና በአማርኛ አቀላጥፈው እንደሚናገሩት ሁሉ የኦሮሞ





ልጆችም በኦሮምኛና በአማርኛ አፋቸውን እየፈቱ ልሳነ-ክልኤ መሆን ይችላሉ።

የሚከተለውን የቁቤ ጽሁፍ ወስደን ከግእዝ እና ከላቲን ፊደል የትኛው ይበልጥ ውጤታማና ብቁ እንደ ሆነ እንመለከታለን፦

Uummanni Oromoo ilmaan namaa biyya lafaa

ኡመኒ ኦሮሞ ኢልማን ነማ ብያ ለፋ

Kanarratti Uumaman kessaa tokkodha Biyyi

ከነረቲ ኡመመን ኬሳ ቶኮዳ ብዪ

Uumamaa fii jireenya issa Aafrikaa Bahaa

ኡመማ ፊ ጀሬኘ ኢሳ አፍሪካ በሃ

Gara kaabaatti Yemmuu ta'u Uummmata

ገረ ካባቲ የሙ ተኡ ኡመተ

Akata Sabaatti baay'ina gudda qabu kan

አከ ሳባቲ የሙ ተኡ ኡመተ

Baha gaanfa Aafrikaatti argamu keessaa

ባሃ ጋንፋ አፍሪካቲ አርገሙ ኬሳ

Isa tokko Seenaan uummata kanaa akkuma

ኢሳ ቶኮ ሴናን ኡመተ ከና አኩማ

Sabaaf sab-lammaota Aafrikaa heddu namnii

ሳባፍ ሳብ ላሞታ አፍሪካ ሔዱ

Seeraaf sirnaan qulqulleessee barreesse

ሴራፍ ስርናን ቁልቁሌሲ በሬሴ

Jiraachun baatullee uummata seenaa

ጂራቹ ባቱሌ ኡመተ ሲና

Gudddaa fii gaarii qabu akka ta'e huba

ጉዳ ፊ ጋሪ ቀቡ አከ ተኤ ሁበ።

Chuun nama hin dhiba

ቹን ነመ ሕን ድቡ

ከላይ ከቀረበው ናሙና ውስጥ የተወሰኑ ቃላትን እየጠቀስን የኢትዮጵው ፊደል ኦሮምኛን ለመጻፍ ከላቲኑ እና ከኢትዮጵያው ፊደል የትኛው ብቁ፣ ቀልጣፋ እና ጊዜ እና ገንዘብ ቆጣቢ እንደሆነ እንይ፤ Uummanni Oromoo ilmaan namaabiyya lafaa

"Uumamaa" የሚለው ቃል በላቲን ሲጻፍ 7 ሆህያት ፈጅቷል። በኢትዮጵያው ግን "ኡመማ" ተብሎ በ3 ፊደላት ይጻፋል። "oromoo" የሚለው ቃል በላቲን 6 ሆህያት አሉት፡፤ በግዕዝ ግን "ኦሮሞ" ተብሎ በ 3 ሆህያት ይጻፋል። "ilmaan" የሚለው በላቲን 6 ሆሄያት አሉት፤ በግዕዝ ግን አራት በቂው ነው። "namaa፣ biyya፣ lafaa፣" የሚሉትም ቃላት በላቲኑ እያንዳንዳቸው 5 ሆሄያት ፈጅተዋል። በግዕዙ ቢሆን ግን "ነማ፣ ቢያ፣ ለፋ" ተብለው እያንዳንዳቸወቅ በ 2 ፊደላት ይጻፋሉ።

ኡመኒ ኦሮሞ ኢልማንነማ ብያ ለፋ Kanarratt Uumama kessaa tokkodha Biyyi የሚሉትን ደግሞ ስናይ "Kanarratti" በላቲን ሲጻፍ 10 ሆሄያት ያስፈልጉታል። በኢትዮጵያው ፊደል በግዕዙ ግን በ 4 ሆሄያት ይጻፋል። "Uumaman" በላቲን 7 ሆሄያት





ያስፈልጉታል። በግዕዝ ግን 4 ሆህያት ይበቁታል። "kessaa" የሚለው በላቲን 6 ሆሄዎች ያስፈልጉታል። በራሳችን ፊደል ግን "ኬሳ" ተብሎ በ2 ፊደላት ይጻፋል። "Tokkodha" እና "Biyyi" የሚሉትም በላቲን እንደ ቅደም ተከተላቸው 7 እና 5 ሆህያት ሲኖሯቸው በግዕዝ ግን 3 እና 2 ሆሄዎች ብቻ ነው የሚኖራቸው።

በገጽ ሲታሰብ በላቲን 100 ገጽ የሚፈጅ ጽሁፍ በግዕዝ ግን በ40 ገጽ ሊጻፍ ይችላል። ብዙ ሺ ኮፒ ሲታተም በላቲን ሲሆን አላግባብ የሚባክነውንና በግዕዙ ሲሆን ግን የሚቆጠበውን ስንትና ስንት ቶን ወረቀት አስቡት። ጊዜንና ገንዘብን በተመለከተም እንዲሁ ነው። አንባቢ ይገምተው።

ለዘለቄታውም መታሰብ አለበት። የኦሮምኛ ተናጋሪ ሕዝብ ቁጥር በጣም በርካታ ስለሆነ ካናዳ ውስጥ እንግሊዝኛንና ፈረንሳይኛን የሥራ ቋንቋዎች አድርገው እንደሚሠሩባቸው በኢትዮጵያ ውስጥም ከአማርኛ ጎን ለጎን ኦሮምኛ ሁለተኛው የፌዴራሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ እንዲሆን ሊታሰብበት እና ጥቅምና ጉዳቱ በተጨባጭ እየተመዘነ፣ አዋጭነቱ በሳይንሳዊ መንገድ እየተጠና፤ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋቸው በተቀበሉ እንደ ደቡብ ክልል ባሉ ሕዝቦች ላይ ጭነት አለመሆኑም በደንብ እየተረጋገጠ በጥንቃቄ ሊመከርበት ይገባል። ይህ ጉዳይ ባንድ ቀን ጀንበር የሚፈጸም ሣይሆን አዲስ ቋንቋን ለመማር በቂ ጊዜ ስለሚያስፈልግ ዓመታት ሊወስድ ይችላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ አሁን አጂግ አስፈላጊና አንገብጋቢ የሆነው የፊደሉ ጉዳይ ነው። ኦሮሞ ያልሆኑ የቋንቋው ተናጋሪዎች በኦሮምኛ ለመጻፍ በላቲን ፊደል እንዲጠቀሙ ሊገደዱ ነው? "ጊዜና ገንዘብ ከሚያባክነው ከላቲኑ ፊደል ይልቅ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ምቹ በሆነውና በምናውቀው ባገራችን ፊደል እንጽፋለን" ቢሉ ምን ሊደረጉ ነው? "በባዕዳን ፊደል የሚጽፉ በቅኝ ገዢዎች ሲገዙ የነበሩና አማራጭ ያልነበራቸው ሕዝቦች ናቸው። እኛ በጀግኖች አባቶቻችን ደም እና አጥንት ነፃነታችን ተከብሮልን የኖርንና አኩሪ ቅርስ የሆነ የራሳችን ፊደል ያለን ሕዝቦች እንደነሱ ልንሆን አይገባም" ብለው ቢቃወሙ ምን ሊባሉ ነው? ይህ መሠረታዊ ጥያቄ ባግባቡ መልስ ሊያገኝ እንጂ እንደ ዋዛ ሊታለፍ አይገባም።

ጠጅ አማረኝ ስላት ማሩን ታስጭናለች

ራበኝም ስላት እህሉን ታስጭናለች

በረደኝም ስላት ሸማ ትሰዳለች

ሌባዬ ተይዛ ባልጋ ትሄዳለች።

የት አባትዋን አውቃ ታሳዝነኛለች፤

የጣቴን ቀለበት አንተ አድርገው ካሣ፣

በኤማ ጣት ገብቶ አስጨነቀኝሣ።

ሕብሩ /ሰምና ወርቁን የያዘው ሐረግ/ በግጥሙ የመጨረሻ ስንኝ ውስጥ ይገኛል፤ "በኤማ ጣት" የሚለው ነው። ስለ ጣት እና ስለ ቀለበት የተናገሩ አስመስለው ችግር እንደ ጠናባቸው ረዳት ልጃቸውንም እንዳጡ "በኤ ማጣት ገብቶ" ብለው የገለጹበት ሰምና ወርቅ ቅኔ ነው።

የቋንቋ እና የባህል ተፅዕኖን በተመለከተ እውነቱን ለመናገር አማራው ኃይልን ወይም ሕግን ተጠቅሞ ቋንቋውን እና ባሕሉን አማራ ባልሆኑ ላይ ፈጽሞ በግድ አልጫነም። ቢፈልግ እንኳ እንዲህ ዓይነት ተፅእኖ ለማሳደር የሚያስችል የመንግሥት ሥልጣንም አማራው ይዞ አያውቅም። ከሁሉም በላይ ደግሞ እንዲህ ዓይነት ተፅዕኖ ማሳደር ተፈጥሮአዊ ባሕሪው አይደለም። ቋንቋውንና ባሕሉን ሌሎች የተጠቀሙበት በፈቃዳቸው ነው እንጂ በግድ አይደለም። አማሮች እና አማርኛ በንጉሠ-ነገሥት ላሊበላ ሞገስ ካገኙበት ከ11ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ በፈቃዳቸው ባማርኛ የሚጠቀሙ ሰዎች እየበዙ ሲመጡ አማርኛም በተፈጥሮአዊ መንገድ እያደገ መጥቷል። አጼ ላሊበላ ሥልጣን እንዲይዝ አማሮች ከረዱት በኋላ ላሊበላ ለአማራው፣ ለአማርኛ ቋንቋ እና ለአማራው ባሕል አድልኦ እና ቀረቤታ አሳይቷል። አገውኛን የኢትዮጵያ የመንግሥት ኦፊሴላዊ ቋንቋ አድርጎ በአዋጅ መሾም ይችል ነበር። ላሊበላ ግን ከአገውኛ ይልቅ አማርኛን መረጠ። በዚህም አማርኛ እና የአማራ ባሕል እዲታወቁ ረዳ።





ከሃምሳ ዓመት በኋላ አማሮች የኦሮሞዋን ወይዘሮ የጊፍቲ ሃዊ መንዲያን ልጅ ተስፋ-እየሱስን /ይኩኖ-አምላክን/ ሥልጣን ላይ ለማውጣት የላሊበላን ልጅ ይትባረክን ወግተዋል። ላሊበላ እንዳደረገው ተስፋ-እየሱስም ለአማሮች፣ ለአማርኛ እና ለአማራ ባሕል ይሁንታ አሳየ። ምክንያቱም ሥልጣን መያዝ እና ስለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት እንደገና መመስረት የቻለው በአማሮች ድጋፍ በመሆኑ ነው። በቤተ-መንግሥቱ፣ በፍርድ ቤቶቹ እና በአስተዳደሩ አማርኛ እንዲነገር አወጀ። በመሆኑም በዛሬው ዘመን ብልጥ የሆኑት ሁሉ እንደሚያደርጉት እንጀራቸውን ማብሰል የሚፈልጉ ሁሉ አማርኛን ለመልመድ ይተጉ ጀመር። ታዲያ በዚህ አማሮች መወቀስ አለባቸው?

ከላይ የተጠቀሰው እውነታ ከትልቁ ራስ ዓሊ እስከ ትንሹ ራስ ዓሊ ጎንደር ከትመው ለነበሩ ኦሮሞ መሪዎች እና ለትግሬው ለአጼ ዮሐንስም ይሠራል። እነዚህ ሁሉ መሪዎች መንግሥታቸውን ባግባቡ ለመምራት በአማርኛ መገልገልን መርጠዋል። ሥልጣኑ በእጃቸው ስለነበረ ኦሮምኛን ወይም ትግርኛን የኢትዮጵያ የመንግሥት የይፋ ቋንቋ አድርገው አዋጅ ቢያናግሩ የሚያግዳቸው ኃይል አልነበረም። እነሱ ግን ሥልጣናቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ከኦሮምኛ ወይም ከትግርኛ ይልቅ በአማርኛ መጠቀምን መረጡ። ታዲያ በዚህ አማሮች መነቀፍ ይገባቸዋል? አማራ ያልሆኑትን የነዚህን የነገሥታቱን አዋጅስ አማሮች እናስቁም ቢሉ በምን አቅማቸው ያስቆሙት ነበር? ከነሱ ቁጥጥር ውጪ ቋንቋቸው ስለተስፋፋ አማሮች ሊወገዙ አይገባም። ይልቅስ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ሊያገናኝ የሚችል ለቅኔ ጥበብ ምቹ የሆነ የተዋበ ቋንቋ ስለአበረከቱልን ሊመሰገኑ እና ሊወደሱ ይገባቸዋል።

በአዲስ አበባና በትልልቅ ከተሞች፣ በትምህርት ቤቶችና በሥራው ዐለም ተቀባይነት ለማግኘት ብለው ወላጆቻቸው ያወጡላቸውን ስሞች ወደ ‹‹ቆንጆ›› የአማርኛ ስሞች የለወጡ ሰዎች አሉ። እነዚህ ደግሞ ኦሮሞዎችና የደቡብ ህዝቦች ብቻ ሳይሆኑ ራሳቸው አማሮችም ጭምር ናቸው። እላይ በተባሉት ምክንቶች አማሮች ሳይቀሩ ስሞቻቸውን ይለውጡ እንደነበር ዐይነተኛ ምሳሌ የሚሆኑት አሁን በባህር ማዶ የሚኖሩት አቶ ለይኩን ቤተሰቦች ናቸው። ታሪካቸውም ዕውነተኛ ነው። በ1933 ዓ.ም ፋሺስት ኢጣልያ

ኢትዮጵያን ከለቀቀች በኋላ የአርበኛው የአቶ ወልደጻድቅ ክብረት ቤተሰቦች ከመራቤቴ ወደ አዲስ አበባ አመሩ። ስሞቻቸውም ‹‹ዳባሽ››፣ ‹‹ባፈና›› እና ‹‹ሺናባቸው›› ነበሩ። እነዚህን ስሞች የሰሙ የአዲስ አበባ ሰዎችም በጣም እየሳቁባቸው ስለቀለዱባቸው ስሞቻቸውን ለመለወጥ ተገደዱ። ስለዚህም ‹‹የውብዳር››፣ ‹‹ኮከብ›› እና ›‹ወርቁ›› ተባሉ። የአቶ ለይኩን ሌላ ዘመድ በመንዝ ይኖሩ ነበር። ስማቸው ‹‹ነቅንቄ ጎንጤ›› ነበር። ይህ ስም በአዲስ አበባ መሳቂያ ስለሆነ የራሳቸውንም፣ ይባስ ብለው የአባታቸውንም ስም ለወጡት ‹‹ሰዋሰው ክብረት›› ሲሉ። የጎጃምና የጎንደር አማሮችም ወደ አዲስ አባባ ሲመጡ እንዲሁ ስማቸውን ይለውጡ ነበር። የእኚሁ የአቶ ለይኩን የጎጃምና ጎንደር ቤተዘመዶችም በአዲስ አበባ ከተማ ስማቸውን ለመቀየር ጫና ደርሶባቸው ነበር። ለምሳሌ የጎጃሜዎቹ ወይዘሮ ‹‹ሰውበኒት›› እና ‹‹ውጭአደሩ›› ስሞቻቸው በአዲስ አበባ አሳፍረዋቸው ‹‹ሰውነት›› እና ‹‹ባንቺ›› ተብለዋል። ይህም የሚጠቁመን ለቦታና ለሥራ እንዲያመች አቅዶ ስሞችን መለወጥ በኦሮሞዎች ብቻ የተጀመረ አይደለም። በአማሮችም እንጂ። ስለዚህ ኦሮሞዎች ይህን በእነሱ ላይ ብቻ የደረሰ ትልቅ በደል ማድረግ የለባቸውም። ነገሩን አስፍተው መመልከት እንጂ።

ሟቹ መለስ ዜናዊ እና ወያኔ ጓዶቹ ሁሉ አማርኛ እና ትግርኛ አቀላጥፈው ያውቁ ነበር። አማርኛ የሥራ ቋንቋ ሆኖ እንዲቀጥል ሲወስኑ የሚበጃቸውን አስተውለው አድርገዋል። ታዲያ በዚህ አማሮች መዘለፍ አለባቸው? በምንሰጠው ፍርድ ፍትሃውያን መሆን አለብን። ትግርኛን የመንግሥታቸው ቋንቋ አድርገው ቢያውጁ ትግሬዎቹን የሚያግዳቸው ምንም ኃይል አልነበረም። በርግጥ ትግርኛ የኢትዮጵያ የይፋ ቋንቋ እንዲሆን ቢያደርጉ ኖሮ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግርኛ ስለማይናገር ኢትዮጵያን ለማስተዳደር አስቸጋሪ ይሆንባቸው ነበር። ከተግባር የአማርኛን ጠቀሜታ ተረድተው ያንኑ አስቀጠሉ። በዚህ የወያኔ ውሳኔ ላይ አማሮች ምንም ሚና አልነበራቸውም። ቋንቋቸውን መለስ ዜናዊ እና የሱ መንግሥት አባላት ሲያቀላጥፉት ዝም ብለው ያዩ እና ይሰሙ ነበር እንጂ። ታዲያ በዚህ አማሮች መከሰስ ይገባቸዋል?





ኑሮን ለማሻሻል እና በመላ ኢትዮጵያ ከማንኛውም ሰው ጋር ለመግባባት ቋንቋውን መቻል ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ ከመንግሥት ውጪም ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ አማርኛን በፈቃዱ ለመማር የሚፈልግ ሆነ።

ርግጥ ነው በኃይለ-ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ገብቶ ለመማር አማርኛ አንድ መስፈርት ነበር። አማራ የሆኑም ያልሆኑም ተማሪዎች በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና አማርኛን ማለፍ ይጠበቅባቸው ነበር። አማራ ላልሆኑ ተማሪዎች ያማርኛን ብሔራዊ ፈተና በጥሩ ውጤት ለማለፍ አዳጋች ነበር። እንደዚያ መደረጉ ተገቢ አልነበረም። ችግሩ መታየት እና መፈታት ይገባው ነበር። በተጨማሪም አማርኛ የማይችሉ ሰዎች ጉዳያቸውን በፍርድ ቤት እቅርበው ለማስወሰን ይቸገሩ ነበር። ደግነቱ ቱርጁማን እንዲቆምላቸው ይደረግ ነበር። ይህ አገለግሎት ዛሬም ይኖራል ብዬ እገምታለሁ።

አልባሳትን በተመለከተስ? የተለያዩ ነገዶች እንደየምርጫቸው የተለያዩ አልባሳትን ይለብሳሉ። ገበሬዎችን ጨምሮ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን እንደየ ምርጫቸው ተመሳሳይ አለባበስ አላቸው። ለምሳሌ ኦሮሞዎችም አማሮችም የኦሮሞዎች አስተዋጽኦ የሆኑትን ቡሉኮ እና ጋቢ ይጠቀማሉ፤ ተነፋነፍ ሱሪ፣ እጀ-ጠባብ እና ኩታ ይለብሳሉ። ወደው በፈቃዳቸው ያደርጉታል እንጂ መንግሥታዊ የባሕል መመሪያ ስለሌለ አንድ ዓይነት ልብስ እንዲለብሱ የሚያስገድዳቸው ሕግ አልነበረም። ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ወታደራዊው መንግሥት ከላብ-አደሩ እና ከአርሶ-አደሩ ጋር ያለውን አንድነት ለመግለጽ በሚል የመንግሥት ሥራ መሪዎች በሙሉ እንደ ሰሜን ኮሪያ እና እንደ ቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ አባላት ከርካሽ ጨርቅ የተሰፋ አንድ ዓይነት ልብስ እንዲለብሱ ካደረገበት ከደርግ ጊዜ በስተቀር (አንዳንድ ባለሥልጣናት ግን የልብሱን ከለር ብቻ አመሳስለወው ከሀር የተሰሩ ውድ ልብሶችን ይለበሱ ነበር) የበፊቱም ሆነ ያሁኑ የኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የደንብ ልብስ እንዲለብሱ አላስገደደም። አንድም አማራ ስልጣን ባልያዘበት ወይም አማራውን የሚወክል መንግሥት ባልተፈጠረበትና በስሙ የባህል ህግና ደንብ በይፋ ባልታወጀበት ሁኔታ ህዝቡ በፈቃዱ ለሚናገረው፣ ለሚለብሰው እና ለሚያደርገው ነገር አማሮች ተጠያቂ

ሊሆኑ አይገባም፡፡ በተጨማሪ "ንፁህ የአማራ ባሕል" የሚባል ነገር የለም፡፡ ባለፉት ምዕራፎች እንዳየነው ታሪካዊ በሆነው በሁለቱ ሕዝቦች ማህበራዊ መስተጋብር የተነሳ የአማራ ባሕል ከኦሮሞ ባህል ጋር ተዳቅሏል፣ተወራርሷል፣ ተቀላቅሎኣል፡፡ ይልቁንም የኦሮሞው ሃይማኖትና ባህል በአማራው ላይ ገንኖ ይንፀባረቃል፡፡ አንዱ ያንዱን ቋንቋ እና ባሕል በውዴታ ይጠቀም ነበር እንጂ በሁለቱ ጎሣዎች ሰፊ- ሕዝቦች ላይ ሆን ተብሎ የተጫነ የባህል ጭቆና አልነበረም፡፡ በርግጥ አማራ እና ኦሮሞ በቅርብ በተዛመዱባቸው ባንዳንድ የኦሮሞ አካባቢዎች በተለይም በወለጋ ኦሮሞ ወላጆች በፈቃዳቸው ለልጆቻቸው የአማራ ስሞችን ያወጡላቸው ነበር፡፡ ኦሮሞ ወላጆች ለልጆቻቸው ያማራ ስም ያውጡላቸው የሚል መንግስታዊ አዋጅ ወይም ህገ- መንግስታዊ ድንጋጌ የለም፡፡ ማሕበረ-ሰቡ ያንን የሚያደርግበት ምክንያት ብዙ ነው፡፡ ሥራ፣ ሃይማኖት፣ ተቀባይነት ፍለጋ፣ ጋብቻ ወይም አፍቅሮተ-ባሕል ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱ ምንም ሆነ ምን በግዴታ እና በኃይል የተጫነ አይደለም፡፡ በህዝብ ፈቃድ የሚደረግ ነበር፡፡ የወለጋ ኦሮሞዎች ለልጆቻቸው የአማራ ስም መስጠታቸው ከምንም ነገር በላይ የሚያረጋግጠው ሰፊው የኦሮሞ ሕዝብ በጋብቻ፣ በሃይማኖት፣ በማሕበራዊ ሕይወት፣ በባህል እና በንግድ ግንኙነት የተቀላቀለውን ሰፊውን የአማራ ሕዝብ መውደዱን ነው፡፡ ለዚያውም የመጀመሪያ ስሞች አማርኛ ቢሆኑም ሃይማኖታቸው የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ካልሆነና ወላጆችም የክርስቲያን ስም ካልያዙ በስተቀር የመጨረሻ ስሞች ባመዛኙ ኦሮምኛ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ የኦሮሞ ወላጆች በየትኛውም ቦታ ቢሆን ለልጆቻቸው ስም የሚያወጡት በኦሮምኛ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሕይወት ሂደታቸው ስኬታማ ከመሆን አግዶኣቸው አያውቅም፡፡ የኦሮሞ ስም ይዘው ባለፉት መንግሥታት ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ኦሮሞዎች እልፍ ናቸው፡፡

ወደ አማራው ስንመለስ ከሙያ አንጻር አማራው በትምህርት (ቅኔ ቤት)፣ በንግድ፣ በግብርና፣ በጽህፈት ሥራ እና ከሁሉም በላይ ባብዛኛው በውትድርና ሙያ ተክኗል፡፡ ለምሳሌ አክሱማይ ገና ትንሽ ልጅ በነበረበት ጊዜ የግብፅ ፈርኦን ሆኖ ራምዜስ ወይም ራሚሱ በሚል የንግሥና ስም ነግሦ ነበር፡፡ ዙፋኑን ሊጠብቁ ከ2850 ዓመት በፊት ንጉሡን እና አሁን ሱዳንን በስምዋ ያስጠራችውን እናቱን





ሳዶንያን አጅበው ከኢትዮጵያ እስከ ግብፅ የሄዱት አማሮች ነበሩ፡፡ ሄደውም እስከ ዛሬ ስማቸውን በሚጠቅስ አማርና ደልታ በተሰኘ ባንድ አካባቢ ሰፈሩ፡፡ እሱውም አማርና-ደልታ የሚባለውና አሁንም በዚሁ ስያሜ እየተጠራ በግብፅ የሚገኘው ቦታ ነው፡፡ በኢንተርኔት ውስጥ ገብተው ራስዎ ሊያረጋግጡ ይችላሉ፡፡ እየሱስ ክርስቶስ፣ ማርያም እና ዮሴፍ ከሮማዉያን ጭፍጨፋ ለማምለጥ ወደ ግብፅ ተሰደው ያረፉበት ቦታ ነው ይህ ታሪካዊ አማርና-ደልታ፡፡ ይህ የግብጽ ክፍለ-ግዛት (የላይኛው ግብፅ) አካባቢ፥ እየሱስ ተወልዶ ወደ ግብፅ በሸሸበት ሰዐት የደሸት ዝርያ በሆነና ንጉሥ አማናቱ ተትናይ በተባለ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ይገዛ ነበር፡፡ 350,000 (ሶስት መቶ ሃምሳ ሺ) የሚሆኑ አማሮችም አክሱማይንና ሞግዚቱ የነበረችውን ወላጅ እናቱን ሳዶኒያን ይጠብቁ ነበር፡፡ እላይ እንደጠቀምኩት ሱዳን የምትባለዋ አገር ስያሜዋን ያገኘችው ከሳዶኒያ ነው መላው ሱዳን እና ኑብያ ሁሉ የኢትዮጵያ ግዛት ስለነበሩ፡፡

የቀዳማዊ ምኒልክ የልጅ-ልጅ-ልጅ የሆነው አክሱማይ ወደኋላ ላይ (ከክርስቶስ ልደት በፊት በዘጠነኛው ዓመተ-ዓለም) የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሲሆን አክሱም ከተማን ቆረቆረ፡፡ ይህን ግዙፍ ግንባታ እንዲያከናውኑ መሃንዲሶችን፣ ባለጆችንና ግንበኞችን ከመላው የኢትዮጵያ ግዛት መረጠ፡፡ ሴት ልጁን ሪብላን ለባቢሎኑ (ያሁኗ ኢራቅ) ንጉሥ ለናቡከደነፆር በጋብቻ ሰጠው፡፡ አሁንም የአማራ ወታደሮች ነበሩ ሪብላን አጅበው ወደ ኢራቅ የተጓዙት፡፡ ሪብላም ኢራቅ ደርሳ በስሟ ከተማ መሰረተች፡፡ አማሮቹም እንዲሁ በኢራቅ ውስጥ ‹‹አማራ›› የተባለች ከተማ በስማቸው ቆረቆሩ፡፡ ሪብላ ከተማ በመሬት ነውጥ የተደመሰሰች ሲሆን ‹‹አማራ›› ከተማ ግን እስከዛሬ በኢራቅ ውስጥ በዚሁ ስምዋ ትገኛለች፡፡ ቀደም ሲል በጠቀስኩት በኒው ዮርክ ታይምስ ላይ እንዳነበብነው አማራ የተባለችው የኢራቅ ከተማ ከስምንት ዓመታት በፊት በሺአይት ሙስሊሞች ተይዛ ነበር፡፡

አጼ ካሌብ በ518 (እ.ኢ.ኣ) ክርስቲያን ዜጎቹን ለመታደግ በየመን ውስጥ በተዋጋበት ወቅት አማራ ወታደሮች ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል፡፡ በጦርነቱ መጨረሻ 5000ዎቹ በብሩክ ዘላለም እየተመሩ የናግራን የየመን) ክፍለ-ግዛት ንጉሥ የነበረውን ሕሩይን ሊረዱ ወደ የመን አቅንተዋል፡፡ እነዚህ አስፈሪና የሰለጠኑ ፈረሰኞችም

የነበሩ አማራ ወታደሮች ጎሽ አሰልጥነው እንደ በሬ ይጠምዱ የነበሩ ገበሬዎችም ነበሩ።(47) በአማርና፣ በአስዋን እና በራቂዲ(የአሁኗ ካይሮ) የግብፅ ከተሞች የቀሩ እነዚህ አማራ ወታደሮች በሺህ ለሚቆጠሩ ዐመታት በተጠቀሱት ከተሞች ኖረዋል።

ከአንድ ሺ ስምንት መቶ ዓመት በኋላ ላሊበላ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ሲያቀና ግብፅ ጎራ አለና በሺዎች የሚቆጠሩ አማራ ወታደሮችን ወደ ኢትዮጵያ አመጣቸው። እነዚያ ወታደሮች በአማርና ደልታ ይኖሩ የነበሩና ባላንጣውን የዛጉዌን ንጉሠ-ነገሥት ሃርቤን ለመጣል ላሊበላን የረዱትና የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት እንዲሆን ያበቁት ነበሩ። ላሊበላ አንዴ ንጉሠ-ነገሥት ከሆነ በኋላ ከፍልፍል ቋጥኝ ቤተክርስቲያናትን ወደ ማነጽ ፊቱን አዞረና በላስታ ላሊበላ የሚገኙትን አነጸ። በዚህ ሥራ የረዱት ከግብፅ የመጡት አማሮች እና ባገር ውስጥ የነበሩትም አማሮች፣ አገዎች እንዲሁም ሌሎች ኢትዮጵያውያን ነበሩ። ከግብጽ ከመጡት አማሮች ውስጥ የተወሰኑት በአማራ ሳይንት፣ በዋድላ ደላንታ እና በሁሉም ቤተ-አማራ ከሚገኙ አማራ ዘመዶቻቸው ጋር ተገናኙ። በዚህም ላሊበላ አማሮችን አቀረባቸው። ሥልጣን ሰጣቸው። ቋንቋቸውንና ባሕላቸውንም እንዲያለሙ ፈቀደላቸው።(48) በዚህ አጋጣሚ የላሊበላ አብያተክርትያናት በራሱ በቅዱሱ ንጉሠነገሥት በላሊበላ ተነድፈውና ተመርተው የተፈለፈሉት በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች እንጂ በመላእክት ወይም በፈረንጆች እንዳልሆነ በኩራት መግለፅ እወዳለሁ። ኢትዮጵያውያን አንድ የሚያስደንቅ ሥራ ሲሠሩ ልጆቻቸው የወላጆቻቸውን ክብር ለራሳቸው እንደማስቀረት ለመላእክትና የውጭ ሃገር ሰዎች ለማደል ይዳዳቸዋል። ይህን በራስ አለመተማመን እና ራስን የመናቅ ባህል ማቆም ይገባል።

አማሮች ገበሬዎች የሌሎች ሙያዎች ባለቤቶች ከመሆናቸው ጎን ለጎን ወታደሮችም በመሆናቸው የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ጠባቂዎች፣ የሉአላዊነቷ አስከባሪዎች እና የነፃነቷ ቀናኢዎችም ነበሩ። ኢትዮጵያን ከጠላት ለመከላከል በየአገሩ በመንከራተታቸው እና በመሞታቸውም ተመናምነው ከኦሮሞዎች ብዛት ጋር ሲነፃፀር ቁጥራቸው ሊመናመን ችሎአል።





አማሮች ደግሞ በፍፁም አገው አልነበሩም። "አገው" የሚለው በሁዋላ የአንድ ጎሣ መጠሪያ የሆነው ቃል በ12ኛው ክፍለ-ዘመን በአጼ ላሊበላ ወይም ዳግማዊ አጼ ገብረ-መስቀል ይባል በነበረው ዘመነ-ግዛት ላንድ የጦር ክፍል የተሰጠ ስያሜ ነበር። በሁዋላ በዚህ ስም የተጠሩት ህዝቦች ከዚያ በፊት "ቺያ" እና "ቤጂያ" ይባሉ ነበር። ከዛሬ 3200 ዓመት በፊት አጼ እስያኤል እስያን ድል ካደረገ በኋላ ነበር ከእስያ ያመጣቸው እና ከአገር- በቀል ኢትዮጵያውያን ጋር እንዲዳቀሉ ያደረጋቸው። ለዚህ ነው የቆዳ ቀለማቸው ቀይጥ የሆነው። ሃይማኖታቸውም ቡዲሂዝም እና ሂንዱይዝም ነበር። (49) አጼ ላሊበላ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት በነበረበት ወቅት የዳሞት ንጉሥ አልገብርም ብሎ አመጸ። አጼ ላሊበላ "አገው" የተባለውን ጦር አዘመተበት። ጦሩ ሰባት ነገዶችን ያቀፈ ነበር። እነሱም አዛል፣ ቺያ፣ ኩናማ፣ አማራ፣ ኩንፈል፣ ቢለን እና ሰሌ /ሰላሌ/ የሚባሉ ነበሩ። እነዚህን 7 ጎሳዎች እና ነገዶች ያቀፈው አገው ጦር ግስንገሳ የተባለውን የዳሞት ንጉሥ ከገደለና አካባቢውን በቁጥጥር ስር ካዋለ በኋላ የዳሞትን ወርቅ እና ለምለምነት ወደደውና እዚያው ሰፈረ። በዚህ ምክንያት አካባቢው "ሰባት ቤት አገው" ተባለ። በጦሩ ስም እና ጦሩ በተውጣጣባቸው ጎሳዎች እና ነገዶች ብዛት ይጠራ ጀመር። ስለዚህ አገው ጦርን "አማራ" ብሎ መጥራት ፍጹም ስህተት ነው። አማሮች ላስታን ላሊበላንና የአገው መኖሪያን ሲይዙ የሚከተለው ግጥም ተገጠመ፤

አገው ሲሰደድ

አማራ ሲለምድ።

አማራ እና አገው የተለያዩ ጎሳዎች ባይሆኑ ኖሮ ለምን ግጥሙ ሁለት የተለያዩ ዝርያዎች አድርጎ አቀረባቸው? የለም፤ አማሮች በፍጹም አገው አይደሉም። እራሳቸውን የቻሉ የደሸት እና ማራ ዝርያዎች ናቸው።

አንድ ብርጌድ የአገው ጦር ጎጃም ውስጥ ከሰፈረ በኋላ አገውኛ የተሰኘውን የራሱን ቋንቋ ማልማት ጀመረ። ሆኖም ቋንቋው ባመዛኙ የብሌን ቋንቋ ነበር። የጎጃም አገው ተናጋሪ የሆነ አንድ የማውቀው ሰው አለ። ከኤርትራ ብሌኖች ጋርም ሆነ ከማንኛውም ብሌን ተናጋሪ

| | |
|---|---|
| መስፍን | ፊትአውራሪ |
| መኮንን | አዝማች |
| ብላቴን | የንጉሥ ልጅ አማካሪ |
| ሊጋባ | ባለሟል |
| አቃቤሰዐት | ህግ አስከባሪ |
| የማነሃራሁ | ቀኝአዝማች |
| ፀጋመሃሪሁ | ግራአዝማች |
| ርዕሰብሄር | ባላንባራስ |
| ንቡረዕድ | አልጋወራሽ |
| ቃሉ-አዜ | መሪራስ፤ ፀሀፊ |
| ሊቀ-ደብተራ | መሪጌታ |

ከላይ የቀረቡት አብዛኞቹ የማዕረግ ስሞች እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ድረስ ይሰራባቸው ነበር። የኦሮሞ ዝርያ ያለው ይኩኖ-አምላክ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ተብሎ ዘውድ ከደፋ በኋላ የኦሮሞ መሳፍንት ባገኙት የጋብቻ ዝምድና ተጠቅመው በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ከፍተኛው የሥልጣን እርከን ላይ ወሳኝ ሚና መጫወት ጀመሩ። የስልጣን ተቀናቃኙ የነበረውን የአጼ ላሊበላን ልጅ ይትባረክን በማሸነፍ ረገድ አማሮች ለዋሉለት ውለታ አጼ ይኩኖ አምላክ አማሮችን በየግዛታቸው ንጉሦች፣ አገረ-ገዢዎች፣ አስተዳዳሪዎች፣ የጦር መሪዎች እና አስተማሪዎች እያደረገ ሾማቸው። አጼ ይኩኖ አምላክ ምንም እንኳን ከአማርኛ ይበልጥ ግዕዝ እና ኦሮምኛ የሚያውቅ ቢሆንም "አማርኛ ቋንቋ የማይችል የማንኛውም ጎሣ አባል እድገት አያገኝም፤ ወደ ቤተ-





መንግሥትም መቅረብ አይፈቀድለትም" የሚል ህግ አውጥቶ ለአማርኛ ቋንቋ ያለውን ወገናዊነት ገለጸ። ስለዚህ ሹመት ማግኘት የሚፈልጉ ሁሉ አማርኛ ለመማር ተገፋፉ። በዚህም ግዕዝ በቤተ-ክህነት ብቻ ተወሰነ። ከዓመታት በኋላ አጼ አምደ-ጽዮን ግዕዝ የገዢው መደብ እና የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ቋንቋ እንዲሆን አደረገ። ከአጼ አምደ-ዮን ሞት በኋላ ዳግማዊ አጼ ኢያሱ ደግሞ አማርኛን መልሶ የመንግሥቱ የሥራ ቋንቋ አደረገ። (52) ከላይ እንደተገለፀው ሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት በዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን ‹‹ዮዲት ጉዲት›› እየተባለች በምትጠራው በአስቴር ከመውደሙ በፊት ያደርጉት እንደ ነበረው ይኩኖ አምላክ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሆኖ ከነገሠ በኋላም ኦሮሞዎች ከሰለሞናዊው ንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት ጋር ከመጋባታቸው በተጨማሪ በመንግሥቱ ጉዳዮች ላይም ጉልህ ሚና መጫወት ጀመሩ። (በአውሮጳውያንና በኢትዮጵያውያን ምሁራን፣ በሁለቱም አንደተነገረን ኦሮሞዎች ኩሻውያን፣ አማሮች ደግሞ ሴማውያን ናቸው። ኦሮሞና አማራ ሥረ-መሰረታቸው አንድ ከሆነና ካንድ ምንጭ ከመጡ አንዱ ኩሻዊ ሌላው ደግሞ ሴማዊ እንዴት ሊሆኑ ይችላሉ? በርግጠኝነት ግን ሁለቱም ኩሻውያን ናቸው። አማርኛም በሴማዊ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ ተመድቧል። ይህ ሃሳብም እንዲሁ እንደገና መጤን አለበት። አማርኛ ከማናቸውም ሴማዊ ተብለው ከተመደቡ ቋንቋዎች ይልቅ ለኦሮምኛ የሚቀርብ መሆኑን የሚያመለክቱ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር፣ የአገባብ፣ የቃላት፣ የአባባሎችና የፈሊጣዊ አነጋገሮች ማስረጃዎች አሉና።

ሁለቱ ዘመዳሞች አማራና አንዳንድ የኦሮሞ ነገዶች (አንዳንድ አልኩ፤ ምክንያቱም ሁሉም የኦሮሞ ነገዶች ከአማራ ጋር አልተዋጉም) በድንበር ግጭቶች፣ ባለመግባባት እና በውጪ ኃይሎች በቀላሉ በመገፋት በዱሮው ጊዜ ተዋግተዋል። ግጭቱ ግን የቤተዘመዳሞች ነው። በመሆኑም የከረረ እና የመረረ ስላልነበር ታርቀው እንደገና አብረው ለመኖር በቅተዋል። ከታሪክ ሀቅ እንደምንማረው አማራ የኦሮሞ ረዳቱ እንጂ ጠላቱ አይደለም። ከስጋ ዝምድናው በተጨማሪ ኦሮሞና አማራ በጋብቻ፣ በጉዲፈቻ፣ በሞጋሳ፣ በባሕል፣ በሃይማኖት (በውቃቢ፣ አቴቴ፣ ኢሬቻ ወዘተ. አምልኮና ክብረ-በዓላት)፣ በንግድ፣

የኔን ጉዳይ እንደ አብነት እንውሰድ፤ በሺዎች የሚቆጠሩ አማሮች በቤንች ማጂ እና በቤንሻንጉል ዞኖች ከመሬታቸውና ከመኖሪያቸው ያለ አግባብ ሲፈናቀሉ፤ መሬታቸው፣ ንብረታቸው እና ገንዘባቸው (ይህ ርዕስ በሚጻፍበት ወቅት በፌዴራሉ መንግሥት ታስረው በመመርመር ላይ ባሉ) በአካባቢው ባለስልጣኖች ሲወረስባቸው በጣም አዝኜ ነበር። ደርግ ሥልጣን ከያዘበት ከዛሬ 40 ዓመት ጀምሮ አማሮች ስለተገለሉ እና ሥልጣን አልባ ስለሆኑ ለማንም ስጋት አለመሆናቸውን አውቃለሁ። ይህንን ኢ-ፍትሐዊነት በመቃወም አንድ ግጥም ጻፍሁ። ለተበደሉ አማሮች መቆርቆሬን ያልወደደ አንድ ሰው ኦሮሞነቴን አስታውሶ ሙልጭ አድርጎ በኢ-ሜይል ሰደበኝ። በጋጠወጥነትም እንዲህ አለ፡- ‹‹ከተማረ ጋላ መሀይም ጉራጌ ይሻላል›› ይህን የጻፈው ትክክለኛ ስሙን ደብቆ ነው። እንዲህ ስል በጥሞና ጻፍኩለት፡- ‹‹እባክህ መሀይም ጉራጌ ከተማረ ጋላ መብለጡን በማስረጃ አረጋግጥና አሳምነኝ፤ ይህን ማድረግ ካልቻልክ ከሰብአዊነት ደረጃ ዝቅ ያልክ ተራ እንስሳ ነህ። ንግግርህ ኦሮሞዎችን ብቻ ሳይሆን ብልሆቹን ወገኖቻችንን ጎራጌዎችንም ያዋርዳል። ኢትዮጵያውነትህን እጠራጠራለሁ›› በርግጥ የማይረባ ዘለፋውን እንዴት አድርጎ በማስረጃ ያስደግፈው? ዝም ብሎ ኦሮሞነቴን እየጠቀሰ መሳደቡን ቀጠለ። ከስድቦቹ መሃል የሚከተለው ይገኝበታል።

‹‹የአርማጌዶን ምልክቱ

ኦሮሞ ቅኔ ልዝረፍ ማለቱ››

ከምርጥ የግዕዝ ባለ-ቅኔዎች ውስጥ እንደ አለቃ ጥበቡ፣ አለቃ ደስታ ነገም፣ መሪጌታ ወልዴ እና መሪጌታ ከበደን የመሳሰሉ ኦሮሞዎች እንዳሉ የማያውቅ ወይም ለማወቅ የማይፈልግ ምን ዓይነቱ ጂል ነው!

በርግጥ ያን ያህል ያብከነከነው ችግረኛውን አማራ ደግፌ የጻፍኩት ግጥም ነው። ነቃፊዬ አማራ ወይም ኦሮሞ እንዳልሆነ ግልጽ ነበር። ምክንያቱም አንዳቸውም ራሳቸውን የሚሰድቡና ስለ አንድነት የተጻፈን ግጥም የሚቃወሙ አይደሉምና። ከደቡብ ኢትዮጵያ እንዳልሆነም ተረድቻለሁ። ከየት ሊሆን እንደሚችል አንባቢዬ





እንደሚገምተው እኔም እገምታለሁ። መለስ ብዬ ሳስበው አንድ ነገር ላይ ርግጠኛ ነኝ። የዘር ጥላቻ የሚያስራጭ፣ የኢትዮጵያ ጠላት የሆነ፣ ከሰው ተራ የወረደ፣ ያልሰለጠነ፣ ኋላቀር ክፉ አውሬ ነው። እሱን መልሶ መስደብ ዓየር የመሳብ ያህል ቀላል ነበር። ሆኖም እንደዚያ ማድረግ እንደሱ ዝቅ ማለት በመሆኑ ትቼዋለሁ። ከሱ ጋር መመሳሰስ ክብር እንዲሰማው ማድረግ መስሎ ተሰማኝ። ስለዚህ በዚች ዓለም ላይ ያልተፈጠረ ያህል ንቄ ተውኩት። እሱ ግን እንድናደድና የሱን ዘር በሙሉ በግምት እንድጠላ ተንኩሶኝ ነበር። ያ ደግሞ ኢ-ምክንያታዊነት ነው ለኔ። በሱ የተነሳ ከኢትዮጵያ ሰንደቅዐላማ፣ ከባሕሏም ጋር ምንም ጉዳይ የለኝም ብዬ ኢትዮጵያዊነቴን አልክድም። በፍጹም ይህን አላደርገውም። በዚያ ሁኔታ ላይ የተማረሩ ወንድሞቼ እና እህቶቼ ምን እንደሚሰማቸው የበለጠ እረዳለሁ እንጂ። በኢትዮጵያ ውስጥ በየትኛውም ቦታ ያጋጥሟቸው በነበሩ ይህን በመሳሰሉ የወረዱ እንስሶች በጣም ይበሳጩ የነበሩ የኦሮሞ ወገኖቼ አሉ። ለነዚህ ወገኖቼ የምለግሰው ምክር በእንደዚህ ዓይነቱ እርጉም አውሬ የተንኮል ድርጊት እንዳይናደዱ ነው። ማን መሆናችሁን ታውቃላችሁ። የነገሥታት ንጉሥ፣ የካህናት አለቃ እና የሁሉም ኢትዮጵያውያን አባት የነበረው የኢትዮጵ፣ እንዲሁም ሙት ታስነሳ የነበረችውና የደሸት ወላጅ እናት የሆነችው የታላቅዋ ነቢይት የሽምሽል እና የነቢዩና የጠቢቡ የደሸት የራሱ ተወላጆች ናችሁ። እንዲሁም የኦሮሞ እና የአማራ ምንጭ የሆነው የታላቁ ፈላስፋ እና ነቢይ የደሸት ልጆች ናችሁ። ምንጫችንን ይበልጥ ራቅ ስናደርገው ደግሞ አይሁዶች ገና ወደ አካባቢው ከመምጣታቸው በፊት የኢየሩሳሌም ገንቢ እና ንጉሥ የነበረው ከሃሊውን ግዚአብሄርን በምድር ላይ የወከለው፥ የካህናቶች ካህናት፥ የንጉሦች ንጉሥ የመልከፃዲቅ ዝርያ ነን። ለዚህ ለትልቁ አባታችን የአይሁዶች አባት የሆነው አብርሃም ታላቅነቱን አክብሮ ይሰግድለት እና ምርቃቱን ለማግኘት አሥራት ያገባለት ነበር። ይህንንም አባታችንን፥ እንዲሁም ኢትዮጵን እና ደሸትን፥ አማሮችና ሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ዘመዶቻችን ከኛ ጋራ ይጋሩአቸዋል።

ኢትዮጵያን ለምን በጣም እንደማፈቅራት እና ኢትዮጵያዊነቴንም ለምን እንደምወድ አንዳንድ ኦሮሞ ወዳጆቼ ይገርማቸዋል። ኢትዮጵያን አፈቅራታለሁ፤ ምክንያቱም የኦሮሞ እና የሁሉም ኢትዮጵያውያን መገኛ

የሆነውን የታላቁን አባታችንን የኢትዮጵን ስም ይዛለች። ኢትዮጵያዊነቴንም እወደዋለሁ፤ ምክንያቱም አያት ቅድመ-አያቶቼ በዓለም መድረክ ላይ የተጫወቱት ሚና ያኮራኛል። አያት ቅድመ-አያቶቼ ልዩ የሆነውን ቅርሳቸውን የተውልን የኢትዮጵያን ዳር ድንበር አዘለለው መሆኑን አውቃለሁ። ስለዚህ ራሴን "ኦሮምያ" በምትባል ጠባብ ቦታ ላይ ብቻ መወሰን አልፈልግም። ምክንያቱም ጠቅላላዋ ኢትዮጵያ በመላው ቁመትዋ እና ስፋትዋ የኔ፣ የኦሮሞ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ እንዲሁም የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ናት። እስዋንም ለማትረፍ እና ለኛ ለማስተላለፍ ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስክሰዋልና። በሕዝቦቿ ቅርፀ-መልክ፣ በቋንቋዎቿ ብርቅነት፣ በሙዚቃዋ ጥልቀት፣ በጭፈራዋ አማላይነት፣ በስነ-ቃልዋ፣ በታሪኳ፣ በፍልስፍናዋ እና በስነ-ጽሑፍዋ እማረካለሁ። በቤተክርስቲያን ስነ-ሥርዓትዋ እና በሃይማኖትዋ፣ በዜጎቿ መልካም ጠባይ፣ በጨዋነታቸው፣ ለሕይወት ባላቸው አመለካከት እና በአእምሮኣቸው ረቂቅነት እና ጥልቀት እሳባለሁ። በክብራቸው አስፈሪነት፣ በንግግራቸው ተራቃቂነት፣ በጥበባቸው ውስብስብነት፣ ከችግራቸው ባሻገር በአለው ኩራታቸው ጥልቀት እና ተወዳዳሪ በማይገኝለት ገርነታቸው እና በተቅለመለመው ብዙሐንነታቸው እሸነፋለሁ። የኦሮሞዎችን እና የአማሮችን ጨምሮ ይህን እና ይህን መሳዩ የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያውያን ባህርይ እና ማንነት ለኢትዮጵያ እና ለልጆቿ ስሜታዊ እንድሆን ያስገድዱኛል።

ስለዚህ እኔ ፍቅሬ ቶሎሳ (ቶለሳ) ጂግሳ፣ የሳሌም ንጉሥ እና የእግዚአብሔር ከፍተኛ ካህን የነበረው የመልከጼዴቅ ልጅ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት እና የዐለማቱ ፈጣሪ ከፍተኛ ካህን የነበረው የኢትዮጵ ልጅ፣ እንዲሁም ነቢይ እና ፈላስፋ የነበረው የጎጃም ንጉሥ የደሸት ልጅ ነኝ። አዎ! ኦሮሞዎችን፣ አማሮችን፣ ሃድያዎችን፣ ከምባታዎችን፣ ሶማሊዎችን አፋሮችን፣ ጉራጌዎችን እና ሌሎቹንም ኢትዮጵያውን ጨምሮ እንደ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ እኔም የነዚህ ሁሉ ልጅ ነኝ።

የኢትዮጵ ልጆች መሆን እና በዚህም ኢትዮጵያዊ መሆን የሚታፈርበት ሳይሆን የሚኮራበት ነው። የመልከጼዴቅ እና የኢትዮጵ ተወላጅ መሆን የሚያስገርም እና በእጅጉ የሚያኮራ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው እየሱስ ክርስቶስ ወደፊት በኢየሩሳሌም በሚገዛበት





ወቅት በመልከጼዴቅ ሥርዓት መሰረት ነው የሚገዛው። (53) በርግጥ የሚታየውን እና የማይታዩትን ዐለማት የፈጠረ እየሱስ ክርስቶስ የሙሴ ወንድም እና የአይሁድ ከፍተኛ ካህን በነበረው በአሮን ስርዐት አይደለም የሚገዛው። የአሮን ካህንነት ከመልከጼዴቅ እና ከኢትዮጵ አጅግ ዝቅ ያለ ነው። እንዲሁም የንግሥተ-ሳባ እና የንጉሥ ሰለሞን ልጅ እስከ ሆነውና ከእናቱ ሃይማኖትና ባሕል ይልቅ የአባቱ ሃይማኖትና ባሕል በልጦበት ሊቀ-ካህናትነትን በአይሁድነት እስከለወጠው እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ ድረስ ለአንድ ሺ አመታት ባንድ ጊዜ የነገሥታት ንጉሦች እና የካህናት አለቆች ከነበሩት ስፍር ቁጥር ከሌላቸው ከኢትዮጵ ወራሾች ካህንነት በጣም ያነሰ ነው።

ልድገመውና የመልከጼዴቅ፣ የኢትዮጵ እና የተከታዮቹ ንጉሠ-ነገሥትነት እና ሊቀ-ካህናትነት ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ልንኮራበት የሚገባን ትልቅ ነገር ነው።

የኢትዮጵ ልጆች በመሆናችንም ልንኮራ ይገባናል፤ ምክንያቱም ከ4000 ዓመት በፊት የኢትዮጵያን ግዛት መስርቶልናል፤ መጻህፍትም ጽፏል፤ ስለ መንግሥት መዋቅር እና ስለ ህገ-መንግሥት ተከታዮቹን አስተምሯል፤ ፊደላችንን አሻሽሏል።(54) ባለፉት ጊዜያት መላው አፍሪቃ ኢትዮጵያ እየተባለ እንዲጠራ ምክንያት ሆኗል፤ እንዲሁም ታላቅነቱንና ምርቃቱን ለልጆቹ አስተላልፎ ነገሥታት፣ ከፍተኛ ካህናት፣ ነቢያት፣ ፈርኦኖች እና ህንደኬዎች እየሆኑ ኢትዮጵያን፣ እስያን፣ አረቢያን፣ ኒጀርን፣ ናይጀሪያን፣ ግብፅን፣ ኑቢያን፣ ሱዳንን፣ ታንዛኒያን፣ ሞሪታኒያን እና ሊቢያን በጽድቅና በፍትህ አስተዳድረዋል። የኢትዮጵያን ሥልጣኔንም አሰራጭተዋል። ከታላላቅ ንግሥታት መካከል ፋሲላ እኖኒ በሚል ስያሜ የምትጠራውና በአጼ ፈንታሌ ተሾማ 13ኛዋ ህንደኬ የነበረችው መደባይዋ ኦሮሞ ትጠቀሳለች።(55)

ቀደም ሲል እንደዘረዘርኩት ከ2000 አመታት በኋላ አጼ ባዚን ንጉሠ-ነገሥት በነበረበት ወቅት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "የምሥራቅ ጠቢባን" የተባሉት 12ቱ የኢትዮጵ ዝርያዎች አሥራ ሁለት ነገሥታት እና ጠቢባን ሆነዋል። እጆቻቸውን ለእግዚአብሔር ዘርግተውም "ዮጵ" በመባል የሚታወቀውን ልዩዉን የኢትዮጵያን ቢጫ ወርቅ፣ ከርቤ እና

እጣን ሥጦታ አበርክተዋል። የእየሱስ የሥጋ ዘመዶች የሆኑት አይሁዳዉያን መወለዱን እንኳ ገና ሳይሰሙ ነው እንግዲህ በትንቢቱ መሰረት እነዚህ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ትንቢቱን የፈፀሙት። ትንቢቱም "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የሚለው ነው(56)። እነዚህ አሥራ ሁለት "ወንድማማች ንጉሦች" ሁሉንም የኢትዮጵያን ሕዝቦች ይወክላሉ። ለምሳሌ ንጉሥ መጋል፣ ንጉሥ ሙርኖ፣ ንጉሥ መቃዲሺ እና ንጉሥ አጎጃ ጀባን እንደ ቅደም ተከተላቸው ኦሮሞን፣ አፋርን፣ ሶማሌን እና አማራን ይወክላሉ።

ከ3500 ዓመት በፊት ሌላው የኢትዮጵ ተወላጅ የሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምድያም ሊቀ ካህናት እና የሙሴ አማት፣ እኛ ኢትዮጵያውያን የትሮ-አብ ብለን የምንጠራው ትልቅ ሰው ነው። ሙሴን በእግዚአብሔር ሥርዓት ለ40 ዓመት ያሰለጠነው። ከዚህም በላይ፥ በአይሁዳውያን መካከል ይነሳ የነበረውን ፀብና ውዝግብ ሙሴ ለብቻው ለመዳኘት ሲደክምና አይሁዳውያኑም ሲጉላሉ ዐይቶ ሙሴ የፍትህ እና የፍርድ ሥርዓት እንዴት መዘርጋት እንደ አለበት የመከረው እሱው ነው። (56)

እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ነጻ ለማውጣት የተጠቀመበት እና ቃል በቃል በቀጥታ እያነጋገረው አሥርቱ ትዕዛዛትን የሰጠው ብቸኛው ሰው ሙሴ በመሆኑ ሙሴ እንደ ታላቅ ሰው ይታይ ነበር። የኛ የኢትዮጵያውያን ጥንተ-አባት የትሮአብ ግን ከሙሴ እጅግ የሚልቅ ታላቅ ሰው ነበር። ምክንያቱም ቃለ-እግዚአብሔርን፣ መንገደ መለኮትን እና የፍትህ ሥርዓት አዘረጋግን ለሙሴ ያስተማረ የታላቁ እግዚአብሔር ሊቀ ካህን ነበርና። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተገለጸው ሙሴ ለየትሮአብ ባክብሮት ቢያጎነብስለት አያስገርምም። የትሮአብ የመልከፀዴቅ እና የኢትዮጵ ዝርያ ስለነበረ እሥራኤላውን ከባርነት ነፃ ከወጡ ከ3 ዓመታት በሑዋላ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሆነ። አይሁዶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሃባብ ብለው የሚጠሩት የየትሮአብ ልጅ አባ-ብሄር በታላቁ ካህን ልጅነቱ ቃለ-እግዚአብሔርን በደንብ ያውቅ ስለነበር በጉዞአቸው ላይ ህዝቡን በማስተማር ረገድ ሙሴን ለብዙ አመታት ረድቶታል። (57)





የጥንተ-አባታችን የኢትዮጵ ዝርያ ከሆኑ ታላላቅ እንስቶች መካከል፤ የንጉሥ ሰለሞንን ጥበበ-እውቀት ሽታ ከኢትዮጵያ ኢየሩሳሌም ድረስ በመጓዝዋ እየሱስ ያሞገሳት ኢትያኤል (ንግሥተ-ሳባ) (58)፣ በዘራቸው ኢትዮጲያውያን የነበሩት የንጉሥ ዳዊት አያት ሩት እና ሐብሴ እያልን የምንጠራት ወላጅ እናቱ አዶሊያ ይጠቀሳሉ። ሩት ዓለምን የሚያድነውን ኮከብ (የእየሱስን) መወለድ የተነበየው የነቢዩ በልአም የልጅ ልጅ ስትሆን እርሷ ራሷም ስለ ኮከቡ መወለድ ራዕይ ዐይታ ስለ ነበር ያየችውን ራዕይ ለማሰብ የኮከቡን ቅርፅ ሰርታ በልጅዋ በኦቤድ አንገት ላይ አስራላት ነበር። ውሎ አድሮ ንጉሥ ዳዊት ያንን የኮከብ የእጅ-ሥራ ከእናቱ ወረሰ። ዛሬ ድረስ የአይሁድ ሕዝቦች እና መላው ዓለም ያንን የኮከብ ቅርፅ "የዳዊት ኮከብ" እያሉ ይጠሩታል። ስለ ኮከቡ ሠራተኛ ስለ ሩት ግን ምንም አይነሳም። እየሱስ ክርስቶስ "የዳዊት ልጅ" እየተባለ ስለሚጠራ እና እናቱ የኛዋ ኢትጵያዊትዋ አዶሊያ (ሐብሴ) በመሆንዋ(59) በእየሱስ ክርስቶስ ደም ውስጥ ኢትዮጵያዊ ደም ስላለ እየሱስ ክርስቶስ የስጋ ዘመዳችን ነው ብንል ያስኬዳል። ታዲያ ይህ ሁሉ በኢትጵያውነታችን የሚያኮራን አይደለምን?

የሰንደቅ ዓላማን ጉዳይ በተመለከተ ከኦሮሞ የነፃነት ተዋጊዎች ጋር የተያያዘ ሰንደቅ ዓላማ አለ። አራት ወይም ሶስት የተለያዩ ሰንደቅ ዓላማዎች ነበሯቸው። በቀይ እና በአረንጓዴ ቀለማት ያጌጠውንና ማሕሉ ላይ ዋርካ ዛፍ ያለበትን እመርጠዋለሁ። ምክንያቱም የኦሮሞ አዛውንት አካባቢያቸውን እና ሕይወታቸውን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ለመምከር ሲሰበሰቡ ከሚጠለሉባቸው ዛፎች አንዱ የተወከለበት ስለሆነ ነው። ባለፈው ጊዜ ስለነበረው የኦሮሞ ዴሞክራሲ ብዙ የሚናገረው አለ። አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለማት ያሏትን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማም እወዳታለሁ። እስዋንም የምወድበት በቂ ምክንያት አለኝ፤ ከ3400 ዓመት በፊት የፈጠራት የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የአፋር፣ የሶማሊ፣ የሀዲያ እና የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አባት የሆነውና በንግሥና ስሙ "ሰንደቅ አልማ" ይባል የነበረው አጼ ወይም እሴ በመሆኑ ነው።(60) ሰንደቅ-ዐላማ የተባለችው ለዚህ ነው። እሴ የኢትዮጵ ዝርያ ሲሆን እኔ እስከማውቀው ድረስ ፍፁም አቻ የሌለው እጅግ ታላቅ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ነበር። በመልከጼዴቅ እና

በኢትዮጵ ስርዐት መሰረት መንፈሳዊውንና ዓለማዊውን ሥልጣናት አጣምሮ የያዘ ሊቀ-ካህናት እና ንጉሠ-ነገሥት ነበር። እንደ አባቶቹ እሱም ሁለት ታላላቅ ሥልጣኖች ነበሩት ማለት ነው፡- መንፈሳዊ እና ፖለቲካዊ። ከፍ ያለ ዝናን ያተረፈ፣ እንደ ጥንታዉያን የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች የረጂም ዕድሜ ባለፀጋነትን ምስጢር ተረድቶ 480 ዓመት የኖረ፣ ሩቅ ምሥራቅን አስገብሮ በክህነት ስሙ "እስያ" ብሎ ሰይሞ(61) እስከ ዛሬ አህጉሩ "እስያ" እየተባለ የሚጠራለት እጅግ ታላቅ ንጉሠ-ነገሥት ነበር።

እሴ ልዩ ችሎታ የነበረው ሳይንቲስትም ነበር። አዝዕርትንና እፅዋትን እንዲሁም እንስሳትን እያዳቀለና አዳዲስ እፅዋትንና የእንስሳት ዝርያዎችን እያስገኘ በቤተ-መንግሥቱ ያኖር የነበረ የመጀመሪያው በራሄ-ጂን/ዘረ-መል/ መሐንዲስ (Genetic Engineer) ነበር። በሰው በራሄ-ጅን DNA ላይም ምርምር ያደርግ ስለ ነበር ኢትዮጵያውያንን ከእስያውያን፣ እና ከመካከለኛው ምሥራቅ ምርኮኞቹ ጋር እያጋባ ዛሬ ያለን ልዩ የሆነው ቀይጥይጥ የቆዳ ቀለም፣ የፊት ቅርጽ፥ የተለያየ የጸጉር አሠራር እና ልዩ ልዩ የነገድ አካላዊ ቅርፀ-መልክ እንዲኖረን አስችሏል። የተለያዩ ቀለማት እንዳሉት ውብ አበባ በልዩነት እንድናምር ያደረገን እሱ ነው። የቋጥኞችን ተፈጥሮ የተረዳ ጂኦሎጂስት እና አንዳንድ እንስሳትን ከሌሎች ጋር እያዳቀለ አዳዲስ እንስሳት እንዲፈጠሩ ያደረገ ታላቅ ሳይንቲስትም ነበር። በፈልሳፊነቱም ገና በጥንቱ ዘመን የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዐላማ ፈጥሮ የመንግሥት ባለሥልጣናት በየሥራ ቦታዎቻቸውና በየ ሰረገላዎቻቸው ላይ እንዲሁም ከሰራዊቶቻቸው ፊት እና ኋላ እንዲያውለበልቧት በሕግ ደንግጓል። ይህን ሲያደርግ ምናልባት በዐለም የመጀመሪያው መሪ ሳይሆን አይቀርም። የሰንደቅ ዓላማው ቀለም አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ሰማያዊ ነበር። በጥቁር አባይ መነሻ ላይ ሆኖ የሰንደቅ-ዐላማዋን መፈጠር ባወጀበት ዕለት ለዜጎቹ ንግግር ሲያደርግ እግዚአብሔር ምድርን ዳግመኛ በውሀ እንደማያጠፋት ለኖኅ ቃል እንደገባለት እና ለቃል ኪዳኑ ምልክት ቀስተ-ዳመናን እንዳቆመ፤ የቀስተ-ደመናው ቀለማትም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንደሚወክሉ አስታውሶ በተመሳሳይ መንገድ አጼም በነገሥታት እና በሕዝቦች፣ በሱ እና በተወዳጅ ዜጎቹ መካከል ያለውን ፍቅር ለማሰብ ሰንደቅ-ዐላማዋ ከፍ





ብላ እንደምትውለበለብ ማድረጉን ገልጾ ነበር። በገለጻው መሰረት አረንጓዴ ምድራዊነትን፣ ቢጫ ፍቅራችንን፣ ሰማያዊ ደግሞ መንፈሳዊነታችንን ይወክላሉ። የመስቀያው አናት በወርቅ እና በብር የተለበጠ የኮከብ ቅርፅ እንዲሆንና ሰንደቅ-ዐላማዋን ያላውለበለበ ማንኛውም ባለሥልጣን በጥብቅ እንዲቀጣ ደንግጎ ነበር።(62)

እንግዲህ ሰንደቅ-ዐላማችን በአጼ እስያኤል ለመፈጠርዋና የ3300 ዓመት እድሜ ባለጸጋ ለመሆንዋ ማስረጃው አጼ በዚህ ዘመን መግዛቱ የተመዘገበ መሆኑ እና "ሰንደቅ-ዐልማ" ስመ-መንግሥቱ እንደነበረ መረጋገጡ እንዲሁም ሰንደቅ-ዐላማችን የዚያን ልዕለ-ሰብ መሪ ስም ይዛ እስከዛሬ "ሰንደቅ-ዐላማ" እየተባለች መጠራትዋ ነው። ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ከውጪ ወራሪዎች ሲከላከሉ ያፈሰሱትን እና የሚያፈሱትን ደም ለመወከል ታስቦ ከጊዜ በኋላ ሰማያዊው በቀይ ተተክቷል። ከ700 ዓመታት በፊት ይኩኖ አምላክ (የኦሮሞው ዝርያ ንጉሠ-ነገሥት) እና ነአኩቶ ለአብ (የዛጉዌው ንጉሠ-ነገሥት) በአቡነ ተክለሃይማኖት ሽምጋይነት የዛጉዌን ሥርወ-መንግሥት ለሠለሞን ሥርወ-መንግሥት አባላት ለማስተላለፍ ሲስማሙ ይቺ ሰንደቅ-ዐላማ እንደገና ተጠቅሳለች። (63)

አዎ! በርካታ ኦሮሞዎች፣ አማሮች፣ አፋሮች፣ ሀዲያዎች፣ ትግሬዎች እና ሌሎችም ኢትዮጵያውን ይቺ ሰንደቅ-ዐላማ በነፃነት አየር ላይ በክብር እንድትውለበለብ ደማቸውን አፍስሰዋል። ከ24 ዓመት በፊት አንዱ ከእሷ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ግለሰብ ባርቆበት እንደነበረው ላባቶቻችን ይቺ ሰንደቅ-ዐላማ ተራ "ጨርቅ" አይደለችም። የሚገርመው ያ ግለሰብ ሞቶ ወደ መቃብር ሲወርድ አስክሬኑ ይቺኑ የጠላትንና "ጨርቅ" ብሎ ያናናቃትን ሰንደቅ-ዐላማ ለብሶ መታየቱ ነው።

በቅርቡ ያገራችን ታሪክ በአድዋ፥ በማይጨውና በደፈጣ ውጊያ ጦርነቶች እንኩዋ ለዚች ሰንደቅ-ዐላማ ከተፋለሙ ኦሮሞዎች ጥቂቶቹን ለማስታወስ፣ የአጼ ምኒልክ ባለቤት ንግሥት ጣይቱ ብጡል፣ ፊታውራሪ ሃብተ-ጊዮርጊስ ዲነግዴ፣ ፊታውራሪ ባልቻ አባ-ነፍሶ፣ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣ ጀኔራል ጃጋማ ኬሎ፣ እና ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ፣ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ፣ ኮሎኔል አብዲሳ አጋ፣ ራስ አበበ

አረጋይ፣ ደጃዝማች ገብረ-ማሪያም ጋሪ እና ወይዘሮ ልክ የለሽ በያን የሚጠቀሱ ናቸው:: የኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዐላማ በነጻነት ዓየር ላይ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ በጀግንነት የተዋጉትንና ያልተዘመረላቸውን የኦሮሞ ጦረኞች በሙሉ እዚህ መዘርዘር ያስቸግራል::

አባቴ ቶሎሳ(ቶለሳ) ጂግሳ ዋኬኔ ሰላማዊ ዜጋ እንጂ ጦረኛ አልነበሩም:: ዳሩ ግን የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዐላማ በኢትዮጵያ ዐየር ላይ ለማውለብለብ ከጣልያን መፋለም ነበረባቸው:: በወሊጋው ገዢ በቢትወደድ መኮንን ደምሴ ስር ሆነው በ1928 ዓ.ም በማይጨው ጦርነት ከፋሺስት ጣልያን ጋር ተዋግተዋል:: የኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዐላማ ለኢትዮጵያውያን የነጻነት ምልክት ነበረች፤ ነችም:: በኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዐላማ ቀለማት የተሠራ ያንገት ልብስ አንገቴ ላይ ጣል አድርጌ ያየኝ አንድ ወጣት ኦሮሞ ባንድ ወቅት አንባረቀብኝ:: ሰንደቅ-ዐላማዋ ከ3300 ዓመታት በፊት በራሱ ቅድመ አያት የተፈለሰፈች እና በርካታ አባቶቹ እና እናቶቹ ለህልውናዋ የተዋደቁላት መሆንዋን ቢያውቅ ኖሮ ይህን ያህል ጠላትዋ አይሆንም ነበር:: በቅርቡም አረብ አገር በሠራተኛነት የምታገለግል አንዲት ኦሮሞ ሴት የኢትዮጵያን ባንዲራ በጥላቻ አቃጥላለች:: ጥንተ-አባትዋ አጼ ወይም እሴ እና ለሰንደቅ-ዐላማዋ ሕልውና የተዋደቁ እነዚያ ሁሉ ታላላቅ ኦሮሞዎች ድርጊትዋን ቢያዩ ኖሮ በመቃብር ውስጥ አጽማቸው በሀዘን በተገላበጠ ነበር::

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዐላማ በሌሎች እልፍ አእላፍ ኢትዮጵያውን ግን እጅግ ትፈቀራለች:: ለምሳሌ አርቆ አሳቢው የአፋሮች መሪ ክቡር ደጃዘማች ዓሊ ሚራህ ባንድ ወቅት "እኛ ቀርተን ግመሎቻችን እንኩዋ የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዐላማ ያውቋታል" ሲሉ ተናግረዋል:: ኢትዮጵያውያንን በሙሉ የሚወክል ብሔራዊ ምልክት መኖር ስላለበት ሁሉም ኢትዮጵውያን ይቺን ሰንደቅ-ዐላማ ከፍ አድርገው ማውለብለብ ይገባቸዋል:: ይህ ሀቅ የተለያዩ ጎሳዎች ልዩ የሆነውን ቅርሳቸውን እና ባሕላቸውን የሚያንጸባርቅ የራሳቸው የጎሳ አርማ እንዳይኖራቸው የሚያግድ አይደለም:: ለምሳሌ የኦሮሞ ነጻነት ተፋላሚዎች መካከሉ ላይ የዋርካ ዛፍ ያለበት አርማ አላቸው:: ይህንን አርማ ካገራቸው ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዐላማ ጋር በየአካባቢያቸው ከፍ አድርገው ማውለብለብ ይችላሉ:: ይሁንና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምልክት





የሆነችው ሰንደቅ-ዐላማ ከሁሉም አካባቢያዊ አርማዎች ቀድማ መውጣት፣ ልቃ መታየት አለባት:: ምክንያቱም የሁላችንም የሆነችዋን አንዲት አገር የምትወክል የአንድነት ተምሳሌት ናትና:: አንድ ቡድን በሌሎች ጎሣዎች ላይ የራሱን አርማ ብቻ ልጫንባችሁ ቢል ኢ-ፍትሀዊነት እና ጭቆና ነው:: አርማው በማይወክላቸው ጎሳዎች ላይ፣ ለምሳሌ ሠንደቅ-ዐላማችንን "ግመሎቻችን እንኳ ያውቋታል" በሚሉት በአፋሮች ላይ ብሄራዊው ሰንደቅ-ዐላማ ቀርቶ ያንድ ጎሳ አርማ ብቻ ይውለብለብባችሁ ማለት አግባብ አይደለም:: አሁን የአለችው ባለ አረንጓዴ፥ ቢጫ፥ ቀይ ቀለም ሰንደቅ-ዐላማ ለበርካታዎቹ ኢትዮጵያውያን ጥልቅ ትርጉም አላት:: ትርጉሙ ከኦሮሞዎችም ጋር ይያያዛል:: አረንጓዴው የኢትዮጵያን ልምላሜ ብቻ ሳይሆን የኦሮሞንም ምድር አረንጓዴነት ያመላክታል:: ኦሮሞዎች የሚወዱአቸውን ጨፌዎች እና ዛፎችን ጭምር:: ቢጫው መንፈሳዊነትን ሲገልፅ፥ የጥንቶቹን ከኢትዮጵና ከደሸት በቀጥታ የወረዱትን የኦሮሞ ነቢያት እና ካህናት መንፈሳዊነትንም ጭምር ያንፀባርቃል:: ቀዩ ደግሞ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ከውጪ ወራሪዎች ለመከላከል፥ ከሁሉም ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር ሆነው ኦሮሞዎች ያፈሰሱትን ደም ይዘክራል:: ስለዚህ ሶስቱም ቀለማትና ሰንደቅ-ዐላማዋ ራስዋ ከኦሮሞዎች ጋር የቀጥታ ግንኙነት አላቸው:: የጎሣ አርማንና የሀገር ሰንደቅአላማን አስመልክቶ የምለው ይህንኑ ነው::

የሀረሩ አውሳ አዳል ግራእጁ አህመድ ኢብራሂም መሀመድ ምንም እንኳን መፃህፍትና አብያተክርትያን ቢያቃጥልም፥ የሚመሰገንበት ገድል ነበረው:: ከሁሉ አስቀድሞ በኢትዮጵያዊነቱ፥ በኢትዮጵያ ሰንደቅአላማና በኢትዮጵያ አንድነት አይደራደርም ነበር:: ቱርኮችና አረቦች ኢትዮጵያን እንዲያጠፋ ሊጠቀሙበት የጦርመሳሪያና የራሳቸውን ወታደሮች ቢሰጡትም፥ ሙሉ በሙሉ አሻንጉሊታቸው ሆኖ ፍላጎታቸውን አላሙዋላላቸውም:: አብረውት የነበሩት ሱማሌዎች የእኛ ግዛት ከአዋሽ ማዶ አይደለም ሲሉት፥ ቱርኮቹም ያንተ ግዛት ከአዋሽ በታች ነውና ከዛ አትለፍ ተመለስ ሲሉት፥ የእሱ አቅድ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ መግዛት ብቻ ሳይሆን የጥንትዋን ኢትዮጵያን ክብርና ዝና ለማስመለስ ግብፅን፥ የመንን እና ሱዳንን

ጭምር ለመቆጣጠር ስለነበር አሻፈረኝ አላቸው፡፡ ሱማሌዎቹንም ፈጃቸው፡፡

እላይ በተጠቀሰው ምክንያት በተሰለፈበት ቦታ ሁሉ የኢትዮጵያን አረንጓዴ፥ ቢጫ ቀይ ሰንደቅአላማ እና አረቦች የቸሩትን የእስልምና ሃይማኖቱን የሚወክለውን ግማሽ ጨረቃ ያለበትን አረንጓዴ አርማ በኩራት ያውለበልብ ነበር፡፡ የሁዋላ ሁዋላ መላውን ኢትዮጵያን እጠቀልላለሁ ቢልም በመጀመሪያ አነሳሱ ከንጉሠነገሥቱ፥ ከኦሮሞው ተወላጅ ከአፄ ልብነድንግል እውቅና አግኝቶ የንጉሡን ሴት ልጅ አምራ-ፅዮንን አግብቶ ከአዋሽ መለስ እስከ ሀረር ለመግዛት ነበር ፡፡ ስለዚህም ንጉሡን፥ ልጅህን አምራ-ፅዮንን ዳርልኝና አስልሜ አግብቻት፥ ተዛምደን ከአዋሽ በታች እየገዛሁ ግብሬን እያገባሁልህ ላገልግልህ፤ ፍቅራችንም ይፅና፤ ብሎ ደብዳቤ ፃፈለት፡፡ ክርስትያኑ ንጉሥ ግን አልባሌ ነው ብሎ የሚያስበውና ክርስትያን ያልሆነው ሰው ልጅህን ላግባ በማለቱ እንደ ድፍረት ቆጥሮት የዛቻ ደብዳቤ መለሰለት፡፡ ግራእጁ አህመድም በዚህ ተናዶ ጦርነቱን ቀጥሎ ንጉሡን እና ቤተሰቡን እስከመጨረሻው አሳደዳቸው፡፡ ልእልት አምራ-ፅዮንም እንኳን ልታገባው ቀርቶ፥ ግራኝን በጀግንነት ተዋግታው ሞተች፡፡

ግራኝ አህመድ ግን ያን ሁሉ ጦርነት ያኪያሂድ የነበረው በሙስሊም ሰራዊት ብቻ ታጅቦ አልነበረም፡፡ ከሙስሊሞቹ ጋር የተደባለቁ የአማራ ክርስትያን፥ የኦሮሞና የሌሎችም ጎሳዎች ለሱ ይዋጉለት ነበር፡፡ በማእረጋቸውም እስከ ደጃዝማች ያደርሳቸው ነበር፡፡ ቢሆንለት ኖሮ የእስላም መንግሥት መስርቶ፥ ሃበሻ ያላትን መላዋን ኢትዮጵያን በስነስርአት ለማስተዳደር ያስብ ነበር እንጂ ቅዋሜ ያላኪያሄዱበትን ዜጎቹን ወይም በግዛቱ ስር የወደቁቱን ወገኖቹን የግድ ስለሙ ብሎ አያስጨንቅም ነበር፡፡ እኔን ካልተቃወማችሁኝ በመሬታችሁና በሃይማኖታችሁ እንድትፀኑ እፈቅድላችሁአለሁ፡፡ ከተቃወማችሁኝ ግን፥ማስለም ብቻ አይደለም ባርያ አድርጌ ለአረቦች እሸጣችሁአለሁ ብሎ አውጆ ነበር፡፡ ያለውንም አድርጎታል፡፡

እንግሊዞች በአፄ ቴዎድሮስ ላይ ላደረጉት የመጨረሻ ውድቀት ተጠያቂ አፄ ዮሃንስን ብቻ የሚያደርጉ ሰዎች አሉ፡፡ ስለ እውነት እንነጋገር ከተባለ፥ እሳቸው ብቻ ተጠያቂ አይሆኑም፡፡ እሳቸው በአፄ



ቴዎድሮስ ላይ የነበራቸው የግል ቂም ብቻ ነው፡፡ እሱም አንደኛ፥ እሳቸው ካሳ ምርጫ ተብለው በሚጠሩበት ሰዐት የአፄ ቴዎድሮስ ወታደር ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተው እምባቦ ላይ ከደጃዝማች ውቤ ጋር አፄ ቴዋድሮስ ሲዋጉ፥ ካሳ ምርጫና የእናታቸው ወንድም አጎታቸው አርአያ ድምፁ ተሳትፈው ነበር፡፡ አርአያ ድምፁ ከደጃዝማች ውቤ ተጣልተው፥ ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር አድመው፥ በዚሁ በእንባቦ ጦርነት ላይ ጀብድ በመሥራታቸው ከድል በሁዋላ ራስ ብለው ሾመው የትግራይ ገዢ አደረጉዋቸው፡፡ ካሳ ምርጫ ግን ምንም ልዩ ጀብድ ባለማሳየታቸው ባላምባራስ ብለው የመጨረሻ ዝቅተኛ ማእረግ ዳረጉዋቸው፡፡ ይህ ካሳ ምርጫን አስቆጣቸው፡፡ በሞግሼአቸው በካሳ ኃይሉ ላይ ቂም እንዲይዙም አስገደዳቸው፡፡ ይህ በእንደዚህ እያለ አፄ ቴዎድሮስ ሸዋን በወረሩበት ሰዐት በሰላም የተቀበለንን አትዝረፉ ብለው ለወታደሮቻቸው አወጁ፡፡ የባላምባራስ ካሳ ምርጫ ሰራዊት ግን አዋጁን ጥሶ ከመንደር ገብቶ ሲዘርፍ ባላገሩ የአፄ ቴዎድሮስን ትእዛዝ ሰምቶ ስለነበር ዘራፊዎቹን ተቃውሞ አሳደዳቸው፡፡ ዘራፊዎቹ ሲሮጡ ያዩት አፄ ቴዎድሮስ የሚሮጡበት ምክንትያት ሲነገራቸው ሲሆን አዋጁን አክብረው ባላገሩን አለመዝረፍ ነበረባቸው፡፡ ከዘረፉ ደግሞ ቆመው መጋተር ነበረባቸው እንጂ ወታደሮች ሆነው እንዴት ይሸሻሉ፥ ብለው በንዴት እጅ እግራቸውን ቆረጡአቸው፡፡ በላምባራስ ካሳ በዚህ ተበሳጭተውና ይበልጥ ቂም ይዘው ወደ ህውዜን ሄደው አገው ንጉሴ ከተባለ አንድ እልህ አስጨራሽ የአፄ ቴዋድሮስ ጠላት ጋር አብረው ሸፈቱ፡፡ ከዛም ከእንግሊዞችና ፈረንሳይዎች ጋር ደብዳቤ እየተላላኩ በንጉሠነገሥቱ ላይ እያሴሩና እርዳታ እየጠየቁ ከረሙ፡፡ እንግሊዞች አፄ ቴዎድሮስን ሊቀጡ በመጡ ጊዜ ባላምባራስ በአጋጣሚው ተጠቅመው ከእንግሊዞች ተመሳጠሩ፡፡ ይሄው ነው፡፡ ይህንንም ተንኮል ባላምበራሱ ብቻ ሳይሆኑ በአፄ ቴዎድሮስ ላይ ቂም የያዙ ሁሉ መሳፍንት ፈፅመውታል፡፡

ለኦሮምያ ካርታም ያለኝ አመለካከት እንዲሁ ነው፤ በቅርቡ በማሕበራዊ ድረ-ገጽ በቀሰቀስኩት ውይይት ላይ ኦሮሞው ጠባብዋን "ኦሮምያን" ሳይሆን ጠቅላላዋን ኢትዮጵያን እንደ ቤቱ ሊያያት ይገባል ብዬ ላቀረብኩት ሀሳብ አንድ የኦሮሞ ብሔርተኛነት አራማጅ "ጠቅላላዋን ኢትዮጵያን "ኦሮምያ" ብለን እንጥራና ይህን አጀንዳ

እንዝጋው” ሲል አስተያቱን ሰጥቷል፡፡ የዚህን ሀሳብ ተተግባሪነት በኋላ እናያለን፤

አንዳንድ ኦሮሞ ጓደኞቼ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ነገር እንደሌለ እና ኢትዮጵያውያን እንዳልሆኑም ይነግሩኛል፡፡ ኦሮሞዎች ኢትዮጵያውያን ካልሆኑ ምን ሊሆኑ ነው ታዲያ? በኔ አስተያየት ኢትዮጵያዊነቱን የሚክድ ማንኛውም ኦሮሞ፣ ኦሮሞዎች በ16ኛው ክፍለ-ዘመን በማደጋስካር በኩል ከእስያ የመጡ የውጪ ወራሪዎች ናቸው የሚል ሃሳብ በስህተት ከሚያራምዱ ጋር የሚስማማ ነው፡፡ ኦሮሞዎች ከውጪ የመጡ ወራሪዎች ከሆኑ በየትኛው መብታቸው ነው ካንዲት አገር ላይ “ኦሮምያ” የምትባል ግዛት የሚቆርሱት? ያንተ ያልሆነውን ዳቦ እንዴት ትበላዋለህ? ኦሮሞዎችስ ፍፁም ኢትዮጵያውያን ነን፡፡ አማሮች፣ አፋሮች፣ ሀዲያዎች፣ ጉራጌዎች፣ ጋምቤላዎች፣ ከምባታዎች፣ ወላይታዎች፣ ሶማሊዎች እና ሁሉም ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵ ልጆች እንደሆኑ ሁሉ ኦሮሞዎችም የኢትዮጵ ልጆች ናቸው፡፡ ለኢትዮጵያዊነት ሥነ-ልቡና፣ ለታሪክዋ፣ ለባሕልዋ፣ ለቋንቋዋ፣ ለሥነ-ጽሑፍዋ፣ ለማሕበራዊ ሳይንስዋ፣ ለአንትሮፖሎጂዋ እና ለጆኦግራፊዋ እንደሌሎቹ ዜጎች የድርሻቸውን ብዙ አበርክተዋል፡፡ በተጨማሪም ባለፉት 3500 ዓመታት ውስጥ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከልክ በላይ ነው፡፡ ይህን ሁኔታ *“ኦሮሞ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያበረከተው አስተዋጽኦ”* በሚለው ጽሁፌ አብራርቸዋለሁ፡፡ ምንም እንኳ ወታደሮች እና ቀሳውስት ሆነው የተጫወቱትን ሚና ባለፉት 3000 አመታት ውስጥ ቀላል ባይሆንም በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ውስጥ በጋብቻ ገብተው የኢትዮጵያን የታሪክ አቅጣጫ ላለፉት 700 ዓመታት ሲወስኑ መኖራቸው የማይታበል ሀቅ ነው፡፡ ይኸውም ሰለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት በሸዋ እንደገና ከመሰረተው ከአፄ ይኩኖ አምላክ ... ከአዛዥ ጫላ የልጅ ልጅ እና ከጊፍቲ ሀዊ መንዲያ ልጅ ከተስፋ-እየሱስ የግዛት ዘመን ጀምሮ ነው፡፡

ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ አዲስ መጥ ባዕዳን አለመሆናቸውን ይህ በሚገባ ያረጋግጣል፡፡ ኦሮሞዎች ባዕዳንም አይደሉም፤ ታሪክ ሳይኖራቸው የሚጮሁ ድመቶችም አልነበሩም፤ የታላቁን አባታቸውን የኢትዮጵን ደማቅ ታሪክ አንግበው የሚያገሱ አንበሶች ነበሩ እንጂ፡፡





ናቸውም፡፡ ኦሮሞዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥረው እዛው ግሩም ድንቅ ታሪክ የሠሩ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የማይቀበል ማንኛውም ኦሮሞ አንድም የገዛ ታሪኩን የማያውቅ ወይም ክብር ማንነቱን አሽቀንጥሮ የጣለ፥ የሚያሳዝን ሰው ነው፡፡

-----------------------//-------------------------

# *መደምደሚያ*

ከዚህ በላይ በቀረበው ጽሁፍ ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ ባእዳን እንግዶች ሳይሆኑ ልክ እንደ አማራና እንደሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አገር በቀል ኗሪዎች መሆናቸውን ተምረናል። ከዚህም አልፎ ኦሮሞና አማራ በደም የተዛመዱና ላለፉት 3500 ዓመታት በማህበራዊ አኗኗር፣ በባሕል፣ በቋንቋ፣ በሐይማኖትና በመንፈሳዊ ሕይወት የተቀላቀሉ እና የተዋሃዱ መሆናቸውንም አውቀናል። ኦሮሞዎች በኢትዮጵያ አመራር ውስጥ ቁልፍ ሚና የተጫወቱ እና ለኢትዮጵያ ስልጣኔም ጉልህ ድርሻ ያበረከቱ ዜጎች ናቸው። ያበረከቱት አስተዋፅኦም በስነ-ልሳን፣ በፍልስፍና፣ በመንፈሳዊ ባህል በወታደራዊ ሳይንስ፣ በቅኔ፣ በቤተ ክህነት አገልግሎት፣ በዳንኪራ፣ በሙዚቃ እና በእደ-ጥበብ ዘርፎች ተዘርዝሮ ቀርቧል። የኦሮሞና የአማራ ግንኙነት በብዙ መልኮች በርስበርስ መፈቃቀድ፣ መፈቃቀር እና መከባበር ላይ የተመሰረተ እና በርግጥም በአርአያነት የሚታይ መሆኑን ተገንዝበናል። ባለፈው ታሪካቸው ብቻ ሳይወሰኑ ለወደፊትዋም ኢትዮጵያ አንድነት፥ እድገት እና ሰላም ምሰሶ እንደሚሆኑ አልጠራጠርም።

ስለ ኦሮሞና አማራ የዘር ሃረግ ምንጭ ስንመረምር፥ ምንጩ አንድ መሆኑን ተገንዝበናል። ከሌላው ሁሉ ማስረጃ ይበልጥ አንዱ ላይ ብቻ እንኳ ብናተኩር በቂ ነው። ኦሮሞና አማራ በአባይ ዙርያ በጎጃም ከአንድ ምንጭ ለመቀዳታቸው ሶስት የማይነቀነቁ



ማረጋገጫዎች አሉ። አንደኛ፥ አበው ኦሮሞዎች ስነፍጥረትና አባታችን (ደሽት) ከውሃ ውስጥ ፈለቀ ብለው ማውጋታቸው፥ ሁለተኛ፥ በዛው በምስራቅ ጎጃም ውስጥ ከውሃ የፈለቁ እነማይ ወይም የውሃዎቹ ሰዎች የሚባሉ አማሮች አሁንም መኖራቸው፥ እና ሶስተኛው ደሽት የሚባል ሰው እና ዘረ-ደሽት የሚባሉ ሰዎች በዛው በጎጃም እንደነበሩ መታወቁ ነው። ለምሳሌ በ *ውዳሴ ማርያም* አንድምታ ላይ ስለ ዘረ-ደሽት የተመዘገበ ከትውልድ ትውልድ ወደ እኛ የተላለፈ እውነት አለ። በዚህ መፅሃፍ ውስጥ ደሽትን ዘረደሽት ብለው በመጥራት፥ ዘረ-ደሽት ከአባይ ምንጭ አጠገብ ሆኖ በጎሲናው ሲመሰጥ፥ ድንግል ማርያም ወደ ፊት የምትወልደውን እየሱስን አቅፋ፥ በእነሱ ላይ ደግሞ እየሱስ ሲወለድ ወደ ፊት የኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ ወጥታ የደሽትን ልጆች ሰብአሰገልን ወደ ቤተልሄም የምትመራቸውን ኮከብ በቅድሚያ ዐያት። እሱ የዐያትን ኮከብ ከዐያት ከ 1600 ዐመታት በሁዋላ እውነትም ከኢትዮጵያ በተጨማሪ፥ ሱዳን እና የመን ይደርስ የነበረው የኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ ታየች። በአዬ ባዚን ንጉሠነገሥትነት ስር በዛን ጊዜ 12 ነገሥታት የነበሩት የደሽት ልጆች ወንድማማቾች የኦሮሞን፥ የአማራን፣ የትግሬን እና የሌሎቹንም ጎሳዎች ወክለው፥ የኢትዮጵያን ቢጫ ወርቅ፥እጣን እና ከርቤ ይዘው፥ በኮከብዋ እየተመሩ ወደ ቤተልሄም አምርተው ለህፃኑ መሲህ ለእየሱስ ክርስቶስ ገፀበረከት አቅርበዋል። ለምሳሌ ከኦሮሞ ንገሦች አንዱን፥ ከአማራዎቹ ደግሞ ዐራቱን በስም ለመጥቀስ ያህል ኦሮሞው፥ የደርዲና፥ የሰገል፣ የኦርመን (የኦሮሞ)፥ እና የማጂ ንጉሥ፥ አማሮቹ የጎጃም እና የጣና ውስጥና ዙሪያ፥ በደሽት ኩተማ ተቀማጭነት የጎንጂ እና ጉንዳጉንዲት ነገሥታት አጎጃ ጀባን፤ አቦል፤ቶና እና በረካ ነበሩ። የኦሮሞው ንጉስ መጋል ወደ ቤተልሄም ከመጓዙ በፊት የመደባይ-ኦሮሞ ካህናትን ይዞ እና የኦሮሞ ወታደሮችን ክተት ብሎ፣ በአፋሮች ድንቅ መርከብ ተሳፍሮ፥ ባህር ተሻግሮ፥ ስፔንን እና ፖርትጋልን ቅኝ እንደ ገዛ እዚህ ፅሁፍ ከላይ መቀመጡን ተገንዘበናል። እንግዲህ እውነተኛው እና ትልቁ ታሪካችን ይህንን ይመስላል። ይህም ሲባል፥ ዘመዳሞቹ ኦሮሞዎችና አማሮች ባለፈው ታሪካቸው ብቻ ሳይኩራሩና ሳይገቱ፥ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋራ በመተባበር ለወደፊትዋ ኢትዮጵያ አንድነት፥ እድገት እና ሰላም ምሰሶ እንደሚሆኑ አልጠራጠርም።

## Notes:

## The True Origin of the Oromo and Amara

1. Getachew Haile, *Ye Aba Bahriy Dersetoch,* p. 76.

2. Bairu Tafla. *Asma Giyorgis and His Work,* p.308.

3. Bairu Tafla. ibid., p. 309.

4. Bairu Tafla. ibid., p. 311.

5. Bairu Tafla. ibid. p. 138.

6. Aleka Taye Gebremariam, *Ye Ethiopia Hizb Tarik,* pp. 60-61.

7. Tekle Tsadik Mekuria, Ke Atse Libine-Dengil Iske Atse Tewodros, p. 94

8. Yilma Deressa, Ye Ethiopia Tarik Basra Sidestengaw Kifle Zemen,pp. 214-215.

9. Mohammed Hassen, *The Oromo of Ethiopia*, p. 4

10. Getachew Haile. ibid., pp. 26-27.





11. Bonnie K. Holocomb and Sisai Ibssa, *The Invention of Ethiopia ,p.5.*

12. Harold Marcus. *A History of Ethiopia,* pp. 34-35.

13. Tekletsadik Mekuria, ibid., p. 9.

14. Bairu Tafla, ibid., p. 204.

15. Bairu Tafla, ibid., p. 879.

16. N.Y, Saturday, October 21, 2006.

17. Aman Belai, Metsehafe Abrihit, p. 490-492.

18. Bairu Tafla. ibid., p.202.

19. Merigeta Lisane Work Gebre Giorigis, *Tintawi Sirate Mahlet Ze Abune Yared Liq,*

pp. 14-16.

20. Aman Belai, *Metsehafe Subae Ka'le.* p. 309.

21. Aman Belai. Ye Tintwa Ye Ethiopia Tarik. p. 350.

22. Aman Belai, Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik. p. 41.

23. Aman Belai, .ibid. p. 43.

24. Aman Belai. ibid. p. 57.

25. Aman Belai, pp. 306-308.

26. *Strong's Greek Lexicon.* #2739 and #4028, available on line.

27. Psalm 68: 31.

28. Aman Belai, Ye Tintwa Ethiopia Tinsae Tarik, p.10

29 Aman Belai. Metsihafe Subae Zebeaman Kale, pp. 320-334.

30. Aman Belai. ibid., p.324.

31. Psalms, 72:10.

32. Aman Belai, locit., p. 324.

33. Getachew Haile, ibid., p.76.

34. G.W.B. Huntingford, in *The History of The Galla of Ethiopia,* p.12.

35. Aman Belai. Hizbaw Kedamawi Mestawet Tarik, p. 28.

36. *The Holy Bible,* Numbers 21, 14.

37.Bairu Tafla, Asmagiyorgis and His Works, p. 310.

38. Aman Belai. Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik, p. 30.

39. Aman Belai,*Metsihafe Abrihit*, p.479.

40. Aman Belai. Ye Tintwa Ethiopia Tinsae Tarik. p. 202.



41. Aman Belai. Ye Tinatwa Ethiopia Negestat Tarik, pp. 53-55.

42. Aman Belai, *Metsehafe Abrhit*, p. 4.

43. Ye Ethiopia Tarik, Ke Atse Libine-dengil iske Atse Tewodros, p. 21

44. Aman Belai, Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik, p45.

45. Aman Belai. *Yetintwa Ethiopia Tinsae Tarik,* p.320.

46. Belai, Aman, Metsehafe Subae, p.59.

47. Aman Belai, *Metsehafe Abrihit*, p.308.

48. Aman Belai, ibid., pp.485-487.

49. Aman Belai, Metsihafe Subae Zebemaman Kale, pp.127-128.

50. Bairu Tafla, Asma Giyorigis and His Works, p. 202.

51. Aman Bela. *Mtesehafe Abrhit*, p. 521.

52. Aman Belai, Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik, pp. 34-35.

53. 101 Psalm 110, 4

54. Aman Belai. Mesehafe Subae Kale Zebeaman, pp. 58-59

55. Aman Belai, ibid. p. 309.